አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ
BIIROO BARNOOTA BULCHINSA MAGAALAA FINFINNEE
ADDIS ABABA CITY ADMINISTRATION EDUCATION BUREAU

# አማርኛ

## እንደመጀመሪያ ቋንቋ

## የመምህር መምሪያ



## ፩ኛ ክፍል

# አማርኛ

## እንደመጀመሪያ ቋንቋ

## የመምህር መምሪያ

## ፪(2)ኛ ክፍል

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ


**አዘጋጆች**

ሙሉቀን ፈንታ መኮንን

አሻግሬ ግባቱ ገበየሁ

አዲስዓለም አሸኔ ለማ

**ገምጋሚና አርታኢዎች**

መስፍን ደፈረሱ ወ/መድህን

ትንቢት ግርማ ኃይሉ

ፋሲል ብዙነህ በቀለ

**የጥራት ተቆጣጣሪና ገምጋሚ**

ፍሬሕይወት አሰፋ ከበደ

**አስተባባሪ**

ጌታቸው ታለማ አጥናፉ

**አቀማመጥ እና ስዕል**

እንጦጦ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ(TMS)

©      መብቱ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ የተጠበቀ ነው::
2014 ዓ.ም
አዲስ አበባ

## ምስጋና

ይህን የትምህርት መጽሐፍ ከዝግጅት ጀምሮ በውጤት እንዲጠናቀቅ፣ የካበተ ልምዳቸውን በማካፈል፣በፓናል ውይይት ሃሳብ በማፍለቅና በማቅረብ፣ በከተማችን በሚያስተምሩ መምህራን እንዲዘጋጅ በማድረግ፣ አስፈላጊውን በጀት በማስፈቀድ እንዲሁም በጥብቅ ዲስፕሊን እንዲመራ በማድረጋቸው ላደረጉት ከፍተኛ ድጋፍ የትምህርት ቢሮ ኃላፊ ዶ/ር ዘላለም ሙላቱ የላቀ ምስጋና ይገባቸዋል፡፡

ለሥራችን መሳካት ሁልጊዜ አብረውን በመሆን፣ በሚያጋጥሙ ችግሮች መፍትሄ በመስጠት፣ የአፈጻጸም ሂደቱን በመከታተል፣ በመገምገም እንዲሁም የዝግጅቱ ስራ ቁልፍ ስራ መሆኑን ተረድተው ትኩረት በመስጠት ከጎናችን ለነበሩ የትምህርት ቢሮ የማኔጅመንት አባላት የስርዓተ ትምህርት ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ አድማሱ ደቻሳ፣ የትምህርት ቴክኖሎጂ ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ ዳኛው ገብሩ፣ የመምህራን ልማት ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ ሳምሶን መለሰ ፣ የትምህርት ቢሮ ኃላፊ አማካሪ ወ/ሮ አበበች ነጋሽ፣ የትምህርት ቢሮ ጽ/ቤት ኃላፊ አቶ ሲሳይ እንዳለ፣ የቴክኒክ አማካሪ አቶ ደስታ መርሻ ላበረከቱት አስተዋጽኦ ምስጋና ይገባቸዋል፡፡

በመጨረሻም መጽሐፉ ተጀምሮ እስከሚጠናቀቅ ድረስ የትምህርት ቤት ርዕሳነ መምህራን ለስራው ልዩ ትኩረት በመስጠት አዘጋጅ መምህራንን ስለላካችሁልንና የሞራል ድጋፍ ስላደረጋችሁም ምስጋናችንን እናቀርባለን፡፡

# ማውጫ


ይዘት ገጽ

መግቢያ......................................................................................

ምዕራፍ አንድ

ልብስ..........................................................................................1

ምዕራፍ ሁለት

ወቅቶች......................................................................................9

ምዕራፍ ሶስት

ታሪኮች....................................................................................17

ምዕራፍ አራት

የአትክልት ቦታ.........................................................................27

ምዕራፍ አምስት

የአካባቢ ንጽህና አጠባበቅ........................................................41

ምዕራፍ ስድስት

ባህላዊ ሙዚቃ...........................................................................54

ምዕራፍ ሰባት

መልካምሥነ-ምግባር................................................................64

ምዕራፍ ስምንት

የምግብ አዘገጃጀት....................................................................79

ምዕራፍ ዘጠኝ

ዲጅታል ቁስ.............................................................................92

ምዕራፍ አስር

የዱር እንስሳት........................................................................105

መርኅ ትምህርት......................................................................117

# መግቢያ

## ለተጠቃሚዎች

ይህ መጽሐፍ የ፪ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ እንደ መጀመሪያ ቋንቋነት ለሚያስተምሩ መምህራን የተዘጋጀ ነው፡፡ በዚህ መጽሐፍ የሚያስተምሩ መምህራን የሚያስተምሯቸው ተማሪዎች በብቃት ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብና መፃፍ እንዲችሉ ለማድረግ ተሻሽሎ የተዘጋጀ የስርዓተ ትምህርት አካል ነው፡፡

መጽሐፉ ሲዘጋጅ መነሻ ያደረገው የሚያስተምሯቸው ተማሪዎች ማዳመጥ፣ የመናገር፣ የማንበብና የመፃፍ ክሂላቸውን በእኩል ደረጃ እንዴት እንደሚያስተምሩና እንደሚያለማምዱ መጠቆም ላይ የተመሰረተ ነው፡፡

ይህ መጽሐፍ የመጀመሪያ ቋንቋ ስርዓተ ትምህርትን እና መርሃ ትምህርትን መሰረት አድርጎ የተዘጋጀ ሲሆን የሚከተሉትን መሰረታዊ መርሆዎች አካቷል፡፡

## መርህ አንድ

መምህር ለተማሪዎች ስዕሎችንና ርዕሶችን በመመልከት የቅድመ ማዳመጥና ቅድመ ንባብ ጥያቄዎችን እንዲገምቱ በማድረግ ተረቶችን ወይም ታሪኮችን በማዳመጥና በማንበብ የማዳመጥና የማንበብ፣ የመጻፍና የመናገር ክሂላቸውን እንዲያዳብሩ ያደርጋቸዋል።

## መርህ ሁለት

ተማሪዎች በመምህር የሚነበብላቸውን ታሪክ ወይንምንባብበሚገባ በማዳመጥና በማንበብ የአዳምጦ/የአንብቦ መረዳት በንግግርም ሆነ በፅሁፍ በግልፅ ቋንቋ መናገርና መፃፍ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይህንንም ለማድረግ ይችሉ ዘንድ በተከታታይ የመናገርና የመፃፍ ተደጋጋሚ ልምምድ እንዲያደርጉ ያግዟቸዋል፡፡

## መርህ ሶስት

መምህር ተማሪዎች ባዳመጡትና ባነበቡት ፅሁፍ ውስጥ አዳዲስ ቃላትን እንደየ አጠያየቃቸው የሚወክሏቸውን ፍቺ በመፃፍ በተገቢው የቃላት አሰዳደር ስርዓት በመጠቀም ዓረፍተ ነገሮችን እንዲመሰርቱ ያለማምዷቸዋል።

## መርህ አራት

መምህር ተማሪዎች በተለመዱና በአዳዲስ ቃላት የተመሰረቱ ዓረፍተ ነገሮችን ማንበብ እንዲችሉ ልልምድ እንዲያደርጉ ያግዟቸዋል።

## መርህ አምስት

መምህር ተማሪዎች አዳዲስ ቃላትን ሲያዳምጡና ሲያነቡ የአዳዲስ ቃላትን ፍቺያቸውን አብረው እንዲማሩ ፤ የሚያደምጡትንና የሚያነቡትን ሃሳብ እንዲረዱ፤ የቃላት እውቀታቸውን በማሳደግ በንግግርና በፅሁፍ ሃሳባቸውን በአግባቡ እንዲገልፁ ያግዟቸዋል።

# መልዕክት ለመምህራን

ውድ መምህር ተማሪዎች የቋንቋን ትምህርት በአግባቡ ይገነዘቡ ዘንድ የመምህራን እገዛ ያስፈልጋል፡፡ ስለሆነም ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ተግባራት ከግንዛቤ በማስገባት ተማሪዎችን በሚገባ ሊያግዟቸው ይገባል፡፡

፩. ለተማሪዎች የተለያዩ ታሪኮችን፣ ተረቶችን… ይንገሯቸው/ ያንብቡላቸው፡፡

፪. ለተማሪዎች የነገሯቸውን (ያነበቡላቸውን) ታሪክ (ተረት) ተማሪዎች መልሰው እንዲተርኩ (እንዲናገሩ) በተጨማሪም ራሳቸው የሚያውቁትን እንዲተርኩ ያበረታቷቸው፡፡

፫. በተማሪ መጽሐፍ ላይ የቀረቡትን ምንባቦችና ተግባራት እንደየመመሪያቸው በየጊዜው እየተከታተሉ ያሰሯቸው፡፡

፬. ተማሪዎች በራሳቸው ተነሳሽነት የተለያዩ ፅሁፎችን እንዲያዳምጡ፣ እንዲናገሩ፣ እንዲያነቡና እንዲፅፉ ያበረታቷቸው፡፡

፭. ለተማሪዎች ተጨማሪ ተግባራትን በመስጠት በቤታቸው ተዘጋጅተው በመምጣት በተግባር እንዲያሳዩ ያድርጓቸው።

አማርኛ
፪ኛ ክፍል

# ምዕራፍ አንድ
# ልብስ

18
ክፍለ ጊዜ

## የምዕራፉ አላማዎች

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- ከአዳመጡት ጽሑፍ አጠቃላይ ሐሳብ ይለያሉ።
- ከተሰጣቸው ፅሑፍ ውስጥ ዋናውን ሐሳብ ይናገራሉ።
- ለተለመዱ ቃላት ፍቺ ይሰጣሉ።
- ባለ ሶስት ሆሄ ቃላትን ያጣምራሉ ይነጥላሉ።
- ሆሄያትን አቀናጅተው ቃላት ይፅፋሉ።

## የምዕራፉ ይዘቶች

- ማዳመጥና መናገር
- የንግግር ድምፅ ግንዛቤ
- የቃላት ጥናት
- ማንበብ
- የፅህፈት ትክክለኝነት
- ድምፀት

## ((( ማዳመጥ

# ልብስና መስሪያዎቹ

**መምህር፡-**

- በተማሪ መጽሐፍ ላይ ያሉትን የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች ያሰሯቸው፡፡
- ተማሪዎች ለሚሰጧቸው ምላሾች ማበረታቻ ይስጧቸው፡፡
- የሚከተለውን ምንባብ እንደተማሪዎች ሁኔታ በተመጠነ ድምጽና ፍጥነት ያንብቡላቸው፡፡
- በምንባቡ መካከል ያለውን የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄ የምንባቡ መካከል ላይ ሲደርሱ ተማሪዎችን በመጠየቅ ስለወደፊቱ ሀሳብ እንዲገምቱ ያድርጓቸው፡፡

ልብስ ከሰው ልጆች መሰረታዊ ፍላጎቶች መካከል አንዱ ነው፡፡ልብስ ማለት ለሰውነታችን ከለላ በመሆን ሠውነታችንን ከብርድ፣ ከፀሐይና ከመሳሰሉት የሚከላከልልን ነው፡፡

…ተማሪዎች ልብስ ከምን ከምን የሚሰራ ይመስላችኋል?…

ልብስ ከተለያዩ የመስሪያ ቁሶች ይዘጋጃል፡፡ ይኸውም ከጥጥ፣ ከቆዳ (ሌጦ)፣ ከሱፍ ወዘተ. ይሰራል፡፡ ከጥጥ ጋቢ፣ ሂጃብ፣ነጠላና የሐበሻ ቀሚስ ሲሰራ ከቆዳ ኮት፣ ጃኬት፣ ኮፍያ፣ ሱሪ፣ ወዘተ. ከሱፍ ደግሞ ሱሪ፣ ኮት፣ ጃኬት፣ … ይሰራሉ፡፡

**መምህር፡-**

- በተማሪ መጽሐፉ ያሉትን የአዳምጦ መናገር ጥያቄዎች ምንባቡን መሰረት በማድረግ ተማሪዎች በቃል እንዲመልሱ ያበረታቷቸው፡፡
- ተማሪዎች ለሰጡት ምላሽ በቂ ግብረ መልስና ማብራሪያ ይስጧቸው፡፡

## ⊶ ቃላት

**መምህር፡-**

- ✓በተማሪ መጽሐፍ ትዕዛዝ ፩ ላይ ያሉትን የተጓደሉ ፊደላትን በጽሑፍ እንዲያሟሉ ያግዟቸው፡፡
- ✓በተማሪ መጽሐፍ በትዕዛዝ ፪ ላይ ያሉትን ቃላት ቦታ በመቀያየር ሌሎች ቃላት እንዲመሰርቱ ያበረታቷቸው፡፡
- ✓ትክክለኛውን እርማት ይስጧቸው፡፡

የተግባሩ መልስ (ትዕዛዝ ፪)

1. በቀለ
2. ነጠቀ
3. ለማዳ
4. ደለበ
5. ብስል

## ☞ ሞክሼ ፊደላት

**መምህር፡-**

- ስለሞክሼ ፊደላት ምንነትና አይነት በቂ ማብራሪያ ለተማሪዎች ይስጧቸው፡፡
- ተማሪዎች የሞክሼ ፊደላቱን ቅርጽ፣ ስያሜና ዝርያ በደብተራቸው ፅፈው እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡
- ተማሪዎች ሞክሼ ፊደላትና ዝርያቸው የያዙትን ቃላት ከዓረፍተ ነገሮች ውስጥ እንዲለዩና ሞክሼ ፊደላትን በመነጠል እንዲያሳዩ ያድርጓቸው፡፡
- ልዩ ፍላጎት የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ካሉ የመማር ማስተማሪያ ዘዴዎችን እገዛ ከሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ሁኔታ ጋር አስማምተው ያቅርቡ፡፡

| ሀሌታው (ሀ) | ሐመሩ (ሐ) | ብዙኀኑ (ኀ) |
| --- | --- | --- |
| ንጉሡ (ሠ) | እሳቱ (ሰ) | |
| አልፋው (አ) | ዐይኑ (ዐ) | |
| ጸሎቱ (ጸ) | ፀሐዩ (ፀ) | |

## ንባብ

# የበዓል ልብስ

**መምህር፡-**

- በተማሪ መጽሐፍ ላይ ያሉትን የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች ያሰሯቸው፡፡
- ተማሪዎች ለሚሰጧቸው ምላሾች ማበረታቻ ይስጧቸው፡፡
- በተማሪዎች መጽሐፍ ላይ ያለውን "የበዓል ልብስ" የሚለውን ምንባብ ተማሪዎቹ እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡
- ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን በምንባቡ መሰረት እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡
- ለሰጡት ምላሽም እርማት ይስጧቸው፡፡

## አቀላጥፎ ማንበብ

**መምህር፡-**

- በተማሪ መማሪያ መጽሐፍ ላይ "የበዓል ልብስ" በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ተማሪዎች አቀላጥፈው እንዲያነቡ ያግዟቸው፡፡
- በመቀጠል የንባብ መከታተያ ሰንጠረዥ በማዘጋጀት ተማሪዎች ሲያነቡ ደቂቃ በመያዝ የንባብ ችሎታቸውን እየገመገሙ ማበረታቻና አስተያየት ይስጧቸው፡፡
- በተጨማሪም ተማሪዎች ሌሎች አጫጭር ፅሁፎችን ሰዓት(ደቂቃ) ተይዞላቸው እንዲያነቡ ሁኔታዎችን ያመቻቹላቸው፡፡
- በተግባሩም የንባብ ፍላጎታቸው መሻሻሉን ይከታተሉ፡፡
- የንባብ ፍጥነታቸውን ለመከታተልም የወሰደባቸውን ጊዜ በሰንጠረዥ ላይ በመመዝገብ ይከታተሉ፡፡

## ቃላት

**መምህር፡-**

- ስለተመሳሳይ የቃላት ፍቺ ማብራሪያና ምሳሌ ከሰጡ በኋላ በተማሪ መማሪያ መጽሐፍ ላይ ትዕዛዝ ፩ን የክፍል ሥራ ይስጧቸው፡፡
- ለሰጧቸው የክፍል ሥራ እርማት ይስጧቸው፡፡

**የትዕዛዝ ፩ መልስ**

1. ሠ
2. ሐ
3. ለ
4. ሀ
5. መ

- በተማሪ መጽሐፍ ትዕዛዝ ፪ ላይ በስዕል የቀረቡትን አልባሳትና ቀለሞችን በሚገባ እንዲገነዘቧቸው ምሳሌውን ያብራሩላቸው፡፡
- ከዚያም ወደቃል በመቀየር እንዲፅፉና እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡
- ተግባሩን በታዘዙት መሰረት እየሰሩ መሆናቸውን እየዞሩ ይከታተሉ፡፡
- በተጨማሪም ይዘቱን ለማበልጸግ ሆሄ የተቀረፀባቸው ስዕሎች፣ ፍላሽ ካርድ፣ ባለቀለም ወረቀቶች፣ ቅርፃ ቅርፆች፣ ካርቱኖች፣ ጥቁር ሰሌዳ … ይጠቀሙ፡፡

☞ውስብስብ ፊደላት

መምህር፡-

- ስለውስብስብ ፊደላት ምንነት ገለፃ ከሰጡ በኋላ በተማሪ መጽሐፍ ላይ በቅደም ተከተል £ተቀመጡትን ውስብስብ ፊደላት ተማሪዎቹ ተራ በተራ እ£ተነሱ እንዲያነቧቸው ¦በረታቷቸው፡፡
- ተማሪቹን በቡድን በማስቀመጥ በምሳሌው መሰረት ከውስብስብ ፊደላት መካከል አራቱን በመምረጥ ቃላት እንዲመሰርቱ ¦ድርጉ፡፡
- ተማሪቹ በቡድን በመሆን በውስብስብ ፊደላት የመሰረቱትን ቃላት በሚገባ ተመልክተው ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡

☞ማጣመርና መነጠል

መምህር፡-

- በተማሪ መጽሐፍ ትዕዛዝ ፩ ላ¨ £ቀረቡትን ውስብስብ ፊደላት ነጣጥለው እንዲፅፉ ያበረታቷቸው፡፡
- በመቀጠል በተማሪ መጽሐፍ ትዕዛዝ ፪ ላ¨ £ቀረቡትን ፊደላት በማጣመር ውስብስብ ፊደላት እንዲፅፉ ያበረታቷቸው፡፡
- ነጣጥለውና አጣምረው Eየፃፉቸው ውስብስብ ፊደላት እርማት ይስጧቸው፡፡

## ✍ ጽሕፈት

**መምህር፡-**

- ❖ በተማሪ መጽሐፍ ትዕዛዝ ፩ ላ¨ በቀረበው ምሳሌ መሰረት የተለያዩ ድርጊታዊ ገለጻዎችን ለተማሪዎቹ በሚገባ በማሳየት ድርጊቱን በቃላት እንዲፅፉ አድርጓቸው፡፡
- ❖ ተማሪዎቹ ድርጊታዊ ገለጻውን በሚገባ በቃላት መግለፃቸውን ያረጋግጡ፡፡ ከዚያም ተማሪዎችም እርስ በርስ ድርጊታዊ ገለጻዎችን እየተገበሩ በቃላት እየተከ ተግባሩን የበለጠ እንዲያዳብሩት ጊዜ ይስጧቸው፡፡
- ❖ የሚከተሉትን ቃላት ድምፅዎን ከፍ አድርገው በመናገር ተማሪዎቹ እንዲፅፏቸው ያድርጉ፡፡
  1. አሯሯጠ
  2. አሟላ
  3. ፏፏቴ
  4. ትምህርቷ
  5. እጇ

## ☞ስርዓተ-ነጥብ

**መምህር፡-**

- ✓ ስለስርዓተ-ነጥብ ምንነትና ጠቀሜታ በግልፅ ውይይት ያድርጉ፤
- ✓ ተማሪዎችን በጥንድ ያስቀምጧቸውና የሚከተለውን ፅሁፍ በሰሌዳ ላይ ይፃፉላቸው፡፡

መምህሩ ወደክፍል ገቡ፡፡ “ተማሪዎች እንደምን አደራችሁ?” በማለት ሰላምታ ሰጡ፡፡ ከዚያም ተማሪዎቹን እየዞሩ መመልከት ጀመሩ፡፡ ሁሉም ተማሪዎች ትኩረታቸውን ወደመምህሩ አደረጉ፡፡ የመምህሩ አተያይ ተማሪዎችን አስደነቃቸው፡፡ መምህሩም “አስቴር ለምን የደንብ ልብስሽን አለበስሽም?” በማለት ጠየቋት፡፡

- ✓ በሰሌዳ ላይ የፃፉትን ጽሁፍ (አራት ነጥብና የጥያቄ ምልክትን ብቻ) ከጽሁፉ ውስጥ በማስወገድ ተማሪዎች ጽሁፍ እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ ተማሪዎቹ አራት ነጥብና ጥያቄ ምልክት የሌለበትን ጽሑፍ ሲያነቡ በንበታችሁ ላይ ምን ምን ለውጥ እንዳዩ በቡድን እንዲወያዩ ያድርጓቸው፡፡ ከዚያም አንድ ፅሁፍ ከነስርዓተ-ነጥብና ከስርዓተ-ነጥቡ ውጪ ሲነበብ ያለውን ልዩነት ይጠይቋቸው፡፡
- ✓ ስርዓተ-ነጥቦች በንበት ሥርዓታችን ላይ ያላቸውን ሚና በማስመልከት በቂ ማብራሪያ ይስጧቸው፡፡
- ✓ በተማሪ መጽሐፍ ትዕዛዝ ፪ ያለውን ተግባር ከማሰራትዎ በፊት የህይወት ታሪክ ማለት ስለራስ ማንነት የሚገልፅ፤ ራስን የማስተዋወቂያ መንገድ፤ እንደሆነ ለተማሪዎቹ ምሳሌ እየጠቀሱ አጭር ገለፃ ያድርጉላቸው፡፡
- ✓ በመጨረሻም አራት ነጥብን በመጠቀም የህይወት ታሪካቸውን የሚገልፁ ዓረፍተነገሮች እንዲፅፉ ያበረታቷቸው፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ልብስና መስሪያዎቹ የሚለውን ምንባብ ተማሪዎቹ እንዲያዳምጡ ተደርገዋል፡፡ ሞክሼና ውስብስብ ቃላትን እንዲለዩና በእነሱም ቃላትን እንዲመሰርቱ፤ የፊደላትን ቦታ በመቀያየር ሌሎች ቃላትን እንዲያዋቅሩ ተደርጓል፡፡ “የበዓል ልብስ” የሚለውን ምንባብ እንዲያነቡ፤ ለቃላት ተመሳሳይ ፍቺ እንዲሰጡ፤ በተጨማሪም ስለሥርዓተ ነጥብ ምንነትና አጠቃቀም እንዲረዱ ተደርጓል፡፡

ከላይ በተጠቀሱት ተግባራት ተማሪዎች በዋናነት የማዳመጥ፣ የመናገር፣ የማንበብና የመጻፍ ክህሎታቸው እንዲዳብር ይፈለጋል፡፡ ይህንንም ለመመዘን በተማሪው መጽሐፍ የማጠቃለያ መልመጃዎች ቀርበዋል፡፡ እነዚህን ትግበራዎች ተማሪዎች እንዲተገብሩ በማድረግ የተማሪዎችን ክህሎት ይፈትሹ፡፡ ወደኋላ የቀሩ ተማሪዎች ካሉ በተለያዩ ተግባራት እንዲያዳብሩ እገዛ ያድርጉላቸው፡፡

አማርኛ
፪ኛ ክፍል

# ምዕራፍ ሁለት
# ወቅቶች

18
ክፍለ ጊዜ

## የምዕራፉ አላማዎች

ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ መጠናቀቅ በኋላ፡-

- ፅሁፍን በማዳመጥ የተለየውን ሐሳብ ይፅፋሉ።
- የምንባቡን ይዘት በቃላቸው ይናገራሉ።
- ከ"ወቅቶች" ጋር ለተገናኙ ቃላት ፍቺ ይሰጣሉ።
- ድምፆችን ያጣምራሉ፤ይነጥላሉ።
- ባለ አራት ፊደል ተዘውታሪ ቃላትን ይፅፋሉ።
- አራት ነጥብን ይጠቀማሉ።

## የምዕራፉ ይዘቶች

- ማዳመጥና መናገር
- የንግግር ድምፅ ግንዛቤ
- የትምዕርተ ድምፅ ግንዛቤ
- የቃላት ጥናት
- ማንበብ
- ፅህፈት
- ድምፀት

## 👂 ማዳመጥ

**መምህር፡-**

- ✓ የዕለቱን የትምህርት ዓላማ ያስተዋውቁ፡፡
- ✓ በሚያስተምሩበት ጊዜ በመማሪያ ክፍሉ አካባቢ ያለውን ሁኔታ ተመልክተው ምን ዓይነት ወቅት እንደሆነ ይጠይቋቸው፡፡
- ✓ ስዕሎችን እንዲገምቱ የመነሻ ሐሳብ ይስጧቸው፡፡
- ✓ ተማሪዎች የሚገምቷቸውን አንዳንድ ሐሳቦች ለናሙና ያህል በሰሌዳው ላይ ይፃፉላቸው፡፡
- ✓ እንደሁኔታው የአካቶ ትምህርትን ይተግብሩ፡፡
- ✓ የቅድመ ማዳመጥ ተግባራቱን ከ3-5 ደቂቃ ባለ ጊዜ ውስጥ ያሰሯቸው፡፡
- ✓ እንደተማሪዎቹ ሁኔታ ምንባቡን በተመጠነ ድምፅና ፍጥነት ያንብቡላቸው፡፡
- ✓ በንባብ ጊዜ ላይ ያለውን ጥያቄ ለተማሪዎች ያቅርቡላቸው፡፡

## ኢትዮጵያና ወቅቶቿ

በኢትዮጵያ አራት ወቅቶች አሉ፡፡ እነሱም፡- ክረምት፣መኸር (መፀው)፣ በጋ (ሐጋይ) እና በልግ (ፀደይ) ናቸው፡፡ ክረምት የሚይዘው ሰኔ፣ ሐምሌ፣ ነሐሴና ጳጉሜ ወሮችን ነው፡፡ መኸር (መፀው) መስከረም፣ ጥቅምትና ህዳር ወሮችን ያካትታል፡፡

| ተማሪዎች በጋ እና በልግ ወቅቶች ምን ምን ወራትን የሚይዙ ይመስላችኋል? |
|---|

በጋ ታህሳስ፣ ጥር እና የካቲትን የሚይዝ ሲሆን በልግ ደግሞ መጋቢትን፣ ሚያዚያንና ግንቦትን ያጠቃልላል፡፡

### አዳምጦ መናገር

**መምህር፡-**

- ✓ ተማሪዎች የምንባቡን አንኳር ነጥብ ተራ በተራ እንዲናገሩ ያድርጉ።
- ✓ የሰጡትን ምላሽ መሰረት በማድረግ ግብረ መልስ ይስጧቸው።
- ✓ በተማሪው መጽሐፍ ላይ የተሰጡትን የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች በማሰራት የተማሪዎችን የአዳምጦ መረዳት ሁኔታ ይፈትሹ፤ ማስተካከያም ይስጧቸው።
- ✓ ምንባቡን መሰረት አድርገው በመማሪያ መፅሃፉ ላይ የቀረቡትን የእውነት/ሐሰት ጥያቄዎች ያሰሯቸው።እርማትም ይስጧቸው።

**የተግባሩ መልስ**

1. ሐሰት
2. እውነት
3. ሐሰት

### 🗝 ቃላት

**መምህር፡-**

- ✓ የማዛመድ ተግባሩን ከማሰራትዎ በፊት ምሳሌ ይስጧቸው።
- ✓ በመማሪያ መጽሐፉ ላይ ያለውን ተግባር (ወቅቶችን ከወራት ጋር ማዛመድ) እንዲያዛምዱ ያድርጉ፤ ማስተካከያም ይስጧቸው።
- ✓ በክፍል ውስጥ ዓይነ ስውር ተማሪዎች ካሉ በቃል ያንብቡላቸውና ምላሽ ይቀበሏቸው፤ ማስተካከያም ይስጧቸው፡
- ✓ ቃላት ሲያስሩ የልዩ ፍላጎት ተማሪዎችንም ታሳቢ ያድርጉ።

**የተግባሩ መልስ**

1. ሀ
2. ሐ
3. ለ

- ✓ ተማሪዎች ቻርቱ ውስጥ ባለ አራት ፊደል ወራትን እንዲፅፉ ያድርጓቸው፤ እርማትም ይስጧቸው።

| | |
|---|---|
| ጥቅምት | መጋቢት |
| ታህሳስ | ሚያዚያ |
| የካቲት | ግንቦት |

- ✓ በመማሪያ መፅሃፉ በቻርት መልኩ የቀረበውን የሳምንቱ ቀናትን ተግባር ያሰሯቸው፤ ምላሽ ይስጧቸው።

## 🕮 ንባብ

*መምህር፡-*

- ✓ ከምንባቡ በፊት የቀረቡትን የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች ከ3-5 ባለው ደቂቃ ውስጥ ያሰሯቸው፤ተማሪዎች የሚሰጧቸውን መልሶችና ግምቶች የተወሰኑትን በሰሌዳው ላይ ይፃፉላቸው፡፡
- ✓ ተማሪዎች የ"አበባ አየሁሽ" ጭፈራውን ሌሎች ተማሪዎችን በማይረብሽ መልኩ ከክፍል ውጪ እንዲተገብሩት ያበረታቷቸው፡፡
- ✓ አተገባበሩም፡- አንዲት መሪ (አውጪ) እና ሶስት ተቀባይ ተማሪዎች ሆነው በክፍል ጓደኞቻቸው ፊት ለፊት እንዲወጡ ያድርጉ፤ በመቀጠል ጭፈራውን እየተቀባበሉ እንዲተገብሩት ያድርጉ፡፡
- ✓ እንደትምህርት ቤቱና መማሪያ ክፍሉ ተጨባጭ ሁኔታ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ጭፈራውን እንዲተገብሩት ማድረግም ይችላሉ፡፡
- ✓ ከላይ ከተቀመጠው አተገባበር ባሻገር እርስዎ የራስዎን የማስተማር ስነ-ዘዴ መተግበር ይችላሉ፡፡
- ✓ በመቀጠል የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎች ባማከለ መልኩ ያሰሯቸው፡፡
- ✓ ተማሪዎች የሚያውቋቸውን ሌሎች የበዓላት መዝሙሮች፣ ጭፈራዎች፣ ጨዋታዎች ወዘተ. እቤታቸው ተለማምደው መጥተው ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያቀርቡ በቤት ስራ መልኩ ይስጧቸው፡፡

## ☞ መነጠልና ማጣመር

**መምህር፡-**

✓ መነጠልና ማጣመርን በተመለከተ ምንነቱንና ጠቀሜታውን ለተማሪዎች ያስረዷቸው፡፡

መነጠልና ማጣመር

ይህ ድምፆችንና ቃላትን በማንበብና ወደ ተለያዩ ክፍሎች በመነጠል ወይም በማጣመር ላይ ስለሚያተኩር፣ ልጆቹ ድምፃችንና ቃላትን እንዲያነቡና በተገቢ የፊደል አሰዳደር ስርዓት እንዲፅፉ ያደርጓቸዋል፡፡

ማጣመር፡- ሲባል ድምጾቹን/ቃላቱ የተመሰረቱባቸውን ፊደሎች ወይም የቃላቱን የተነጣጠሉ አሃዶች ለየብቻ ያነባሉ፤ መልሰውም አንድ ላይ ይጠሯቸዋል፡፡

መነጠል፡- ደግሞ ቃላቱን ያነባሉ፤ ቀጥለውም ወደፊደላት ወይም ወደ አነስተኛ አሐዶች ይነጥላሉ፡፡

✓ ከላይ ያለውን ፅንሰ ሃሳብ በቃል ካስረዷቸው በኋላ ምሳሌ ይስጧቸው፤ በመቀጠል ማስተካከያ ይስጧቸው፡፡

✓ ተጨማሪ የክፍል ስራ ይስጧቸው፡፡

በተማሪው መጽሐፍ ትዕዛዝ ፪ ላይ ያሉትን ቃላትን ከአብዥ ቅጥያ “ዎች” ጋር በማጣመር ተማሪዎቹ ተግባሩን እንዲሰሩ አጭር ገለጻና ምሳሌ በመስጠት እንዲሰሩ ያግዟቸው፤ እርማትም ይስጧቸው፡፡

✓ በመቀጠል በተማሪው መጽሐፍ ትዕዛዝ ፫ ላይ በሰንጠረዡ ውስጥ የቀረቡትን ፊደላት በማገጣጠም ቃላትን የመመስረት ተግባርን በጥንድ በመሆን እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡

የተግባሩ መልስ፡- -ቀጠረ፣ ረጠበ፣ በረት፣ ተመለከተ…

✓ ቃላት በሚለው ርዕስ ስር ያለውን ተግባር በምሳሌው መሰረት ያሰሯቸው፡፡

## አቀላጥፎ ማንበብ

**መምህር፡-**

- ✓ "አካባቢያችንን እንጠብቅ" በሚል ርዕስ ስር የቀረበውን ምንባብ ተማሪዎች እየደጋገሙ እንዲያነቡት ያግዟቸው፡፡
- ✓ አልፎ አልፎ አንዳንድ ተማሪዎች ቆመው ድምፅ በማሰማት ለክፍል
- ✓ ጓደኞቻቸው እንዲያነቡ አድርጓቸው፡፡የልዩ ፍላጎት ተማሪዎችን ያማከለ አቀላጥፎ የማንበብ ተግባር ያከናውኑ፡፡
- ✓ የተማሪዎችን የአቀላጥፎ ማንበብ ሁኔታ እየገመገሙ የተሻለ የማንበብ ለውጥ ያመጡ ተማሪዎችን ያበረታቷቸው፡፡

## ✍ ጽሕፈት

**መምህር፡-**

- ✓ የሚከተሉትን ቃላት እያነበቡላቸው በደብተራቸው እንዲፅፉ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ካሉ በወረቀት ፅፈው ይስጧቸው፡፡

**ቃላት**

- ተዘጋ
- ተማረ
- አወጣ
- ጠላት
- ኩራት

- ✓ ተማሪዎች ከላይ ያሉትን ቃላት ካፃፏቸው በኋላ የመጀመሪያ ፊደላቸውን እያጠፉ እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡
- ✓ በመቀጠል ባጠፏቸው ፊደላት ምትክ ሌላ ፊደል ተክተው ቃል እንዲመሰርቱ ያድርጉ፡፡

## መልስ

1. ተዘጋ = ዘጋ = አዘጋ (ሌላም ፊደል ሊተኩ ይችላሉ።)
2. ተማረ = ማረ =አማረ (ሌላም ፊደል ሊተኩ ይችላሉ።)
3. አወጣ = ወጣ =ተወጣ (ኃላፊነቱን ተወጣ)
4. ጠላት = ላት = አላት (ሌላም ፊደል ሊተኩ ይችላሉ።)
5. ኩራት = ራት =አራት (ሌላም ፊደል ሊተኩ ይችላሉ።)

- ✓ ተማሪዎች በቡድን በመሆን መጽሐፉ ላይ የቀረቡትን ቃላት በተለያዩ ዓ.ነገሮች ውስጥ በማስገባት የተለያዩ ፍቺ እንዲኖራቸው ያድርጉ።
- ✓ በየቡድኑ እየተዘዋወሩ ያግዟቸው፤ይምሯቸው።

## የተግባሩ መልስ

1. ሄደ፡- ሰዓቱ ሄደ።

   ልጁ ወደ ትምህርት ቤት ሔደ።
2. ዓይኖች፡- የባትሪው ዓይኖች ተቃጠሉ።

   የልጁ ዓይኖች ትላልቅ ናቸው።
3. ውኃ፡- ከምግብ በኋላ ውኃ እጠጣለሁ።

   ለበዓል የተዘጋጀው መውደድ ውኃ ነው።
4. ጠላ፡- የአስቴር ጠላ ይጥማል።

   ከማል በቅቤ መብላት ጠላ።
5. ተሾመ፡- ተሾመ ጎበዝ ተማሪ ነው።

   ኢብራሒም የክፍል አለቃ ሆኖ ተሾመ።

- ✓ ለሥርዓተ ነጥብ ማስተማሪያነት የተዘጋጀውን ምንባብ በጥቁር ሰሌዳው ላይ ይፃፉላቸው። ተማሪዎች ተራ በተራ እየተነሱ በአንቀፁ ውስጥ አራት ነጥብ እንዲያስገቡ ያግዟቸው።

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ “የኢትዮጵያ ወቅቶች” የሚለውን ምንባብ ተማሪዎቹ እንዲያዳምጡ ተደርገዋል፡፡ ባለአራት ሆሄ ቃላትን እንዲለዩ፣ የሳምንቱን ቀናት እንዲናገሩና እንዲፅፉ ፤ የፊደላትን ቦታ በመቀያየር ሌሎች ቃላትን እንዲያዋቅሩ ተደርጓል፡፡ “አካባቢያችንን እንጠብቅ” የሚለውን ምንባብ እንዲያነቡ፤ በተጨማሪም በአራት ነጥብ ፅሁፍን እንዲያሟሉ ተደርጓል፡፡

ከላይ በተጠቀሱት ተግባራት ተማሪዎች በዋናነት የማዳመጥ፣ የመናገር፣ የማንበብና የመጻፍ ክህሎታቸው እንዲዳብር ይፈለጋል፡፡ ይህንንም ለመመዘን በተማሪው መጽሐፍ ከገጽ 15-17 የማጠቃለያ መልመጃዎች ቀርበዋል፡፡ እነዚህን ትግበራዎች ተማሪዎች እንዲተገብሩ በማድረግ የተማሪዎችን ክህሎት ይፈትሹ፡፡ ወደኋላ የቀሩ ተማሪዎች ካሉ በተለያዩ ተግባራት እንዲያዳብሩ እገዛ ያድርጉላቸው፡፡

አማርኛ
፩ኛ ክፍል

# ምዕራፍ ሶስት
# ታሪኮች

18
ክፍለ ጊዜ

**የምዕራፉ አላማዎች**

ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ መጠናቀቅ በኋላ፡-

- ያዳመጡትን ምንባብ አጠቃላይ ሐሳብ ለይተው ቃላዊ ዘገባ ያቀርባሉ፡፡
- ካነበቡት ፅሑፍ ውስጥ አጠቃላይ ሐሳቡን ይፅፋሉ፡፡
- በዓረፍተ ነገር ውስጥ አራት ነጥብን ይጠቀማሉ፡፡
- ባለ አራት ፊደል ተዘውታሪ ቃላትን ይፅፋሉ፡፡
- ቃለ አጋኖ እና የጥያቄ ምልክትን ይጠቀማሉ፡፡

**የምዕራፉ ይዘቶች**

- ማዳመጥና መናገር
- የንግግር ድምፅ ግንዛቤ
- የትምዕርተ ድምፅ ግንዛቤ
- የቃላት ጥናት
- ማፍለቅና መረዳት
- ማንበብ
- ፅህፈት
- ድምፀት

## ማዳመጥ

### ታሪኮች

**መምህር፡-**

- ✓ የዕለቱን የትምህርት ዓላማ ያስተዋውቁ፡፡
- ✓ ስዕሎችን እንዲገምቱ የመነሻ ሐሳብ ይስጧቸው፡፡
- ✓ የተማሪዎችን የማንበብ ፍላጎት ለማነሳሳትና ዝግጁ ለማድረግ ይረዳ ዘንድ ከምንባቡ ጋር ዝምድና ስላለው ተረት ምንነት ይጠይቋቸው፤ አንዳንድ መልሶቻቸውን በሰሌዳው ላይ ይፃፉላቸው፡፡
- ✓ ተማሪዎች የሚገምቷቸውን አንዳንድ ሐሳቦች ለናሙና ያህል በሰሌዳ ላይ ይፃፉላቸው፡፡
- ✓ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ካሉ ጽሑፉን በወረቀት በማዘጋጀት ያቅርቡላቸው፡፡
- ✓ የቅድመ ማዳመጥ ተግባራቱን ከ3-7 ደቂቃ ባለ ጊዜ ውስጥ ያሰሯቸው፡፡
- ✓ እንደተማሪዎቹ ሁኔታ ምንባቡን በተመጠነ ድምፅና ፍጥነት ያንብቡላቸው፡፡

# አውራ ዶሮና ቀበሮ

በጫካ ውስጥ የሚኖር አንድ ቀበሮ አንድ ቀን በጣም ርቦት ከመንደር ውስጥ ገብቶ ሲዞር አውራ ዶሮ በማየቱ በጣም ደስ አለው፡፡ ቀበሮው አውራ ዶሮውን ያየው “ኩኩሉ…” እያለ ሲጮህ ነበር፡፡ ቀበሮውም ወደዶሮው ተጠጋና “ጥሩ ድምጽ ስላለህ እባክህን ኩኩሉ በልልኝ፡፡” አለው፡፡ አውራ ዶሮውም “እሺ!” አለውና እንደገና “ኩኩሉ…” ለማለት ዐይኑን ጨፍኖ ጎንበስ አለ፡፡ አውራ ዶሮው ባጎነበሰበት ቅጽበት ቀበሮው ቶሎ ዘሎ አውራ ዶሮውን ያዘና ወደጫካ ሮጠ፡፡ እረኞች ደግሞ የቀበሮውን ድርጊት በርቀት ሆነው ስለተመለከቱ እየተጣደፉ ይከተሉት ጀመር፡፡

…ተማሪዎች ዶሮው ከተኩላው የሚያመልጥ ይመስላችኋል?…

ቀበሮው ፍጥነቱን በመጨመር አውራ ዶሮውን በአፉ ይዞ ወደፊት ፈረጠጠ፡፡ እረኞቹም በተመሳሳይ ፍጥነታቸውን በመጨመር ተከተሉት፡፡ በዚህ ጊዜ አውራ ዶሮው ቀበሮውን “የሚከተሉህ ሰዎች እንዳይገድሉህ የያዝኩት ዶሮ የናንተ አይደለም በላቸው፡፡” አለው፡፡ ቀበሮውም ዶሮው የነገረውን ለእረኞቹ ለመናገር አፉን ሲከፍት ዶሮው ወደእረኞቹ ሮጠ፡፡ እረኞቹም ዶሮውን ይዘው ወደ ቤታቸው ተመለሱ፡፡ ዶሮው በቀበሮው ብልሀት ቢታለልም የቀበሮውን ብልሀት ለራሱም ስለተጠቀመበት ከመበላት ዳነ፡፡

## አዳምጦ መናገር

**መምህር፡-**

- ✓ ተማሪዎች የምንባቡን አንኳር ነጥብ ተራ በተራ እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡ የሰጡትን ምላሽ መሰረት በማድረግ ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡
- ✓ በተማሪው መፅሃፍ ላይ የተሰጡትን የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች በማሰራት የተማሪዎችን የአዳምጦ መረዳት ሁኔታ ይፈትሹ፤ ማስተካከያም ይስጧቸው፡፡
- ✓ ምንባቡን መሰረት አድርገው በመማሪያ መፅሃፉ ላይ የቀረቡትን በቃል የሚመለሱ ጥያቄዎች ያሰሩዋቸው፤ እርማትም ይስጧቸው፡፡

**መምህር፡-**

- ✓ የጥያቄዎቹ መልሶች እንደተማሪዎቹ የግናዛቤ ሁኔታ ስለሚለያይ እርስዎ የጋራ የሆነ ግንዛቤ እንዲይዙ ምላሽ ይስጧቸው፡፡
- ✓ ተማሪዎቹ ያዳመጡትን ተረት በማስታወስ ተራ በተራ እየተነሱ በቃል እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡
- ✓ ተማሪዎች የሚያውቋቸውን ተረቶች እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡
- ✓ በተረቱ ውስጥ ሊተላለፍ የተፈለገውን አንኳር ነጥብ በአጭሩ ይግለፁላቸው፡፡

## ቃላት

መምህር፡-

- ✓ ተማሪዎች የማዛመዱን ጥያቄ ከመስራታቸው በፊት ከምንባቡ ውስጥ ሁለት ቃላትን በማውጣት እንዴት በምንባቡ መሰረት ፍቺ እንደሚሰጥ ያሳዩዋቸው፡፡
- ✓ ቃላት በሚለው ተግባር ስር ያለውን ማዛመድ በምንባቡ መሰረት ለቃላት ፍቺ እንዲሰጡ ያድርጉ፡፡

መልስ

1. ሠ
2. ሐ
3. ለ
4. መ
5. ሀ

### መነጠልና ማጣመር

መምህር፡-

- ✓ ተነጣጥለው የተቀመጡትን ቃላት በምሳሌው መሰረት በማጣመር እንዲሰሩ ያግዟቸው፡፡
- ✓ ተጨማሪ የተነጣጠሉ ቃላትን ለተማሪዎቹ በመስጠት በቡድን ሆነው እንዲያጣምሯቸው በማድረግ ተግባሩን በአግባቡ እንዲለማመዱ ያድርጉ፡፡

የተግባሩ መልስ

1. ጀመረች
2. አፋን
3. ቀበሮው
4. ወደጫካ
5. ለመናገር

- ✓ በትዕዛዝ ፪ ላይ ተጣምረው የቀረቡትን ቃላት ከብዙ ቁጥር ወደ ነጠላ ቁጥር ቀይረው እየነጣጠሉ እንዲያስቀምጡ ያድርጉ።
- ✓ በዚህ መልኩ እርማት ይስጧቸው፡-

የተግባሩ መልስ

1. ቅርስ-ኦች= ቅርስ
2. መጽሃፍ-ኦች= መጽሃፍ
3. ገበሬ-ዎች= ገበሬ
4. በሬ-ዎች= በሬ
5. ጫማ-ዎች= ጫማ

በማለት ማስተካከያ ይስጧቸው።

መምህር፡-

- ✓ የዕለቱን ትምህርት ያስተዋውቁ።
- ✓ ከምንባቡ በፊት የቀረቡትን የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች ከ3-7 ባለው ደቂቃ ውስጥ ያሰሯቸው፤ ተማሪዎች የሚሰጧቸውን መልሶችና ግምቶች የተወሰኑትን በሰሌዳ ላይ ይፃፉላቸው።
- ✓ ተማሪዎች በተለያዩ ጊዜያት የጎበኟቸውን ቅርሶች መገኛ ቦታቸውን ጭምር ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲናገሩ ያድርጉ።
- ✓ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረበውን ምንባብ ሁሉም ተማሪዎች በግላቸው እንዲያነቡ ያድርጉ፤ በመቀጠል የምንባቡን አንቀፅ ለተማሪዎቹ በማከፋፈል ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያነቡ ያድርጓቸው።
- ✓ ተማሪዎች አንብበው ከጨረሱ በኋላ ያበረታቷቸው።

መምህር፡-

- ✓ ለቃላት ፍቺ የምንሰጥባቸው መንገዶች በርካታ ናቸው። ከእነዚህም መካከል የቃላት ተቃራኒ ፍቺ አንዱ ነው። የተወሰኑ ቃላትን በምሳሌነት በመስጠት እንዴት ተቃራኒ ፍቺ እንደሚፈልጉ ያሳዩዋቸው።
- ✓ በመቀጠል የቀረበውን ተግባር በግል እንዲሰሩ ያድርጉ፤ እርማት ይስጧቸው።

መልስ፡- 1. ጥቂት

2. ጥላቻ

3. ጦርነት

4. ገጠር

5. ዘንድሮ

## አቀላጥፎ ማንበብ

መምህር፦

- በተማሪው መፅሀፍ ላይ ያለውን "እናስተዋውቃችሁ" የሚለውን ንባብ ተማሪዎች አቀላጥፈው እንዲያነቡ ያግዟቸው።
- በመቀጠል የንባብ መከታተያ ሰንጠረዥ በማዘጋጀት ተማሪዎች ሲያነቡ ደቂቃ በመያዝ የንባብ ችሎታቸውን እየገመገሙ ማበረታቻና አስተያየት ይሰጣቸው።
- የተማሪዎች የአቀላጥፎ ማንበብ ሁኔታ እየገመገሙ የተሻለ የማንበብ ለውጥ ያመጡ ተማሪዎችን ያበረታቷቸው።

. ስለ ባለ አራት ፊደል ቃላት አጭር ገለፃ ያድርጉላቸው።

| |
|---|
| ባለ አራት ፊደል ቃል ማለት  በአራት ፊደላት የተዋቀረ ቃል ነው፤ ምሳሌ ይስጧቸው። |

- በመቀጠል በተማሪ መፅሀፍ ትዕዛዝ ፩ ላይ"እናስተዋውቃችሁ" በሚል ርዕስ ካነበቡት ምንባብ ላይ ባለ አራት ፊደል ቃላትን ለይተው እንዲፅፉ ያድርጉ።

. በትዕዛዝ ፪ ላይ ለቀረቡ ቃላት ተመሣሣያቸውን እንዲፈልጉ ያድርጓቸው።

. በተማሪ መማሪያ መፅሀፍ በትዕዛዝ ፫ ላይ ተቀረቡትን ፊደላት በማጣመር የተለያዩ ቃላት እንዲመሰርቱ ያድርጓቸው።

. በመጨረሻ ተማሪዎች ለሠሯቸው ተግባራት እርማት ይስጧቸው።

- ✓ ተግባሩን ሲሰሩ ዓይነ ስውር ተማሪዎች ካሉ ከልዩ ፍላጎት ባለሙያዎች ጋር በመነጋገር የሚያቀርቡትን ይዘት እነሱን ባማከለ መልኩ ይቅረጹ፤ ሌሎች ልዩ ፍላጎት የሚስፈልጋቸው ተማሪዎች ካሉ እንደሁኔታው አካተው ያሰሯቸው፡፡

የተግባሩ መልስ ትዕዛዝ ፩

1. ምህረት
2. ትውልድ
3. ግንቦት
4. ታህሳስ
5. መምህር

(ሌሎችም ቃላት ሊኖሩ ይችላሉ፤ ስለዚህ ከምንባቡ በማመሣከር መልሳቸውን ይቀበሏቸው

የተግበሩ መልስ ትዕዛዝ ፫

1. ተረት
2. ቅሪት
3. ቅርስ
4. ተስፋ
5. በረታ

- ✓ ተማሪዎች ትዕዛዝ ፫. ላይ የመሰረቷቸውን ቃላት ተጠቅመው ዓረፍተ ነገር እንዲሰሩባቸው ያድርጉ፡፡
- ✓ ከትዕዛዝ ፫ ተግባር ጋር ተዛማጅነት ያለው የቤት ስራ ይስጧቸው፡፡
- ✓ ተማሪዎቹ ከሠዎች የሰሟቸውን ተረቶች (ከመፅሀፍት ከነበቧቸው ታሪኮች መካከል አንዱን በመምረጥ ሥርዓቱን ጠብቀው እንዲፅፉ ያበረታቷቸው፡፡ በሚፅፉበት ጊዜ አራት ነጥብን፣የጥያቄ ምልክትንና ቃለ አጋኖ በመጠቀም በዐረፍተ ነገሮች ውስጥ እንዲጠቀሙ ያበረታቷቸው፡፡

መምህር፡-

- ✓ የምዕራፉን አንኳር ነጥቦች በአጭሩ ይከልሱላቸው፡፡
- ✓ ተማሪዎች 5 አባላት ያሉት ቡድን እንዲመሰርቱ ያድርጉ፤ ከዚያም የማጠቃለያ መልመጃዎችን ቡድን ሆነው እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡ የሰሯቸውን የሥርዓተ ነጥብ ጽሑፎች በሚገባ በመገምገም ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡
- ✓ የማጠቃለያ መልመጃውን ያሰሯቸው፤ በሚከተለው መልኩ እርማትም ይስጧቸው፡፡

መልስ፡-

| ባለ 2 ፊደል | ባለ 3 ፊደል | ባለ 4 ፊደል |
|---|---|---|
| ሰራ | አሰራ | ወንበር |
| ፈራ | ሰራች | አበደረ |
| ደራ | በለጠ | አጣራች |
| ጣረ | ባለጌ | ወሰደች |
| ሰጠ | ጠለፈ | ተራበች |

- ✓ ከላይ ከቀረቡት ቃላት በተጨማሪ ሌሎችን ቃላት መመስረት ይችላሉ፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ “አውራ ዶሮና ቀበሮ” የሚለውን ምንባብ ተማሪዎቹ እንዲያዳምጡ ተደርገዋል፡፡ ባለአራት ሆሄ ቃላትን እንዲለዩ፣ የቃላት ተቃራኒ ፍቺ እንዲፈልጉ፤ በፊደላት ቃላትን እንዲያዋቅሩ፤ ቃላትን ከብዙ ቁጥር ወደነጠላ ቁጥር እንዲለዩ ተደርጓል፡፡ “አዲስ አበባ” የሚለውን ምንባብ እንዲያነቡ፤ በተጨማሪም በአራት ነጥብ፣ በጥያቄ ምልክትና በቃለአጋኖ ዓረፍተ ነገር እንዲጽፉና በፅሁፍ ውስጥ እንዲያሟሉ ተደርጓል፡፡ ከላይ በተጠቀሱት ተግባራት ተማሪዎች በዋናነት የማዳመጥ፣ የመናገር፣ የማንበብና የመጻፍ ክህሎታቸው እንዲዳብር ይፈለጋል፡፡ ይህንንም ለመመዘን በተማሪዎች መጽሐፍ የማጠቃለያ ተግባራት ቀርበዋል፡፡

# አማርኛ
## ፩ኛ ክፍል

# ምዕራፍ አራት
# የአትክልት ቦታ

18
ክፍለ ጊዜ

**የምዕራፉ አላማዎች**
**ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ መጠናቀቅ በኋላ፡-**

- ከዳመጡት ምንባብ ለወጡ ቃላት ፍቺ ይሰጣሉ፡፡
- ከምንባቡ ውስጥ ልዩ የሆነውን ሀሳብ ያወጣሉ፡፡
- ቃለአጋኖንና የጥያቄ ምልክትን ይለያሉ፡፡
- በነጠላ ዓረፍተ ነገሮች መጨረሻ ላይ አራት ነጥብ ያስገባሉ፡፡

**የምዕራፉ ይዘቶች**

- ማዳመጥና መናገር
- የንግግር ድምፅ ግንዛቤ
- የትምዕርተ ድምፅ ግንዛቤ
- የቃላት ጥናት
- ማፍለቅና መረዳት
- ማንበብ
- ፅህፈት

## ((( ማዳመጥ

# የማርታ ማስታወሻ

**መምህር፡-**

- የዕለቱን የትምህርት ዓላማ ያስተዋውቁ፡፡ ቅድመ ማዳመጥ ተግባርን ከ5-7 ደቂቃ በመጠቀም ያሰሯቸው፡፡
- ተማሪዎች በሚኖሩባቸው አካባቢዎች ያሉ የአትክልት ቦታዎችን ወይም መናፈሻዎችን እንዲዘረዝሩ ያድርጉ፡፡
- የአትክልት ቦታዎችና የመናፈሻዎችን ጥቅም በተመለከተ ተማሪዎች ሀሳብ እንዲሰጡ ያበረታቷቸው፡፡
- መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ካሉ ጽሑፉን በወረቀት በማዘጋጀት ያቅርቡላቸው፡፡
- ለተማሪዎች ስለምን እንደሚያነቡላቸው ይግለጹላቸው፡፡
- እንደተማሪዎቹ ሁኔታ ምንባቡን በተመጠነ ድምፅና ፍጥነት ያንብቡላቸው፡፡
- በንባብ ጊዜ ላይ ያለውን ጥያቄ ለተማሪዎች ያቅርቡላቸው፡፡ ምላሻቸውን ይቀበሏቸው፡፡

## የማርታ ማስታወሻ

ወሩ የካቲት ነው። የአንደኛው መንፈቀ ዓመት ትምህርት ተጠናቆ የሁለተኛው መንፈቀ ዓመት የተጀመረበት እለት ነው። ረፍት ሲደወል ከሚላትና ማርታ የአንደኛው መንፈቀ ዓመት የረፍት ጊዜያቸውን እንዴት እንዳሳለፉ ማውራት ጀመሩ። ማርታ ለከሚላት "ብታይ ከሚላት ጥሩ ውጤት በማምጣቴ እናቴ ልብስ፣ ጫማ፣ የተረት መጽሐፍ ገዝታ ሸለመችኝ። አባቴ ደግሞ በጣም የሚያማምሩ ልዩ ልዩ አበቦችና ዛፎች ያሉበት ልዩ ስፍራ ወሰደኝ። መዝናኛው ቦታ እንደገባን አንድ ሰውዬ ስለቦታው ሊነግረን ወደእኛ ቀረብ አለ። እኔም ማስታወሻ መያዝ ጀመርኩ።"

| ...ሰውየው ሊናገረው ስለሚችለው ሀሳብ ገምቱ።... |
|---|

ሰውዬው መናገር ጀመረ። "ቦታው ሐምሌ 19 መናፈሻ ይባላል። የተመሰረተው በ1975 ዓ.ም. ነው። በ20 ሄክታር ላይ አርፏል። የቀበና ወንዝና የአሜሪካ ኢምባሲ ያዋስኑታል። የተለያዩ ሀገር በቀልና የውጪ ዛፎች፣ አበባዎች፣ ሳርና መሰል እጽዋት በውስጡ ይዟል። ሰርግ፣ ልደትና ልዩ ልዩ ዝግጅቶች ይዘጋጁበታል። 'አረንጓዴው ገነት' እየተባለም ይጠራል። እቴጌ መነንም ሱባዔ የሚገቡበት ልዩ ቦታ ነበር።" በማለት ማብራሪያ ሰጠን። ብታይው ከሚላት ቦታው እንዴት እንደሚያምር!" በማለት ነገረቻት። ከሚላትም በተነገራት ነገር በጣም በመጓጓት "ይህ መናፈሻ የሚገኘው የት ነው?" በማለት ጠየቀቻት። ማርታም "ሐምሌ19 መናፈሻ የሚገኘው ወደ ሽሮ ሜዳ በሚወስደው መንገድ ስንጓዝ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ስድስት ኪሎ ግቢ በላይ ከስብሰባ ማዕከል ጎን በስተቀኝ በኩል አጠፍ ስትይ ይገኛል።" በማለት ነገረቻት። ወዲያው የእረፍት ሰዓት ተደውሎ ወደክፍል ገቡ።

(GPSMYCITY 2021)

## አዳምጦ መናገር

መምህር፡-

- ✓ ተማሪዎች የምንባቡን አንኳር ነጥብ ተራ በተራ እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡
- ✓ የሰጡትን ምላሽ መሰረት በማድረግ ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡
- ✓ በተማሪው መጽሐፍ ላይ የተሰጡትን የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች በማሰራት የተማሪዎችን የአዳምጦ መረዳት ሁኔታ ይፈትሹ፡፡
- ✓ ተማሪዎች ከሰጡት ምላሽ በመነሳት እርማትም ይስጧቸው፡፡
- ✓ በማዳመጥ ተግባሩ በተጠበቀው የብቃት ደረጃ ላይ ያልደረሱ ተማሪዎች ካሉ ክፍተቱን ለመሸፈን የተለያዩ የተቀረጹ ንግግሮችን በመርጃ መሳሪያነት በመጠቀም የማዳመጥ ተግባርን እንዲለማመዱ ያድርጉ፡፡

## ቃላት

መምህር፡-

- ✓ የማዛመድ ተግባሩን ከማሰራትዎ በፊት ምሳሌ ይስጧቸው፡፡
- ✓ በመማሪያ መጽሐፉ ላይ ያለውን ተግባር (ስዕሎችን ከመግለጫቸው ጋር) እንዲያዛምዱ ያድርጉ፤ ማስተካከያም ይስጧቸው፡፡

✓ ስዕሎችን በቃላት በመግለጽ ሲያሰሩ ሌሎች የልዩ ፍላጎት ተማሪዎች ካሉ የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ያግዟቸው፡፡

**የሰዕል ማዛመድ ተግባር መልስ**

1. ሐ
2. ሀ
3. መ
4. ሠ
5. ለ

✓ በክፍል ውስጥ ዓይነ ስውር ተማሪዎች ካሉ በቃል ስዕሉን በሚገባ ያብራሩላቸው፤ ምላሻቸውን በቃል ይቀበሏቸው፤ ማስተካከያም ይስጧቸው፡፡

☞ **መነጠልና ማጣመር**

**ተግባር ፩**

**መምህር፡-**

✓ መነጠልና ማጣመርን በተመለከት ምንነቱንና ጠቀሜታውን ለተማሪዎች ይከልሱላቸው፡፡

✓ ለተማሪዎቹ የሚከተሉትን ቃላት አንብቡላቸው፡፡

| | |
|---|---|
| ሰበሰበ | ዶማ |
| ረዘመ | ቀጠቀጠ |
| ሰላጣ | ደለበ |

✓ ተማሪዎቹ ያነበቡላቸውን ቃላት በትክክል መጻፋቸውን እየዞሩ ደብተራቸውን በማየት ያረጋግጡ፡፡

✓ የጻፏቸውን ቃላት የመጀመሪያ ፊደላት እንዲያጠፉና እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡

✓ በፃፉት ቃላት ውስጥ ያሉ ፊደላትን ቦታ እንዲያቀያይሩና ሌላ አንድ ፊደል በመጨመር ሌላ ቃል እንዲመሰርቱ ያበረቷቷቸው፡፡

✓ ለተማሪዎች አሰራሩ ግልጽ ይሆንላቸው ዘንድ በርካታ ምሳሌዎችን ቀድመው ይስጧቸው፡፡

✓ ተማሪዎች ተግባሩን ለመተግበር የሚቸገሩ ከሆነ ከተሰጡ ቃላት የመጀመሪያ ፊደሎችን ለይቶ የሚያሳይ ቻርት አዘጋጅተው ለሁሉም ተማሪዎች የሚታይ ቦታ ላይ ያስቀምጡት፡፡

## የተግባር ፩ መልስ

| የተሰጠ ቃል | ቦታ ሲቀያየሩ | ምስርት ቃል |
|---|---|---|
| ሰበሰበ = | በሰበሰ | በሰበሰች |
| ረዘመ = | መረዘ | ተመረዘ |
| ሰላጣ = | ላሰጣ | ላሰጣው |
| ዶማ = | ማዶ | የማዶ |
| ቀጠቀጠ= | ጠቀጠቀ | ጠቀጠቀው |
| ደለበ = | በደለ | የበደለ |

(የተግባር አንድ ምላሾች ከላይ የተጠቀሱት ብቻ ሳይሆኑ ሌሎች አማራጮችና ምላሾችም ሊኖሯቸው ይችላል፡፡)

## ተግባር ፬

መምህር፡-

- ✓ በተግባር ሁለት ላይ ተነጣጥለውና ተጣምረው የቀረቡትን ቃላትን ነጣጥለውና አጣምረው እንዲያነቡ ያግዟቸው፡፡
- ✓ ተማሪዎች ተግባሩን በሚገባ እንዲያከናውኑት ከተግባራቱ ውስጥ የመጀመሪያውን በምሳሌነት ያንብቡላቸው፡፡
- ✓ ተግባሩን በትክክል መሥራታቸውን ለመመዘን ተጨማሪ የቤት ስራ ይስጧቸው፡፡

## ተግባር ፫

መምህር፦

- ✓ በተግባር ሶስት በብዙ ቁጥር የቀረቡ ቃላትን ወደ ነጠላ ቁጥር እንዲቀይሩ ያግዟቸው፡፡
- ✓ ተግባሩን በሚገባ እንዲሰሩ በቂ ምሳሌዎችን ይስጧቸው፡፡
- ✓ ሁሉም ተማሪዎች ተግባሩን እንዲሰሩ እርማት ይስጧቸው፡፡
- ✓ የማጠናከሪያ ተግባርም በክፍል ሥራነት ወይም በቤት ሥራነት ይስጧቸው፡፡

## 🕮 ንባብ

መምህር፡-

- ✓ ከምንባቡ በፊት የቀረቡትን የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች ከ3-5 ባለው ደቂቃ ውስጥ ያሰሯቸው፤ ተማሪዎች የሚሰጧቸውን መልሶችና ግምቶች የተወሰኑትን በሰሌዳው ላይ ይፃፉላቸው፡፡
- ✓ ተማሪዎች "አበባማው ግቢ" የሚለውን ምንባብ በግላቸው እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡
- ✓ በንባብ ጊዜ የሚሰሩ ጥያቄዎችን ምላሽ ይሰጡ ዘንድ ያበረታቷቸው፡፡

መምህር፡-

- ✓ የንባቡ ሂደት ሲጠናቀቅም የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎች ባማከለ መልኩ በጽሁፍ ያሰሯቸው፡፡
- ✓ ተማሪዎች "አበባማው ግቢ" ከሚለው ምንባብ ምን እንደተማሩ በጋራ እንዲወያዩ፡-
    - አምስት አባላት ያሉት ቡድን ይመስርቱ፡፡
    - የቡድን አወያይ (መሪ) እዲመርጡ ያድርጉ፡፡
    - የቡድን አባላቱ ከምንባቡ የተማሩትን በተመለከተ ውይይት እንዲያደርጉ ያመቻቹ፡፡
    - የቡድናቸውን ሀሳብ በጽሑፍ እንዲያቀርቡት ያድርጉ፡፡
    - ሁሉም ቡድኖች በታዘዙት መልኩ መስራታቸውን ለማረጋገጥ ቅኝት ያድርጉ፡፡
    - ከዚያም ከቡድን አባላቱ መካከል አንድ ተማሪ በጽሁፍ ያዘጋጁትን የቡድኑን ሀሳብ ለክፍል ጓደኞቹ እንዲያቀርብ ያድርጉ፡፡ ሁሉም ቡድኖች ሀሳቦቻቸውን ለክፍል ጓደኞቻቸው ከገለጹ በኋላ እርስዎ ጠቅለል ያለ ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡

## 🗝 ቃላት

### ተግባር ፩

**መምህር፡-**

- ✓ ተማሪዎች በተዘረዘሩላቸው ፊደላት የሚመሰረቱ ቃላትን ከሳጥኑ ውስጥ በመምረጥ በፊደላቱ ጎን ቃላቱን እንዲጽፉ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ ተግባሩን ከማሰራትዎ በፊት ምሳሌዎችን ይስጧቸው፡፡
- ✓ ተግባሩን በተባሉት መንገድ መስራታቸውን ለማረጋገጥ በመማሪያ ክፍሉ እየተዘዋወሩ ቅኝት ያድርጉ፡፡
- ✓ ተማሪዎች ቃላትን ከሆሄዎች ጋር በየግላቸው እንዲያዛምዱ ካደረጉ በኋላ የሰሩትን በማየት ግብረ-መልስ ይስጧቸው፡፡ ከዚያም እርስዎ የሰሯቸውን መልሶች ለተማሪዎች ንገሯቸው፡፡

### ተግባር ፪

- ✓ በተግባር ፪ ላይ ያሉ ምስሎችን በትኩረት በመመልከት ስማቸውን በክፍት ቦታው ላይ እንዲጽፉ ያበረታቷቸው፡፡
- ✓ የሰጧውን ምላሾች በመመልከት የተሳሳቱ ተማሪዎች ካሉ ማስተካከያ ይስጧቸው፡፡

### ተግባር ፫

- ✓ ተማሪዎች በክቡ ውስጥ በተዘረዘሩላቸው ፊደላት ቃላት እንዲመሰርቱባቸው ያድርጓቸው፡፡
- ✓ ተግባሩን ከማሰራትዎ በፊት ምሳሌዎቹን እንዲያዩ ያድርጓቸው፤ ግልፅ ካልሆነላቸው አሰራሩን ተጨማሪ ምሳሌዎችን በመስጠት ያሳዩዋቸው፡፡

- ✓ ተግባሩን በተባሉት መንገድ መስራታቸውን ለማረጋገጥ በመማሪያ ክፍሉ እየተዘዋወሩ የጻፏቸውን ቃላት ይመልከቱላቸው፡፡
- ✓ የቃላት ምስረታውን ተግባር ተማሪዎች በግል ከሰሩ በኋላ የሰሯቸውን መልሶች ከተማሪዎች ጋር እንዲነጋገሩ ያድርጉና ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡
- ✓ አንዱን ፊደል በአንድ ቃል ውስጥ ደጋግመው መጠቀም እንደሚችሉ ይንገሯቸው፡፡

የተግባር ፫ ናሙና መልስ

አቀላጥፎ ማንበብ

1. መኮትኮት
2. አንድነት
3. አካፋዎች
4. አከናወነ
5. አተካከል
6. ተከለከለ …

- ✓ ፈጣን ተማሪዎችን ለመደገፍ ሌላ ተመሳሳይ ተግባር አዘጋጅተው እንዲተገብሩ ያድርጉ፡፡

ተግባር ፬

መምህር፡-

- ✓ "አበባማው ግቢ" በሚል ርዕስ ስር ለአንብቦ መረዳት ተግባር የቀረበውን ምንባብ ተማሪዎች እየደጋገሙ እንዲያነቡት ያግዟቸው፡፡

- ✓ ተማሪዎች የቀረበላቸውን ምንባብ ከማንበባቸው በፊት እንዴት ማንበብ እንዳለባቸው ለማሳየት አንድ አጠር ያለ ጽሑፍ መርጠው ወይም አዘጋጅተው በጥሩ የአነባበብ ስልት ያንብቡላቸው፡፡

## ተግባር ፩

**መምህር፡-**

- ✓ ባለፉት ምዕራፎች አቀላጥፌው ያላነበቡ ተማሪዎችን በመለየት ቆመው ድምፅ በማሰማት ለክፍል ጓደኞቻቸው ደቂቃ እየመዘገቡ እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡ (ደቂቃውን እርስዎ ይያዙላቸው)
- ✓ አቀላጥፎ ማንበብን ሲተገብሩ በእርስዎ መንገድ የተለያዩ መተግበሪያ ስልቶችን ቢተገብሩ ይበረታታል፡፡
- ✓ በአቀላጥፎ ማንበብ ወቅት የሚያጋጥሙ ችግሮችን እርስ በእርስ የሚተራረሙበትን አውድ ያመቻቹላቸው፡፡
- ✓ ዐይነ ስውራን ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ካሉ የሚያነቡትን ጽሑፍ በብሬል እንዲጻፍላቸው ከልዩ ፍላጎት ባለሙያዎች ጋር አብረው ይሥሩ፡፡
- ✓ በአቀላጥፎ ማንበብ ስር በትዕዛዝ ፪ ያለውን ተግባር ለተማሪዎቹ ያሳሯቸው፡፡
    - አራት ነጥብ፣ የጥያቄ ምልክትና ቃለ አጋኖ በዓረፍተ ነገር ውስጥ ምን አይነት ድምጸት ሊኖረው እንደሚችል ተማሪዎችን ያስረዷቸው፡፡
    - ሀሳቡ የበለጠ የተብራራ ይሆን ዘንድ የተለያዩ አስረጂዎችን በመጠቀም ያስረዷቸው፡፡
    - ከዚያም በሰጧቸው ምሳሌ መሰረት በተግባር ሁለት የቀረቡትን ዓረፍተ ነገሮች አቀላጥፌው እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ ዓረፍተ ነገሮቹን የተለያዩ ተማሪዎች እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡
- ✓ እጅ የማያወጡ (ለማንበብ ፍቃደኛ ያልሆኑ) ተማሪዎች ካሉም እነሱም እንዲሳተፉ ያበረታቷቸው፡፡
- ✓ የአነባበባቸውን ትክክለኛነት አስመልክቶ እርማት ይስጧቸው፡፡
- ✓ የተማሪዎችን የአቀላጥፎ ማንበብ ሁኔታ እየገመገሙ የተሻለ የማንበብ ለውጥ ያመጡ ተማሪዎችን ያበረታቷቸው፡፡

## ✍ ጽሕፈት

### በቃላት ዓረፍተ ነገር መመስረት

መምህር፡-

- ✓ ተማሪዎች በቃላት ዓረፍተ ነገር በማፍለቅ እንዲመሰርቱ ያድርጓቸው።
- ✓ ተግባሩን ለየብቻቸው እንዲሠሩት ያድርጉ።
- ✓ የሠሩትን ዓረፍተ ነገር የብጤ እርማት እንዲሠጡበት ሁኔታዎችን ያመቻቹላቸው።
- ✓ በመጨረሻም ተማሪዎች ለሠሩት ተግባር እርማትይስጧቸው፡

### ሥርዓተ ነጥብ

- ✓ የአራት ነጥብና የጥያቄ ምልክትን አጠቃቀም በተመለከተ ባለፉት ምዕራፎች የተማሩትን ይዘት ከአሁኑ ይዘት ጋር ለማዛመድ እንዲመች ይከልሱላቸው።
- ✓ ስለቃለአጋኖ አጠቃቀም ያስታውሱ ዘንድ ይከልሉላቸው።
- ✓ አራት ነጥብ፣ የጥያቄ ምልክት እና ቃለ አጋኖን የሚገልጽ ምልክት እና ስማቸውን የሚያሳይ ቻርት በመርጃ መሳሪያነት ይጠቀሙ።
- ✓ ከክለሳውና ከገለጻው በኋላ ቃለአጋኖን በመጠቀም ሁለት ዓረፍተ ነገሮችን እንዲጽፉ ያድርጉ።
- ✓ የጻፉትን ዓረፍተ ነገር ከሥርዓተ ነጥቦች ጋር በማዛመድ መጻፋቸውን ይመልከቱ።

## ታሪክ መጻፍ

- ✓ ታሪክ ለመጻፍ እንደመነሻነት እንዲጠቀሙት የቀረበውን አንቀጽ በአንክሮ እንዲያነቡት ያግዟቸው፡፡
- ✓ ጽሑፉን ሲያነቡ ትኩረት ማድረግ ያለባቸውን ጉዳዮች ቀድመው ይንገሯቸው፡፡
- ✓ ታሪክ እንዴት መጻፍ እንዳለባቸው በቡድን ውይይት እንዲያደርጉ ያመቻቹላቸው፡፡
- ✓ ከዚያም ከቤተሰቦቻቸው ወይም ከሚያውቋቸው ሰዎች አንዳቸውን በመምረጥ ባነበቡት ጽሁፍ መሰረት የህይወት ታሪካቸውን በየግል እንዲጽፉ የቤት ሥራ ይስጧቸው፡፡
- ✓ በግል የጻፏቸውን ታሪኮች በቡድን ሆነው ካዩዋቸው በኋላ አንዱን የተሸለ አጻጻፍ የተከተለውን ታሪክ እንዲመርጡና እንደገና አሻሽለው እንዲጽፉ ያግዟቸው፡፡
- ✓ በየቡድኑ እየተዘዋወሩ ያግዟቸው፤ይምሯቸው፡፡
- ✓ የጻፉትን ታሪክም በማየት እርማት ይስጧቸው፡፡

## የቃላት ፍቺ

- ✓ "የማዕዶት አጎት" የሚለውን ምንባብ መሰረት በማድረግ በመማሪያ መጽሐፉ ለተዘረዘሩ ቃላት ተመሳሳይ ፍቺ እንዲሰጡ ያድርጉ፡፡
- ✓ ለተግባራቱም በቂ ግብረ መልስ ይስጡ፡፡

## የተግባሩ መልስ

| | |
|---|---|
| ሀ. ትጉ | መ. በቀጣይ |
| ለ. ስፍራ | ሠ. ስራውን |
| ሐ. በርትቶ | |

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ "የማርታ ማስታወሻ" የሚለውን ምንባብ ተማሪዎቹ እንዲያዳምጡ ተደርገዋል፡፡ ስዕላዊ መግለጫዎችን በቃላት መግለፅ፤ ቃላትን በመነጠልና በማጣመር እንዲፅፉ፤ የፊደላትን ቦታ በመቀያየር ሌሎች ቃላትን እንዲያዋቅሩ ተደርጓል፡፡ "አበባማው ግቢ" የሚለውን ምንባብ እንዲያነቡ፤ በተጨማሪም በአራት ነጥብ፤ በጥያቄ ምልክትና በቃለ አጋኖ የተጻፈ ፅሁፉን እንዲያነቡ ተደርጓል፡፡

ከላይ በተጠቀሱት ተግባራት ተማሪዎች በዋናነት የማዳመጥ፣ የመናገር፣ የማንበብና የመጻፍ ክህሎታቸው እንዲያዳብሩ ይፈለጋል፡፡ ይህንንም ለመመዘን በተማሪ መጽሐፍ ላይ የማጠቃለያ ተግባራት ቀርበዋል፡፡ እነዚህን ትግበራዎች ተማሪዎች እንዲተገብሩ በማድረግ የተማሪዎችን ክህሎት ይፈትሹ፡፡ ወደኋላ የቀሩ ተማሪዎች ካሉ በተለያዩ ተግባራት እንዲያዳብሩ እገዛ ያድርጉላቸው፡፡ በተማሪ መጽሃፍ ላይ የተቀመጠውን የክለሳ ጥያቄዎች ያሰሯቸው በአግባቡ መስራታቸውን በመከታተል ተገቢውን ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡

አማርኛ
፩ኛ ክፍል

# ምዕራፍ አምስት
# አካባቢ ንፅህና አጠባበቅ

18 ክፍለ ጊዜ

## የምዕራፉ አላማዎች

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- ካዳመጡት ምንባብ ለወጡ ቃላት ፍቺ ይሰጣሉ፡፡
- ከምንባቡ ውስጥ ልዩ የሆነውን ሀሳብ ያወጣሉ፡፡
- ቃለ አጋኖንና የጥያቄ ምልክትን ይለያሉ፡፡
- በነጠላ ዓረፍተ ነገሮች መጨረሻ ላይ አራት ነጥብ ያስገባሉ፡፡

## የምዕራፉ ይዘቶች

- ማዳመጥና መናገር
- የንግግር ድምፅ ግንዛቤ
- የትዕምርተ ድምጽ ግንዛቤ
- የቃላት ጥናት
- ማፍለቅና መረዳት
- ማንበብ
- ፅህፈት

## ማዳመጥ

### የጤና ቁልፍ

**መምህር፡-**

የዕለቱን የትምህርት ዓላማ ያስተዋውቁ፡፡ ቅድመ ማዳመጥ ተግባርን ከ5-7 ደቂቃ በመጠቀም ያሰሯቸው፡፡

- ምን እንደሚያነቡላቸው ተማሪዎች የሚገምቱበት ቻርት ያዘጋጁላቸው፡፡
- መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ካሉ ጽሑፉን በወረቀት በማዘጋጀት ያቅርቡላቸው፡፡
- ለተማሪዎች ስለምን እንደሚያነቡላቸው ይግለጹላቸው፡፡
- እንደተማሪዎቹ ሁኔታ ምንባቡን በተመጠነ ድምፅና ፍጥነት ያንብቡላቸው፡፡
- በንባብ ጊዜ ላይ ያለውን ጥያቄ ለተማሪዎች ያቅርቡላቸው፡፡ ምላሻቸውን ይቀበሏቸው፡፡

### የጤና ቁልፍ

ሁሉም ልጆች አባባ ምትኩ ጋር ለመሄድ ተጣድፈዋል፡፡ ጊዜው ረፍዷል፡፡ ልጆቹ እንደምንም ብለው ግን አባባ ጋር ደረሱ፡፡ አባባም ልጆችዬ እንዴት አደራችሁ? ሰላም ናችሁ? በማለት ሰላምታ ሰጡ፡፡ ልጆቹም ደህና መሆናቸውን ገለፁላቸው፡፡ አባባም ተረታችውን ለማውራት የልጆቹን ሁኔታ መመልከት ጀምሩ፡፡ ሁሉም ልጆች ከሌላ ቀናቸው ለየት ብለው አዩዋቸው፡፡ የተወሰኑት ጸጉራቸው ተንጨብርሯል፤ የተወሰኑት ደግሞ ልብሳቸው ቆሽሿል፡፡ አባባም ሊያወሩት ያሰቡትን ተረት ትተው ወደ ምክር ገቡ፡፡

“ልጆችዬ "ጤና ለሰው ልጅ ወሳኝ ነው፡፡ የሰው ልጆች ጤና ከሌለን በህይወት መኖር አንችልም፡፡ መማር፣ መስራትና ያሰብንበት ቦታ ለመድረስ ይከብደናል፡፡ ስለዚህ ሁላችንም ጤናችንን መጠበቅ ይኖርብናል፡፡”

| ተማሪዎች ጤነኛ ለመሆን ምን ምን ማድረግ አለብን? |
| --- |

ጤናማ ለመሆን ደግሞ የግልና የአካባቢችንን ንፅህና መጠበቅ ያስፈልጋል፡፡ በግላችን ልብሳችንን "ማጠብ፣ ሰውነታችንን መታጠብ፣ ፀጉራችንን መታጠብና ማበጠር፣ ጥርሳችንን መፋቅ እንዲሁም ጥፍራችንን መቁረጥ ይገባል፡፡ ይህንን ብቻ በማድረግ ደግሞ የተሟላ ጤናን ማግኘት አይቻልም፤ ስለዚህአካባቢያችንን ዘወትር በጋራ በመሆን ማፅዳትና መንከባከብ አለብን፡፡ ሌላው የምንጠጣውን ውኃ በማፍላት፤ የሕመም ስሜት ሲሰማን በመታከም ጤናችንን እንጠብቅ፡፡ በአጠቃላይ የጤናችን ቁልፍ ንጽሕህና ስለሆነ ንጽህናችንን በመጠበቅ ጤናችንን እንጠብቅ፡፡"

ብለው ለልጆቹ ምክራቸውን ለገሱ፡፡

መምህር፡-

- ❖ በተማሪው መጽሐፍ ላይ የተሰጡትን የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች በማሰራት የተማሪዎችን የአዳምጦ መረዳት ሁኔታ ይፈትሹ፡፡
- ❖ ተማሪዎች ከሰጡት ምላሽ በመነሳት እርማትም ይስጧቸው፡፡
- ❖ በማዳመጥ ተግባሩ በተጠበቀው የብቃት ደረጃ ላይ ያልደረሱ ተማሪዎች ካሉ ክፍተቱን ለመሸፈን የተለያዩ የተቀረጹ ንግግሮችን በመርጃ መሳሪያነት በመጠቀም የማዳመጥ ተግባርን እንዲለማመዱ ያድርጉ፡፡

🗝 ቃላት

ተግባር ፩

መምህር፡-

- ✓ የማዛመድ ተግባሩን ከማሰራትዎ በፊት ምሳሌ ይስጧቸው፡፡
  - ✓ በተማሪ መጽሐፍ ትዕዛዝ ፩ ላይ ያሉትን የማዛመድ ጥያቄዎች እንዲሰሩ ያግዟቸው፡፡
  - ✓ ትክክለኛውን እርማት ይስጧቸው፡፡

## የተግባር ፩ መልስ

| | |
|---|---|
| 1. ሰ | 4. መ |
| 2. ሠ | 5. ሐ |
| 3. ሀ | 6. ለ |

## ተግባር ፪

**መምህር፦**

- ✓ በተማሪ መጽሐፍ በተግባር ፪ ላይ የተዘረዘሩትን ቃላት በመጠቀም ሌሎች ቃላትን እንዲመሰርቱ ይዘዟቸው፡፡
- ✓ ተግባሩን ለማቅለል ይመች ዘንድ የተለያዩ ምሳሌዎችን ያሰሯቸው፡፡
- ✓ የሚመሰርቷቸው ቃላት የፊደል ብዛታቸው ስላልተወሰነ በአንዱ ቃል በርከት ያሉ ምሳሌዎችን እንዲያፈልቁ ያበረታቷቸው፡፡
- ✓ ተማሪዎች በታዘዙት መልኩ እየሰሩ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ተግባሩን ሲሰሩ እየተዘዋወሩ ይቃኟቸው፡፡
- ✓ ሰርተው እንደጨረሱም የሰሩትን ሥራ ይዩላቸውና ለተሳሳቱ ተማሪዎች ማስተካከያ ይስጡ፤ ተማሪዎች ከጠቀሷቸው ውጭ ሌሎች ቃላት መመስረት ከቻሉ ይቀበሏቸው፡፡

☞ **ማጣመርና መነጠል**

**ተግባር ፩**

**መምህር፡-**

- ✓ ማጣመርና መነጠል በተመለከተ ምንነቱንና ጠቀሜታውን ለተማሪዎች ይከልሱላቸው፡፡
- ✓ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ለማጣመር ተግባር ተነጣጥለው የቀረቡ ቃላትን አጣምረው እንዲጽፉና እዲያነቡ ያድርጉ፡፡
    - በመጀመሪያ በቂ ምሳሌዎችን በመለማመጃነት ያሰሯቸው፡፡
    - ከዚያም በመማሪያ መጽሐፉ ትዕዛዝ ፩ ላይ ተነጣጥለው የተጻፉ ቃላትን አጣምረው እንዲጽፉ ያድርጉ፡፡
    - ከዚያ ሁለት ሁለት ተማሪዎችን በየተራ እያስነሱ አንደኛው ተማሪ ከመማሪያ መጽሐፉ ተነጣጥለው የተጻፉትን ሲያነብ ሌላኛው ተማሪ ደግሞ ተጣምረው የተጻፉ ቃላትን እንዲያነብ ያድርጉ፡፡
    - ነጣጥለውና አጣምረው ሲያነቡ የሚኖሩ ስህተቶችን በመመልከት ቃላዊ ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡
- ✓ ትምህርቱን ለማበልጸግ በመርጃ መሳሪያነት ስዕል፣ የቃላት ካርድ፣ ባለቀለም ወረቀት፣ ካርቶን፣ ጥቁር ሰሌዳ … እንዳስፈላጊነቱና እንደመማሪያ ክፍሉ አመችነት በመምረጥ ይጠቀሙ፡፡

ተግባር ፪

መምህር፡-

✓ በተግባር ፪ ላይ በአዎንታዊ ቅርጽ የቀረቡ ቃላትን ወደአሉታዊ ቅርጽ የሚቀይር ቅጥያ በመጨመር እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡

- ተማሪዎች ተግባሩን በሚገባ እንዲያከናውኑት ከተግባራቱ ውስጥ የመጀመሪያውን በምሳሌነት ያንብቡላቸው፡፡
- በመቀጠል በአዎንታዊ ቅርጽ ከቀረቡት ቃላት ላይ /አል-/ን መጀመሪያ ላይ "-ም"ን ደግሞ መጨረሻ ላይ እንዲቀጥሉ ያግዟቸው፡፡
- በመቀጠል የተነጣጠሉትን ቃላት እንዲያነቧቸው እድል ይስጧቸው፡፡
- በመጨረሻም ቅጥያዎችን ከቃላቱ ጋር አጣምረው እንዲያነቧቸው ያድርጉ፡፡

✓ ተግባሩን በትክክል መሥራታቸውን ለመመዘን ተጨማሪ የቤት ስራ ይስጧቸው፡፡

ንባብ

"ታሞ ከመማቀቅ..."

ተግባር ፩

መምህር፡-

❖ በተማሪ መጽሐፍ ላይ ያሉትን የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች ያሰሯቸው፡፡
❖ ተማሪዎች ለሚሰጧቸው ምላሾች ማበረታቻ ይስጧቸው፡፡
❖ በተማሪዎች መጽሐፍ ላይ ያለውን "ታሞ ከመማቀቅ" የሚለውን ምንባብ ተማሪዎቹ እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡

❖ በንባብ ጊዜ የሚሰሩ ጥያቄዎችን ምላሽ ይሰጡ ዘንድ ያበረታቷቸው፡፡

❖ ተማሪዎች ግለንባባቸውን ሲጨርሱ በተዕዛዝ ፩ የተገለፁትን የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡

**የተግባር ፩ መልስ**

| | |
|---|---|
| 1. ለ | 3. ሐ |
| 2. ሐ | 4. ለ |

❖ ለሰጡት ምላሽም እርማት ይስጧቸው፡፡

## ተግባር ፪

❖ ተማሪዎች "ታሞ ከመማቀቅ..." የሚለውን ምንባብ መልዕክት እንዲለዩ በጋራ እንዲወያዩ ያድርጉ፡፡

- ተማሪዎች ሶስት ወይም አራት አባላት ያሉት ቡድን እንዲመሰርቱ ያድርጉ፡፡
- የቡድን አወያያ (መሪ) እዲመርጡ ያድርጉ፡፡
- የቡድን አባላቱ የምንባቡ መልዕክት በተመለከተ ውይይት እንዲያደርጉ ያመቻቹ፡፡
- የቡድናቸውን ሀሳብ በሁለት ዓረፍተ ነገር ጠቅለል አድርገው እንዲጽፉ ያድርጉ፡፡
- ሁሉም ቡድኖች በታዘዙት መልኩ መስራታቸውን ለማረጋገጥ ቅኝት ያድርጉ፡፡
- ከዚያም ከቡድን አባላቱ መካከል አንድ ተማሪ እርስዎ መርጠው በጽሁፍ ያዘጋጁትን የቡድኑን ሀሳብ ለክፍል ጓደኞቹ እንዲያቀርብ ያድርጉ፡፡ ሁሉም ቡድኖች ሀሳቦቻቸውን ለክፍል ጓደኞቻቸው ከገለጹ በኋላ እርስዎ ጠቅለል ያለ ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡

## አቀላጥፎ ማንበብ

### ተግባር ፩

መምህር፡-

- “ታሞ ከመማቀቅ...” በሚል ርዕስ ስር ለአንብቦ መረዳት ተግባር የቀረበውን ምንባብ ተማሪዎች እየደጋገሙ እንዲያነቡት ያግዟቸው፡፡
- ተማሪዎች ምንባቡን ከማንበባቸው በፊት እንዴት ማንበብ እንዳለባቸው ለማሳየት የተመረጠውን ምንባብ አንድ ጊዜ በጥሩ የአነባበብ ስልት ያንብቡላቸው፡፡
- ባለፉት ምዕራፎች አቀላጥፈው ያላነበቡ ተማሪዎችን በመለየት ቆመው ድምፅ በማሰማት ለክፍል ጓደኞቻቸው ደቂቃ እየመዘገቡ እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡ (ደቂቃውን እርስዎ ይያዙላቸው)
- መጀመሪያ የሚያነቡትንና መጨረሻ ላይ የሚያነቡትን በመገምገሚያና በመከታተያ ቅጽ መዝግበው እገዛ ለሚያስፈልጋቸው እገዛ ይስጡ፡፡
- ተግባሩን ሲያስተገብሩ በመከታተያና በመገምገሚያው ቅጽ መሰረት ግብረመልስ ይስጡ፡፡

| | መስፈርቶች | የመጀመሪያ ንባብ (/) | ሁለተኛ ንባብ (/) |
|---|---|---|---|
| ሀ | በትክክል ያልተነበቡ ፊደላት ብዛት | | |
| ለ | ተቆራርጠው የተነበቡ ፊደላት ብዛት | | |
| ሐ | በትክክለኛ ድምጸት ያልተነበቡ ሥርዓተ ነጥቦች ብዛት | | |
| መ | በአንድ ደቂቃ ውስጥ የተነበቡ ቃላት ብዛት | | |

- ከላይ ለአቀላጥፎ ማንበብ የተዘጋጀውን የትግበራ መከታተያና መገምገሚያ ቅጽ እንዳስፈላጊነቱ ይጠቀሙበት፡፡
- ተማሪዎችም እርስበርስ የብጤ እርማት ይሰጣጡበት ዘንድ በቻርት አዘጋጅተው ለተማሪዎች የሚታይ ቦታ ላይ ያድርጉላቸው፡፡

**ተግባር ፬**

**መምህር፡-**

- ✓ በአቀላጥፎ ማንበብ ስር በትዕዛዝ ፬ ያለውን ተግባር ለተማሪዎቹ ያስሯቸው፡፡
    - አራት ነጥብ፣ የጥያቄ ምልክትና ቃለ አጋኖ በዓረፍተ ነገር ውስጥ ምን አይነት ድምጸት ሊኖርው እንደሚችል ለተማሪዎች ይከልሱላቸው፡፡
    - ሀሳቡ የበለጠ የተብራራ ይሆን ዘንድ የተለያዩ አስረጂዎችን በመጠቀም ያስረዷቸው፡፡
    - ከዚያም በሰጧቸው ምሳሌ መሰረት በተግባር ሁለት የቀረቡትን ዓረፍተ ነገሮች አቀላጥፈው እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ ዓረፍተ ነገሮቹን የተለያዩ ተማሪዎች እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡
- ✓ በመገምገሚያው መስፈርት መሰረት እርስበርስ እንዲተራረሙ ያመቻቹ፡፡
- ✓ የአነባበባቸውን ትክክለኛነት አስመልክቶ እርማት ይስጧቸው፡፡
- ✓ የተማሪዎችን የአቀላጥፎ ማንበብ ሁኔታ እየገመገሙ የተሻለ የማንበብ ለውጥ ያመጡ ተማሪዎችን ያበረታቷቸው፡፡
- ✓ ዐይነ ስውራን ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ካሉ የሚያነቡትን ጽሑፍ በብሬል እንዲጻፍላቸው ከልዩ ፍላጎት ባለሙያዎች ጋር አብረው ይሥሩ፡፡

🗝 ቃላት

## ተግባር ፩

**መምህር፡-**

- ስለተቃራኒ ቃላት ፍቺ ማብራሪያና ምሳሌ ከሰጡ በኋላ በተማሪ መማሪያ መጽሐፍ ትዕዛዝ ፩ ላይ ያለውን ተግባር የክፍል ሥራ ይስጧቸው፡፡
- ለሰጧቸው የክፍል ሥራ እርማት ይስጧቸው፡፡

**የተግባሩ ፩ መልስ**

1. ሠ
2. ሀ
3. መ
4. ለ
5. ሐ

## ተግባር ፪

- ተግባሩን ከማሰራትዎ በፊት ቃላትን ከዓረፍተ ነገሮች ጋር እንዴት ማዛመድ እንዳለባቸው ያስረዷቸው፡፡
- በትዕዛዝ ፪ ላይ በ "ሀ" ረድፍ ያሉ ቃላት በ "ለ" ረድፍ ካሉ ያለውን ቃላትን ከዓረፍተ ነገሮች ጋር የማዛመድ ተግባር ያሰሯቸው፡፡
- በመቀጠል ለተግባሩ እርማት ይስጧቸው፡፡

## ተግባር ፫

- በተማሪ መጽሐፍ ትዕዛዝ ፫ ላይ በስዕል የቀረቡትን ከንጽህና ጋር የተያያዙ አገላለጾችን መረዳት ይችሉ ዘንድ ምሳሌውን ያብራሩላቸው፡፡
- ከዚያም ተግባሩን እንዲሰሩ ያድርጉ፡፡
- ተግባሩን በታዘዙት መሰረት እየሰሩ መሆናቸውን እየዞሩ ይከታተሉ፡፡
- በተጨማሪም ይዘቱን ለማበልጸግ ስዕሎችን፣ ፍላሽ ካርዶችን፣ ባለቀለም ወረቀቶች፣ ቅርፃ ቅርፆችን፣ ካርቱኖችን፣... ይጠቀሙ፡፡

## ተግባር ፱

- በተማሪ መጽሐፍ ትዕዛዝ ፱ ላይ ያልተሟሉ ቃላትን (የተጓደሉ ሆህያትን ያሉባቸው ቃላትን) እንዲያሟሉ የሚያዝ ተግባር ቀርቧል። ተግባሩን ሳይቸገሩ መስራት ይችሉ ዘንድ ምሳሌውን ያብራሩላቸው።
- በምሳሌው መሰረት ተግባሩን እንዲሰሩ ያበረታቷቸው።
- ልዩ ፍላጎት የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች በመማሪያ ክፍል ውስጥ ካሉ ተግባሩ እነሱን ያማክል ዘንድ እንደሁኔታው እርዳታ ያድርጉላቸው።
- ተግባራቱን ሲሰሩ ክትትል ያድርጉላቸው።
- በመጨረሻም እርማት ይስጧቸው።

**ማጣመርና መነጠል**

**መምህር፡-**

- በተማሪ መጽሐፉ ተነጣጥለው የተጻፉ ቃላትን አጣምረው እንዲጽፉ ያድርጉ።
- ተነጣጥለውና ተጣምረው የተጻፉ ቃላትን ተራ በተራ እንዲያነቡና ሁሉም ተማሪዎች እንዲሳተፉ ያበረታቷቸው።
- ሲያጣምሩም ሆነ ሲያነቡ የተፈጠሩ ስህተቶች ካሉ እርማት ይስጧቸው። በትክክል ካጣመሯቸውና ካጣመሯቸው ደግሞ ማበረታቻ ቃላትን ተጠቅመው ያበረታቷቸው።

## ✍ ጽሕፈት

### የተጓደለ ዓረፍተ ነገርን ማሟላት

**መምህር፡-**

- ✓ ተማሪዎች የተጓደሉ ዓረፍተ ነገሮችን በማሟላት እንዲጽፉ ያድርጓቸው።
- ✓ ተግባሩን ለየብቻቸው እንዲሠሩት ያድርጉ።

- ✓ የሚያሚሏቸውን ዓረፍተ ነገሮች የብጤ እርማት እንዲሠጣጡበት ሁኔታዎችን ያመቻቹላቸው፡፡
- ✓ በመጨረሻም ተማሪዎች ለሠሩት ተግባር እርማት ይስጧቸው፡፡

## የቃል ጽሕፈት

መምህር፡-

- ✓ የሚከተሉትን ቃላት እያነበቡላቸው በደብተራቸው እንዲፅፉ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ካሉ በወረቀት ፅፈው ይስጧቸው፡፡

| | |
|---|---|
| • ፎጣ | . ሶፍት |
| • በረኪና | . መወልወያ |
| • ሳሙና | . ውኃ |

- ✓ በትክክል መጻፋቸውን እየዞሩ ይከታተሏቸው፤ ግብረ መልስም ይስጧቸው፡፡

## ስርዓተ-ነጥብ

መምህር፡-

- ✓በትዕዛዝ ፫ ያሉ ዓረፍተ ነገሮችን አራት ነጥብ በመጨመር እንዲያሚሉ ያድርጉ፡፡
- ✓ተግባሩን በተናጥል እንዲሰሩ ያግዟቸው፡፡
- ✓በመርጃ መሳሪያነት የሥርዓተ ነጥቡን ምልክት የያዘ ቻርት ያሳዩአቸው፡፡
- ✓በመጨረሻም የብጤ እርማት እንዲሰጣጡ አድርገው ጠቅለል ያለ ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡
- ✓ተግባሩን ሲሰሩ ዓይነ ስውር ተማሪዎች ካሉ ከልዩ ፍላጎት ባለሙያዎች ጋር በመነጋገር የሚያቀርቡትን ይዘት እነሱን ባማከለ መልኩ ይቅረጹ፤ ሌሎች ልዩ ፍላጎት የሚስፈልጋቸው ተማሪዎች ካሉ እንደሁኔታው አካተው ያሰሯቸው፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የጤና ቁልፍ የሚለውን ምንባብ ተማሪዎቹ እንዲያዳምጡ ተደርገዋል፡፡ “ታሞ ከመማቀቅ” የሚለውን ምንባብ እንዲያነቡ፤የአንብቦ መረዳት፤የ ቃላት፤የማጣመርና የመነጠል፤የዕህፈት…ተግባራት እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡

ከላይ በተጠቀሱት ተግባራት ተማሪዎች በዋናነት የማዳመጥ፣ የመናገር፣ የማንበብና የመጻፍ ክህሎታቸው እንዲዳብር ይፈለጋል፡፡ ይህንንም ለመመዘን በተማሪው መጽሐፍ የማጠቃለያ መልመጃዎች ቀርበዋል፡፡ እነዚህን ትግበራዎች ተማሪዎች እንዲተገብሩ በማድረግ የተማሪዎችን ክህሎት ይፈትሹ፡፡ ወደኋላ የቀሩ ተማሪዎች ካሉ በተለያዩ ተግባራት እንዲያዳብሩ እገዛ ያድርጉላቸው፡፡

አማርኛ

፪ኛ ክፍል

# ምዕራፍ ስድስት

# ባህላዊ ሙዚቃ

18

ክፍለ ጊዜ

## የምዕራፉ አላማዎች

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች�:-

- ፅሑፍን አዳምጠው ተዘውታሪ ቃላትን በመጠቀም ዓረፍተ ነገር ይመሰርታሉ::
- ከሚነበበው ጽሑፍ ውስጥ ተዘውታሪ ቃላትን በመለየት ፍቺ ይሰጣሉ::
- የጥያቄ ምልክትንና ቃለ አጋኖን ይጠቀማሉ::
- ቃላትን ከመነሻ ቅጥያቸው ጋር አጣምረው ይጠራሉ::

## የምዕራፉ ይዘቶች

- ማዳመጥና መናገር
- የንግግር ድምፅ ግንዛቤ
- የትዕምርተ ድምጽ ግንዛቤ
- የቃላት ጥናት
- ማፍለቅና መረዳት
- ማንበብ
- ፅህፈት
- ድምፀት

## 👂 ((( ማዳመጥ

### ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች

**መምህር�:-**

- ቅድመ ማዳመጥ ተግባርን ከ3-5 ደቂቃ በመጠቀም ያሰሯቸው፡፡
- ምን እንደሚያነቡላቸው ተማሪዎች የሚገምቱበት ቻርት ያዘጋጁላቸው፡፡
- ከገመቷቸው ሀሳቦች መካከል የተወሰኑትን ይጻፏቸው፡፡
- መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ካሉ ጽሑፉን በወረቀት በማዘጋጀት ያቅርቡላቸው፡
- ለተማሪዎች ስለምን እንደሚያነቡላቸው ይግለጹላቸው፡፡
- ከሚያዳምጡት ምንባብ ውስጥ የተረዱትን ሃሳብ በሁለት አረፍተነገር እንዲገልጹ ይዘዟቸው፡፡
- እንደተማሪዎቹ ሁኔታ ምንባቡን በተመጠነ ድምፅና ፍጥነት ያንብቡላቸው፡፡
- በንባብ ጊዜ ላይ ያለውን ጥያቄ ለተማሪዎች ያቅርቡላቸው፣ ምላሻቸውን ይቀበሏቸው፡፡

### ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች

ኢትዮጵያ ብዙ የተለያዩ ባህሎች አሏት፡፡ከባህሎቿ አንዱ ባህላዊ ጭፈራ ነው፡፡ባህላዊ ጭፈራውን የሚያጅቡ ደግሞ በርከት ያሉ ባህላዊ ሙዚቃ መሳሪዎች አሉ፡፡ ከባህላዊ የሙዘቃ መሳሪዎች መካከል ማሲንቆ፣ ክራር፣ ዋሽንት፣ በገናና ከበሮ ይጠቀሳሉ፡፡

| ተማሪዎች ክራር ከምን ከምን የሚሰራ ይመስላችኋል? |
|---|

ማሲንቆ ከእንጨትና ከፈረስ ጭራ የሚሰራ ባለአንድ አውታር(ክር) ነው፡፡ ክራር ከእንጨትና ከጅማት ክር አልፎ አልፎ ከቀጭን ሽቦ የሚዘጋጅ ነው፡፡ ዋሽንት ከሸንበቆ የሚሰራ እስከ ስድስት ሚደርሱ ቀዳዳዎች ያሉት የትንፋሽ መሳሪያ ነው፡፡ በገና ከበግ ወይም ከፍየል አንጀት እና ከእንጨት የሚሰራ ባህላዊ ሙዚቃ መሳሪያ ነው፡፡

እነዚህ ባህላዊ ሙዚቃ መሳሪያዎች የተለያዩ ባህላዊ ዘፈኖችን በማጀብ ዜማቸው የተስተካከለ እንዲሆን ያደርጋሉ፡፡ ዜማቸውን ለማስተካከል ማሲንቆ፣ ክራር፣ በገና በእጅ ጣቶች የሚቃኙ ሲሆን ከበሮ በእጅ ይመታል፡፡ ዋሽንት ደግሞ በትንፋሽአገልግሎት ላይ ይውላል፡፡ ባህላዊ ዘፈኑን በመምራት አገልግሎት ላይ የሚውሉት እነዚህ ባህላዊ ሙዚቃ መሳሪያዎች የአገር መለያና ቅርሶች ናቸው፡፡

መምህር፡-

❖ በተማሪው መጽሐፍ ላይ የተሰጡትን የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች በማሰራት የተማሪዎችን የአዳምጦ መረዳት ሁኔታ ይፈትሹ፡፡

❖ ተማሪዎች ከሰጡት ምላሽ በመነሳት እርማትም ይስጧቸው፡፡

❖ ተግባር ፪ን ለማሰራት የሚከተሉትን መንገዶች ይከተሉ፡፡

- ከአራት እስከ ስድስት አባላት ያሉት ቡድን እንዲመሰርቱ ይዘዟቸው፡፡
- የውይይቱን ሂደት እየዞሩ ይከታተሉ፡፡
- በቡድን ሆነው ሲወያዩ የቡድኑ አባላት በማዳመጡ ሂደት የጻፏቸውን ሀሳቦች መሰረት አድርገው እንዲናገሩ ያድርጓቸው፡፡
- በቡድን ውይይቱ የተነሱ ሀሳቦችንና ያዳመጡትን ምንባብ ጠቅለል አድርገው በአንድ ላይ እንዲጽፉ ያድርጓቸው፡፡
- የጻፉትንም ጽሑፍ በማንበብ እርማት ይስጧቸው፡፡

❖ በማዳመጥ ተግባሩ በተጠበቀው የብቃት ደረጃ ላይ ያልደረሱ ተማሪዎች ካሉ ክፍተቱን ለመሸፈን የተለያዩ የተቀረጹ ንግግሮችን በመርጃ መሳሪያነት በመጠቀም የማዳመጥ ተግባርን እንዲለማመዱ ያድርጉ፡፡

🗝 ቃላት

## ተግባር ፩

መምህር፡-

- በተማሪ መጽሐፍ ትዕዛዝ ፩ ላይ በስዕል የቀረቡትን የሙዚቃ መሳሪዎች ከስያሜያቸው ጋር እንዲያዛምዱ ይዘዟቸው፡፡
- ተግባሩን በታዘዙት መሰረት እየሰሩ መሆናቸውን እየዞሩ ይከታተሉ፡፡
- በተጨማሪም ይዘቱን ለማበልጸግ ስዕሎችን፣ ፍላሽ ካርዶችን፣ ባለቀለም ወረቀቶች፣ ቅርፃ ቅርፆችን፣ ካርቱኖችን፣... ይጠቀሙ፡፡
- ትክክለኛውን እርማት ይስጧቸው፡

### የተግባር ፩ መልስ

1. ለ
2. ሀ
3. መ
4. ሠ
5. ሐ

## ተግባር ፪

መምህር፡-

- ✓ በተማሪ መጽሐፍ በተግባር ፪ ያለውን ግጥም በትኩረት ደጋግመው እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡
- ✓ ከዚያም ጥንድ ጥንድ ሆነው በግጥሙ ውስጥ በተመሳሳይ ፊደል የሚጨርሱ ቃላትን ለይተው እንዲያወጡ ይዘዟቸው፡፡
- ✓ ተግባሩን ግልፅ ለማድረግ ይመች ዘንድ የተለያዩ ምሳሌዎችን በመስጠት ያብራሩላቸው፡፡

- ✓ በመጨረሻም በትክክል መስራት አለመስራታቸውን ለማረጋገጥ ደብተራቸውን በማየት ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡
- ✓ የተማሪዎችን ደብተር ሲመለከቱ በርካታ ስህተቶችን የሰሩ ተማሪዎች ካሉ ይዘቱን ለማበልጸግ ቤታቸው ሰርተው የሚያመጡት ሌላ ተግባር ይስጧቸው፡፡

### ተግባር ፫

- ➢ ከማሰራትዎ በፊት ሆህያትን ከቃላት ጋር እንዴት ማዛመድ እንዳለባቸው ያስረዷቸው፡፡
- ➢ በትዕዛዝ ፫ ላይ ያሉትን ሆህያት ከቃላት ጋር የማዛመድ ተግባር ያሰሯቸው፡፡
- ➢ በመቀጠል ለተግባሩ እርማት ይስጧቸው፡፡

☞ **መነጠልና ማጣመር**

### ተግባር ፩

**መምህር፡-**

- ✓ በቃል መጀመሪያ ላይ ሊመጡ ስለሚችሉ ቅጥያዎች በልጆቹ ደረጃ መጥነው ያስረዷቸው፡፡ የማብራሪያ ዓላማ ስለቅጥያዎቹ አይነትና አገልግሎት ማሳወቅ ሳይሆን መነጠል እንዲችሉ ለማድረግ ነው፡፡
- ✓ ማብራሪያው ለተማሪዎቹ ግልጽ ይሆን ዘንድ በተለያዩ አስረጅዎች ይደገፉ፡፡
- ✓ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ለመነጠል ተግባር የቀረቡ ቃላትን ነጣጥለው እንዲጽፉና እዲያነቡ ያድርጉ፡፡
- ✓ ነጣጥለው የጻፏቸውን ለማንበብ ሁለት ሁለት ተማሪዎችን በየተራ እያስነሱ አንደኛው ተማሪ ከመማሪያ መጽሐፉ ተጣምረው የተጻፉትን ሲያነብ ሌላኛው ተማሪ ደግሞ ተነጣጥለው የተጻፉ ቃላትን እንዲያነብ ያድርጉ፡፡

- ✓ ነጣጥለውና አጣምረው ሲያነቡ የሚኖሩ ስህተቶችን በመመልከት ቃላዊ ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡
- ✓ ተግባሩን በሚገባ እንዲሰሩ ለተማሪዎች ተጨማሪ ቃላቶቸን ይስጧቸው፡፡ ለፈጣን ተማሪዎች ደግሞ የመጀመሪያና የመጨረሻ ቅጥያ ያላቸውን ቃላት በመስጠት እንዲነጣጥሉና እንዲያጣምሩ ያግዟቸው፡፡

**የተግባር ፩ መልስ**

1. ከ - እንጨት
2. የ - መሳሪያ
3. የ - ሚሰራ
4. ከ - ሽንበቆ
5. በ - ከብት

## ተግባር ፪

**መምህር፡-**

- ✓ የተማሪዎችን ትዕምርተ ድምጻዊ ግንዛቤ (ምልክቶችን የመረዳትና የመለየት ችሎታን) ለማሳደግ በትዕዛዝ ፪ ላይ ያለውን “እኔ ማን ነኝ?” የሚለውን ተግባር ያሰሯቸው፡፡
- ✓ በትክክል ለመለሱ ተማሪዎች የማበረታቻ ቃላትን ይጠቀሙ፤ ለተሳሳቱት ደግሞ እርማት ይስጧቸው፡፡
- ✓ የተማሪዎች ሄህያትን የመለየት ችሎታ በመመዘን የሚከብዷቸውን ሆህያት እንዲለዩ ስዕሎችን፣ ፍላሽ ካርዶችን፣ ባለቀለም ወረቀቶችን፣ ቅርፃ ቅርፆችን፣ ካርቱኖችን፣... በመርጃ መሳሪያነት በመጠቀም ያለማምዷቸው፡፡

## 📖 ንባብ

**መምህር፡-**

- ❖ በተማሪ መጽሐፍ ላይ ያሉትን የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች ያሰሯቸው፡፡
- ❖ ተማሪዎች ለሚሰጧቸው ምላሾች ማበረታቻ ይስጧቸው፡፡
- ❖ በተማሪዎች መጽሐፍ ላይ ያለውን "የባህል ቀን" የሚለውን ምንባብ ተማሪዎቹ እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡
- ❖ በንባብ ጊዜ የሚሰሩ ጥያቄዎችን ምላሽ ይሰጡ ዘንድ ያበረታቷቸው፡፡
- ❖ ተማሪዎች ግለ ንባባቸውን ሲጨርሱ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን በምንባቡ መሰረት እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡
- ❖ ለሰጡት ምላሽም እርማት ይስጧቸው፡፡

## ቃላት

### ተግባር ፩

**መምህር፡-**

- ➢ በተማሪ መማሪያ መጽሐፍ ትዕዛዝ ፩ ላይ ያለውን የማዛመድ ተግባር የክፍል ሥራ ይስጧቸው፡፡
- ➢ ለሰጧቸው የክፍል ሥራ እርማት ይስጧቸው፡፡

**የተግባሩ ፩ መልስ**

| | |
|---|---|
| 1. ሐ | 4. ሠ |
| 2. ለ | 5. መ |
| 3. ሀ | |

## ተግባር ፬ እና ፫

- ተግባሩን ከማሰራትዎ በፊት በተመሳሳይ ፊደል የሚጀምሩና የሚጨርሱ ቃላትን እንዴት መመስረት እንደሚችሉ ያስረዷቸው።
- የሚሠሩትን ተግባር ሳይቸገሩ ይተገብሩት ዘንድ ከተማሪ መጽሐፉ ካለው ምሳሌ በተጨማሪ ሌሎች ምሳሌዎችንም ይስጧቸው።
- በትዕዛዝ ፬ ላይ የተሰጧቸው ፊደላት በመነሻነት በመጠቀም ቃላትን እንዲመሰርቱ ያግዟቸው።
- በተጨማሪም በትዕዛዝ ፫ ላይ በሚገኘው ትዕዛዝ መሰረት በተመሳሳይ ፊደል የሚጨርሱ ቃላትን እንዲመሰርቱ ያድርጓቸው።
- ተማሪዎቹ ተግባሩን በሚያከናውኑበት ወቅት ምልከታ ያድርጉ።
- በመቀጠል ለተግባሩ እርማት ይስጧቸው።

## ተግባር ፬

- በተማሪ መጽሐፍ ትዕዛዝ ፬ ላይ በሳጥኑ ውስጥ ያሉትን የሙዚቃ መሳሪያዎች ባህላዊና ዘመናዊ በማለት እንዲመድቡ ይዘዟቸው።
- ተግባሩን የበለጠ ግልጽ እንዲሆንላቸው ምሳሌዎችን ቀድመው ይስጧቸው።
- ተግባሩን በታዘዙት መሰረት እየሰሩ መሆናቸውን እየዞሩ ይከታተሉ።
- በተጨማሪም ይዘቱን ለማበልጸግ ስዕሎችን፣ ፍላሽ ካርዶችን፣ ባለቀለም ወረቀቶች፣ ቅርፃ ቅርፆችን፣ ካርቱኖችን፣... ይጠቀሙ።
- ለሰሩት ተግባር ማስተካከያ ይስጧቸው።

## የተግባር ፬ መልስ

| ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች | ዘመናዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች |
|---|---|
| ከበሮ | ጊታር |
| ማሲንቆ | ሳክስፎን |
| ክራር | ፒያኖ |
| በገና | ማንዶሊን |
| ዋሽንት | ኪቦርድ |

## አቀላጥፎ ማንበብ

**መምህር፡-**

- "የባህል ቀን" በሚል ርዕስ ስር ለአንብቦ መረዳት ተግባር የቀረበውን ምንባብ ተማሪዎች እየደጋገሙ እንዲያነቡት ያግዟቸው፡፡
- ተማሪዎች ምንባቡን ከማንበባቸው በፊት እንዴት ማንበብ እንዳለባቸው ለማሳየት የተመረጠውን ምንባብ አንድ ጊዜ በጥሩ የአነባበብ ስልት ያንብቡላቸው፡፡
- ባለፉት ምዕራፎች አቀላጥፈው ያላነበቡ ተማሪዎችን በመለየት ቆመው ድምፅ በማሰማት ለክፍል ጓደኞቻቸው ደቂቃ እየመዘገቡ እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡ (ደቂቃውን እርስዎ ይያዙላቸው)
- መጀመሪያ የሚያነቡትንና መጨረሻ ላይ የሚያነቡትን በመገምገሚያና በመከታተያ ቅጽ መዝግበው እገዛ ለሚያስፈልጋቸው እገዛ ይስጡ፡፡
- ተግባሩን ሲያስተገብሩ በመከታተያና በመገምገሚያው ቅጽ መሰረት ግብረመልስ ይስጡ፡፡

| መስፈርቶች | | የመጀመሪያ ንባብ | ሁለተኛ ንባብ |
|---|---|---|---|
| | | (/) | (/) |
| ሀ | በትክክል ያልተነበቡ ፊደላት ብዛት | | |
| ለ | ተቆራርጠው የተነበቡ ፊደላት ብዛት | | |
| ሐ | በትክክለኛ ድምጸት ያልተነበቡ ሥርዓተ ነጥቦች ብዛት | | |
| መ | በአንድ ደቂቃ ውስጥ የተነበቡ ቃላት ብዛት | | |

- ከላይ ለአቀላጥፎ ማንበብ የተዘጋጀውን የትግበራ መከታተያና መገምገሚያ ቅጽ እንዳስፈላጊነቱ ይጠቀሙበት፡፡
- ተማሪዎችም እርስበርስ የብጤ እርማት ይሰጣጡበት ዘንድ በቻርት አዘጋጅተው ለተማሪዎች የሚታይ ቦታ ላይ ያድርጉላቸው፡፡

✍ ጽሕፈት ተግባር ፩

## የቃል ጽሕፈት

መምህር፡-

✓ የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች እያነበቡላቸው ተማሪዎቹ በደብተራቸው እንዲፅፉ ያድርጓቸው፡፡

- ባህላዊ መሳሪያዎች ለሙዚቃ ያስፈልጋሉ፡፡
- ሙዚቃ መንፈስን ያድሳል፡፡

✓ የጻፏቸውን ዓረፍተ ነገሮች በትክክል መጻፋቸውን በመመልከት እርማት ይስጧቸው፡፡ ትምህርቱን ለማበልጸግም የተለያዩ የተቀረጹ ድምጾችን በመርጃ መሳሪያነት ያቅርቡላቸው፡፡

## ተግባር ፪
## ስርዓተ-ነጥብ

መምህር፡-

✓በመርጃ መሳሪያነት የጥያቄ ምልክትና ቃለ አጋኖን ሥርዓተ ነጥቦችን የያዘ ቻርት (ፍላሽ ካርድን) ይጠቀሙ፡፡

✓ትዕዛዝ ፪ ላይ ያለውን ተግባር ያሰሯቸው፡፡

✓የእርስ በርስ እርማት እንዲሰጣጡ አድርገው ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡

## ተግባር ፫

## ተማሪዎቹ ላወጡት ጥያቄ በጽሑፍ ምላሽ መስጠት

✓በትዕዛዝ ፫ የቀረቡትን ተግባራት በቡድን ሆነው እንዲሰሩ እገዛ ያድርጉላቸው፡፡ ተማሪዎቹ ጥያቄዎች አውጥተው በጋራ በመሆን በፅሁፍ ምላሽ የሰጡበትን ተግባር ላይ ውይይት በማድረግ ማስተካከያ ሃሳብ ይስጧቸው፡፡

✓ተግባሩን ሲሰሩ ዓይነ ስውር ተማሪዎች ካሉ ከልዩ ፍላጎት ባለሙያዎች ጋር በመነጋገር የሚያቀርቡትን ይዘት እነሱን ባማከለ መልኩ ይቅረጹ፤ ሌሎች ልዩ ፍላጎት የሚስፈልጋቸው ተማሪዎች ካሉ እንደሁኔታው አካተው ያሰሯቸው፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ “ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች” የሚለውን ምንባብ ተማሪዎቹ እንዲያዳምጡ ተደርገዋል፡፡ “የባህል ቀን” የሚለውን ምንባብ እንዲያነቡ፤ የአንብቦ መረዳት፤የቃላት፤ የማጣመርና የመነጠል፤የፅህፈት…ተግባራት እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡

ከላይ በተጠቀሱት ተግባራት ተማሪዎች በዋናነት የማዳመጥ፣ የመናገር፣ የማንበብና የመጻፍ ክህሎታቸው እንዲዳብር ይፈለጋል፡፡ ይህንንም ለመመዘን በተማሪው መጽሐፍ የማጠቃለያ ተግባሮች ቀርበዋል፡፡ እነዚህን ትግበራዎች ተማሪዎች እንዲተገብሩ በማድረግ የተማሪዎችን ክህሎት ይፈትሹ፡፡ ወደኋላ የቀሩ ተማሪዎች ካሉ በተለያዩ ተግባራት እንዲያዳብሩ እገዛ ያድርጉላቸው፡፡

## አማርኛ
## ፪ኛ ክፍል

# ምዕራፍ ሰባት
# መልካም ስነ ምግባር

18
ክፍለ ጊዜ

**የምዕራፉ አላማዎች**

ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ መጠናቀቅ በኋላ፡-

- የአዳመጡት ፅሑፍ ውስጥ አዳዲስ ቃላትን በመጠቀም ነጠላ ዓ.ነገር ይመሰርታሉ፡፡
- ከምንባቡ ለወጡ ቃላት አውዳዊ ፍቺ ይሰጣሉ
- ተመሳሳይ ቅጥያ ያላቸውን ቃላት ይዘረዝራሉ፡፡
- በተገቢ ፍጥነት አጫጭር ታሪኮችን ያነባሉ፡፡
- የተሰጣቸውን ቃላት በትክክል ይፅፋል፡፡

**የምዕራፉ ይዘቶች**

- ማዳመጥና መናገር
- የንግግር ድምፅ ግንዛቤ
- የትምዕርተ ድምፅ ግንዛቤ
- የቃላት ጥናት
- ድምፅን የመገንዘብ ችሎታ
- ንባብ
- ፅህፈት
- ማፍለቅና መረዳት

## ((( ማዳመጥ

### ትክክለኛ ዳኛ

**መምህር፡-**

- የዕለቱን የትምህርት ዓላማ ያስተዋውቁ፡፡ ቅድመ ማዳመጥ ተግባርን ከሶስት እስከ አምስት ደቂቃ በመጠቀም ያሰሯቸው፡፡
- ምን እንደሚያነቡላቸው ተማሪዎች የሚገምቱበት ቻርት ያዘጋጁላቸው፡፡
- ተማሪዎች ለቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች የሰጧቸውን ምላሾች በመገመቻ ቻርት ላይ እንዲያሰፍሩ ይዘዟቸው፡፡
- መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ካሉ ጽሑፉን በወረቀት በማዘጋጀት ያቅርቡላቸው፡፡
- ለተማሪዎች ስለምን እንደሚያነቡላቸው ይግለጹላቸው፡፡ በተጨማሪም ሲያዳምጡ አዳዲስ ቃላት ሲገጥሟቸው እንዲመዘግቡ ያድርጓቸው፡፡
- እንደተማሪዎቹ ሁኔታ ምንባቡን በተመጠነ ድምፅና ፍጥነት ያንብቡላቸው፡፡
- በንባብ ጊዜ ላይ ያለውን ጥያቄ ለተማሪዎች ያቅርቡላቸው፡፡ ምላሻቸውን ይቀበሏቸው፡፡

### ትክክለኛ ዳኛ

ፍርድ እንዳይጓደልበት አጥብቆ የሚጠነቀቅ አንድ እውነተኛ ዳኛ ነበር፡፡ ከእለታት አንድ ቀን ወዳጁ ከሰው ጋር ተጣልቶ ተከሰሰና ወደ እርሱ ዘንድ መጣ፡፡ ወዳጁ ወደፍርድ ቤት ከመሄዱ በፊት ከዳኛው ቤት ሄዶ እንዲህ አለው፡፡ "ከአቶ በልሁ ጋር ተካሰን ለሙግት አንተ ጋር መቅረባችን ነውና እንግዲህ የወዳጅነትህን ስራ እንድትሰራልኝ አደራህን፡፡" አለው፡፡

ዳኛው ግን "እኔ በዳኝነቴ የሁለታችሁንም ነገር ያለአድሎ በማመዛዘን እመለከታለሁ፤ እንጂ ወዳጄ ነህ ብዬ ላንተ የምሰራልህ ነገር የለም፡፡" ብሎ መለሰለት፡፡

ወዳጁ ተቆጥቶ "ያንተ ስራ ዳኝነት ነው፡፡ በዳኝነት ስራህ እኔን ወዳጅህን ልትረዳኝና ልትጠቅመኝ ይገባል፡፡ ይህን ካልፈቀድክ ያንተ ፍቅር ለኔ ምን ይጠቅመኛል?" አለው፡፡ ዳኛውም መልሶ "አንተ በእውነት ወዳጄ ከሆንክ ፍርድ ማጉደልን የሚያህል ትልቅ ሐጢያት እንዳልሰራ ታበረታታኛለህ? ህሊናዬንና ክብሬን የሚያዋርድ ተግባር እንድሰራ ትጠይቀኛለህ? ወዳጅነትህ ለዚህ ከሆነ ወዳጅነትህና ፍቅርህ አይጠቅሙኝም፡፡" በማለት መለሰለት፡፡

(ከበደ ሚካኤል፣ ታሪክና ምሳሌ ከተሰኘው መጽሐፍ ለማስተማሪያነት እንዲመች ተሻሽሎ የተወሰደ)

## ተግባር ፩

**መምህር፡-**

- ❖ ተማሪዎች በቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች መሰረት ያሰፈሯቸውን ግምቶች ከአዳመጡት ምንባብ ጋር መዛመዱን እንዲገመግሙ እድል ይስጧቸው፡፡
  - ጥንድ ጥንድ በመሆን የአንዳቸውን ግምት ሌሎቹ እንዲገመግሙ ያድርጉ፡፡
  - የሰጡት ግምት ከተደመጠው ሀሳብ ጋር ለተዛመደላቸው ተማሪዎች የማበረታቻ ቃላትን በመጠቀም ያበረታቷቸው፡፡

- ምስሉ ከተደመጠው ተግባር ጋር ያለውን ግንኙነት በተመለከተ ተማሪዎች ሀሳብ እንዲሰጡ እድል ይስጧቸው፡፡
- የተማሪዎችን ምላሽ በመመልከት በምስሉ ላይ ካሉ ሰዎች አቀማመጥና ከሚዛኖቹ ጋር አዛምደው ምስሉ ከተደመጠው ጽሑፍ ጋር ያለውን ትስስር ያብራሩላቸው፡፡

❖ በተማሪ መጽሐፉ ላይ የተሰጡትን የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች ያሰሯቸው፡፡

❖ ተማሪዎች ከሰጡት ምላሽ በመነሳት እርማትም ይስጧቸው፡፡

የማዳመጥ ችሎታቸውን የተሻለ ለማሳደግ የተለያዩ የተቀረጹ ንግግሮችን ወይም ታሪኮችን በመርጃ መሳሪያነት በመጠቀም የመማር ማስተማር ሂደቱን ይደግፉ፡፡

## ተግባር ፪

**መምህር፡-**

❖ ተማሪዎች የመዘገቧቸው እንግዳ ቃላት ካሉ ለቃላቱ እርስ በእርስ ፍቺ እንዲሰጣጡ ያድርጉ፡፡

ከምንባቡ በአዳመጧቸው አዳዲስ ቃላት አምስት ተራ ዓረፍተ ነገር እንዲጽፉ ይዘዟቸው፡፡

❖ ተግባሩን ከመስራታቸው በፊት ሳይቸገሩ ይሰሩ ዘንድ የተለያዩ ምሳሌዎችን ይስጧቸው፡፡

- ❖ ተግባሩን በሚሰሩበት ጊዜ እርዳታ የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ካሉ እየተዘዋወሩ በመመልከት ያግዟቸው፡፡
- ❖ በመጨረሻም የመሰረቷቸውን ዓረፍተ ነገሮች ትክክለኛነት (ከቋንቋ፣ ከሥርዓተ ነጥብና ከይዘት ትክክለኛነት) አንጻር በመፈተሽ እርማት ይስጧቸው፡፡

## ቃላት

### ተግባር ፩

**መምህር፡-**

- ✓ በተማሪ መጽሐፍ ትዕዛዝ ፩ ላይ ያሉትን የማዛመድ ጥያቄዎች እንዲሰሩ ይዘዟቸው፡፡
- ✓ የሰጡትን ምላሽ ከጓደኞቻቸው ጋር እንዲተያዩና እርስ በርስ እንዲተራረሙ ያድርጉ፡፡
- ✓ ትክክለኛውን እርማት ይስጧቸው፡፡

### የተግባር ፩ መልስ

| | |
|---|---|
| 1. ለ | 4. ሐ |
| 2. መ | 5. ሠ |
| 3. ሀ | |

## ተግባር ፬

**መምህር፡-**

- ✓ በተማሪ መጽሐፍ በተግባር ፬ የተዘረዘሩ ቃላት ከመጨረሻ ቅጥያቸው አንጻር በመደብ በመደብ እንዲመድቡ ይዘዟቸው፡፡
- ✓ ተግባሩን ለማቅለል ይመች ዘንድ የተለያዩ ምሳሌዎችን ይስጧቸው፡፡
- ✓ ተማሪዎች በታዘዙት መልኩ እየሰሩ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ተግባሩን ሲሰሩ እየተዘዋወሩ ይቃኟቸው፡፡
- ✓ ሰርተው እንደጨረሱም የሰሩትን ሥራ ይዩላቸው፡፡ በሚከተለው መልኩ ማስተካከያ ይስጧቸው፡፡

| በ"ች" የሚጨርሱ | በ"ዎች" የሚጨርሱ | በ"ነት" የሚጨርሱ |
|---|---|---|
| በላች | ጫማዎች | የዋህነት |
| አየች | ገበሬዎች | ደግነት |
| ሰራች | ተማሪዎች | ቸርነት |

## መነጠልና ማጣመር

**መምህር፡-**

- ✓ በተማሪ መጽሐፍ ላይ “መልካም” ከሚለው ቃል ላይ ሌላ ቃላትን በመጨመር ጥምር ቃል እንዲመሰርቱ የሚያዘውን ተግባር ያሰሯቸው፡፡
- ✓ ተግባሩን በሚገባ እንዲሰሩት በቂ ምሳሌዎችን ይስጧቸው፡፡
- ✓ ተማሪዎች የሰሩትን ተግባር በማየት ለተሳሳቱት እርማት፤ በትክክል ለሰሩት የማበረታቻ ቃላትን ተጠቅመው ያበረታቷቸው፡፡
- ✓ ትምህርቱን ለማበልጸግ በመርጃ መሳሪያነት ስዕል፣ የቃላት ካርድ፣ ባለቀለም ወረቀት፣ ካርቶን፣ ጥቁር ሰሌዳ … እንዳስፈላጊነቱና እንደመማሪያ ክፍሉ አመችነት በመምረጥ ይጠቀሙ፡፡
- ✓ ተግባሩን በትክክል መሥራታቸውን ለመመዘን ተጨማሪ የቤት ስራ ይስጧቸው፡፡

## 🕮 ንባብ

መምህር፡-

### ተግባር ፩

- ❖ በተማሪ መጽሐፍ ላይ ያሉትን የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች ያሰሯቸው፡፡
- ❖ ተማሪዎች ለሚሰጧቸው ምላሾች ማበረታቻ ይስጧቸው፡፡
- ❖ በተማሪዎች መጽሐፍ ላይ ያለውን "ሀሁ…" የሚለውን ምንባብ ተማሪዎቹ እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡
- ❖ በንባብ ጊዜ የሚሰሩ ጥያቄዎችን ምላሽ ይሰጡ ዘንድ ያበረታቷቸው፡፡
- ❖ ተማሪዎች "ሀሁ…" የሚለውን ምንባብ በግል አንብበው ሲጨርሱ በጥንድ እየተነሱ ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡

### አንብቦ መረዳት

- ❖ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን በምንባቡ መሰረት እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡
- ❖ ለሰጡት ምላሽም እርማት ይስጧቸው፡፡

### የተግባር ፩ መልስ

1. ለ
2. ሐ
3. ሀ

ተግባር ፪

- ተማሪዎች ሶስት ወይም አራት አባላት ያሉት ቡድን እንዲመሰርቱ ያስተባብሩ፡፡
- የቡድን አወያያ (መሪ) እዲመርጡ ያድርጉ፡፡
- የቡድን አባላቱ የምንባቡ መልዕክት በተመለከተ ውይይት እንዲያደርጉ ያመቻቹ፡፡
- የምንባቡን ዋና ሀሳብ በሁለት ዓረፍተ ነገር ጠቅለል አድርገው እንዲጽፉ ትዕዛዝ ይስጡ፡፡
- ሁሉም ቡድኖች በታዘዙት መልኩ መስራታቸውን ለማረጋገጥ ቅኝት ያድርጉ፡፡
- ከዚያም ከቡድን አባላቱ መካከል አንድ ተማሪ እርስዎ መርጠው በጽሁፍ ያዘጋጁትን የቡድኑን ሀሳብ ለክፍል ጓደኞቹ እንዲያቀርብ ያድርጉ፡፡
- ሁሉም ቡድኖች ሀሳቦቻቸውን ለክፍል ጓደኞቻቸው ከገለጹ በኂላ እርስዎ ጠቅለል ያለ ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡

## ቃላት

ተግባር ፩

መምህር፡-

- በተማሪ መፅሃፍ ውስጥ ተግባር ፩ ላይ የቀረቡት ቃላት “ሀሁ…” ከሚለው ምንባብ የወጡት ስለሆኑ በምንባብ ውስጥ ባላቸው አውድ ተማሪዎች እንዲፈቷቸው ምሳሌ በመስጠት አሳዩዋቸው፡፡
- ተማሪዎች ምንባቡ መሰረት አድርገው ቃላቱን እየፈቱ መሆናቸውን ይከታተሉ፡፡
- ለሰጡት ምላሽም እርማት ይስጧቸው፡፡

## የተግባር ፩ መልስ

1. ማወቅ
2. ዘበኛ
3. ጎዳና
4. ትምህርት
5. ተግሳፅ

## ተግባር ፪

### ምልክቶችን ከመጠሪያዎቻቸው ጋር ማስተሳሰር

መምህር፦

- ከተሰጡትን ምልክቶች ውስጥ አንዱን በምሳሌነት ይግለፁላቸው፡፡
- በሂሳብ ትምህርታቸው ላይ የሚገለገሉባቸው ምልክቶችን ተማሪዎቹ እንዲናገሩ እድል ይስጧቸው፡፡ ሀሳቡ የበለጠ የተብራራ ይሆን ዘንድ የተለያዩ ምልክቶችን የሚያሳዩ ካርዶች፣ ስዕሎች፣ ባለቀለም ወረቀቶችና ሌሎችንም በመጠቀም ምልክቶቹን ከፅንሰ ሀሳቦቻቸው ጋር በማያዝ ይግለፁላቸው፡፡
- ከዚያም በሰጧቸው ምሳሌ መሰረት በተግባር ሁለት የቀረቡትን ምልክቶች ከስያሜዎቻቸው ጋር እንዲያዛምዱ ያድርጓቸው፡፡ በመጨረሻም እርማት ይስጧቸው፡፡

## የተግባር ፪ መልስ

1. ለ
2. ሀ
3. ሠ
4. ሐ
5. መ

በተጨማሪ ተማሪዎች ምልክቶችን ከተለያዩ ሀሳቦች ጋር በማጣመር ማንበብና መረዳት እንዲችሉ በትዕዛዝ ፫ ላይ ያለውን ተግባር እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡

- ይዘቱን የበለጠ እንዲረዱት ለማድረግ ሌሎች ምልክቶችን ከተለያዩ ሀሳቦች ጋር በማጣመር እንዲያነቡ የሚያደርጋቸው ተግባር በመቅረፅ ተማሪዎች እንዲሞክሩት ያድርጉ፡፡

**የተግባር ፫ መልስ**

1.አባዛ 2.አካፍል 3.ጨምር 4.ቀንስ 5.እኩል

## አቀላጥፎ ማንበብ

መምህር፡-

- ተማሪዎች "ሀሁ..." የሚለውን ምንባብ በግላቸው እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡
- ደጋግመው በማንበብ እንደአባትና ልጅ በመሆን በቃላቸው እንዲለማመዱ ይዘዟቸው፡፡
- እንደአባትና ልጅ በመሆን በቃላቸው ተለማምደው የመጡ ተማሪዎችን ጥንድ ጥንድ ሆነው ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያቀርቡ እድል ይስጧቸው፡፡
- በሚያቀርቡበትም ሰአት እገዛና ማበረታቻም ይስጧቸው፡፡
- በቃላቸው ሲያቀርቡ ምንባቡን በምን መልኩ እንዳቀረቡት በመከታተያ ቅጽ በመመዝገብ ይከታተሏቸው፡፡
- ተግባሩን በመከታተያና በመገምገሚያው ቅጽ መሰረት ግብረ-መልስ ይስጡ፡፡

| | መስፈርቶች | በጣም ጥሩ | ጥሩ | ዝቅተኛ |
|---|---|---|---|---|
| | | | | |
| ሀ | የተፃፉትን ቃላት በትክክል በቃል የመያዝ ብቃት | | | |
| ለ | የተዘለሉ የቃላት ብዛት | | | |
| ሐ | በትክክለኛ ድምጸት ያልቀረቡ ሥርዓተ ነጥቦች ብዛት | | | |
| መ | በምልልሱ ያለ የመደማመጥ ሁኔታ | | | |

- ከላይ ለአቀላጥፎ ማንበብ የተዘጋጀውን የትግበራ መከታተያና መገምገሚያ ቅጽ እንዳስፈላጊነቱ ይጠቀሙበት፡፡
- ተማሪዎችም እርስበርስ የብጤ እርማት ይሰጣጡበት ዘንድ በቻርት አዘጋጅተው ለተማሪዎች የሚታይ ቦታ ላይ ያድርጉላቸው፡፡

## ጽሕፈት

### ተግባር ፩

መምህር፡-

- ስለተቃራኒ ፍቺ ማብራሪያና ምሳሌ ከሰጡ በኋላ በተማሪ መማሪያ መጽሐፍ ትዕዛዝ ፩ ላይ ያለውን ተግባር የክፍል ሥራ ይስጧቸው፡፡
- የሰሩትን የክፍል ስራ ይዩላቸው፡፡
- ለሰጧቸው የክፍል ሥራ እርማት ይስጧቸው፡፡

## የተግባሩ ፩ መልስ

1. ክፉ
2. ጎበዝ
3. መጥፎ
4. እውነት
5. እርግማን

## ተግባር ፪

ተግባሩን ከማሰራትዎ በፊት መልካም ምግባር እና መጥፎ ምግባር በሚባሉ ርዕሶች ዙሪያ ከተማሪዎች ጋር ውይይት ያድርጉ፡፡ ከዚያም በትዕዛዝ ፪ ስላይ ያለውን ተግባር እንዴት መስራት እንዳለባቸው ያስረዷቸው፡፡

- ከዚያም ተግባሩን ያሰሯቸው፡፡ በመቀጠል ለተግባሩ እርማት ይስጧቸው፡፡

## ተግባር ፫

- በተማሪ መጽሐፍ ትዕዛዝ ፫ ላይ በቀረቡት ቃላት ዓረፍተ ነገር መስራት ይችሉ ዘንድ ምሳሌውን ያብራሩላቸው፡፡ ከዚያም ተግባሩን እንዲሰሩ ያድርጉ፡፡
- ተግባሩን በታዘዙት መሰረት እየሰሩ መሆናቸውን እየዞሩ ይከታተሉ፡፡
- በተጨማሪም ይዘቱን ለማበልጸግ ስዕሎች፣ ፍላሽ ካርዶች፣ ባለቀለም ወረቀቶች፣ ቅርፃ ቅርፆች፣ ካርቱኖች ላይ፣... በተፃፉ ቃላት ተጠቅመው ተማሪዎቹ ዓረፍተ ነገሮችን እንዲሰሩ በማድረግ ያግዟቸው፡፡›

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ “ትክክለኛ ዳኛ” የሚለውን ምንባብ ተማሪዎቹ እንዲያዳምጡ ተደርገዋል፡፡ “ሀሁ…” የሚለውን ምንባብ እንዲያነቡ፤ የአንብቦ መረዳት፤ የቃላት፤ የማጣመርና የመነጠል፤የፅህፈት…ተግባራት እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡

ከላይ በተጠቀሱት ተግባራት ተማሪዎች በዋናነት የማዳመጥ፣ የመናገር፣ የማንበብና የመጻፍ ክህሎታቸው እንዲዳብር ይፈለጋል፡፡ ይህንንም ለመመዘን በተማሪው መጽሐፍ የማጠቃለያ መልመጃዎች ቀርበዋል፡፡ እነዚህን ትግበራዎች ተማሪዎች እንዲተገብሩ በማድረግ የተማሪዎችን ክህሎት ይፈትሹ፡፡ ወደኋላ የቀሩ ተማሪዎች ካሉ በተለያዩ ተግባራት እንዲያዳብሩ እገዛ ያድርጉላቸው፡፡

# አማርኛ ፬ኛ ክፍል

## ምዕራፍ ስምንት
## የምግብ አዘገጃጀት

18 ክፍለ ጊዜ

### የምዕራፉ አላማዎች

ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ መጠናቀቅ በኋላ፡-

- ከአዳመጡት ምንባብ ፅሑፍ ውስጥ ዋናውን መልዕክት ያደራጃሉ፡፡
- ከአዳመጡት ምንባብ ለቃላት ተመሳሳይ ፍቺ ይሰጣሉ፡፡
- ከምንባቡ ውስጥ ተራ ዓረፍተ ነገሮችን ይለያሉ፡፡
- ተመሳሳይ ቅጥያ ያላቸውን ቃላት ይዘረዝራሉ፡፡
- አጫጭር ታሪኮችን አቀላጥፈው ያነባሉ፡፡

### የምዕራፉ ይዘቶች

- ማዳመጥና መናገር
- የንግግር ድምፅ ግንዛቤ
- የት ምዕርተ ድምፅ ግንዛቤ
- የቃላት ጥናት
- ድምፅን የመገንዘብ ችሎታ
- ንባብ
- ፅህፈት
- ማፍለቅና መረዳት
- ድምፀት

## ((( ማዳመጥ

**መምህር፡-**

- የዕለቱን የትምህርት ዓላማ ያስተዋውቁ፡፡ ቅድመ ማዳመጥ ተግባርን ከሶስት እስከ አምስት ደቂቃ በመጠቀም ያሰሯቸው፡፡
- ምን እንደሚያነቡላቸው ተማሪዎች የሚገምቱበት ቻርት ያዘጋጁላቸው፡፡
- ተማሪዎች ለቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች የሰጧቸውን ምላሾች በመገመቻ ቻርት ላይ እንዲያሰፍሩ ይዘዟቸው፡፡
- መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ካሉ ጽሑፉን በወረቀት በማዘጋጀት ያቅርቡላቸው፡፡
- ለተማሪዎች ስለምን እንደሚያነቡላቸው ይግለጹላቸው፡፡ በተጨማሪም ሲያዳምጡ አዳዲስ ቃላት ሲገጥሟቸው እንዲመዘግቡ ያድርጓቸው፡፡
- እንደተማሪዎቹ ሁኔታ ምንባቡን በተመጠነ ድምፅና ፍጥነት ያንብቡላቸው፡፡
- በንባብ ጊዜ ላይ ያለውን ጥያቄ ለተማሪዎች ያቅርቡላቸው፡፡ ምላሻቸውን ይቀበሏቸው፡፡

### ተጋቢኖ

ወ/ሮ መናሹ ለቅሶ ስለ ገጠማቸው በጠዋት ተነስተው ወደ ለቅሶ ሄዱ፡፡ልጃቸው ብሩክም ባለው ወጥ ቁርሱን በልቶ ወደ ትምህርት ቤት ሔደ፡፡ ከትምህርት ቤት ሲመለስ እናቱ አልመጡም፡፡ ወጥም የለም፤ ብሩክም ራበው፤ "እንዴ እናቴ ሽሮ ስትሰራ አይቼ አውቅ የለ ለምን አልሰራም?" ብሎ አሰበ፡፡

ሐሳቡንም እንደሚከተለው ተገበረው። በመጀመሪያ ቀይ እና ነጭ ሽንኩርት ልጦ ከተፈ፤ ቲማቲሙንም ቀጠቀጠ፤ ድስቱን እሳት ላይ ጥዶ ቀይ ሽንኩርቱንና ዘይቱን ጨምሮ አበሰለ፤ የተቀጠቀጠውን ቲማቲም በመጨመር ትንሽ ካበሰለ በኋላ መጠነኛ ውሃ ከለሰ። ውሃው ሲፈላ ምጥን ሽሮ ጨምሮ በሚገባ አዋሃደው። ነጭ ሽንኩርቱንም ጨምሮ በደንብ አንተከተከው። ከማውጣቱ በፊት መብሰሉን አረጋገጠና ጨው ጨምሮ አወጣው።

ከዚያም እንጀራ ላይ አድርጎ ሊበላ ሲል እናቱ በጣም ደክሟቸው መጡ። እግራቸውን አጥቦ ምሳ አቀረበና አብረው በሉ። ወ/ሮ መናሹም በጣም ስለተደሰቱ ብሩክን መረቁት።

## ተግባር ፩

**መምህር፦**

❖ ተማሪዎች በቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች መሰረት ያስፈሯቸውን ግምቶች ከአዳመጡት ምንባብ ጋር መዛመዱን እንዲገመግሙ እድል ይስጧቸው።

- ጥንድ ጥንድ በመሆን የአንዳቸውን ግምት ሌሎቹ እንዲገመግሙ ያድርጉ።
- የሰጡት ግምት ከተደመጠው ሀሳብ ጋር ለተዛመደላቸው ተማሪዎች የማበረታቻ ቃላትን በመጠቀም ያበረታቷቸው።
- ምስሉ ከተደመጠው ተግባር ጋር ያለውን ግንኙነት በተመለከተ ተማሪዎች ሀሳብ እንዲሰጡ እድል ይስጧቸው።

- በተማሪ መጽሐፉ ላይ የተሰጡትን የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች ያሰሯቸው፡፡
- ተማሪዎች ከሰጡት ምላሽ በመነሳት እርማትም ይስጧቸው፡፡

የማዳመጥ ችሎታቸውን የተሻለ ለማሳደግ የተለያዩ የተቀረጹ ንግግሮችን ወይም ታሪኮችን በመርጃ መሳሪያነት በመጠቀም የመማር ማስተማር ሂደቱን ይደግፉ፡፡

## ተግባር ፪

**መምህር፡-**

- ተማሪዎች የምንባቡን ታሪክ በቅደም ተከተል በማደራጀት በዓረፍተ ነገር እንዲያስቀምጡ ያድርጉ፡፡
- ተግባሩን ከመስራታቸው በፊት ሳይቸገሩ ይሰሩ ዘንድ የተለያዩ ምሳሌዎችን ይስጧቸው፡፡
- ተግባሩን በሚሰሩበት ጊዜ እርዳታ የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ካሉ እየተዘዋወሩ በመመልከት ያግዟቸው፡፡
- በመጨረሻም የመሰረቷቸውን ዓረፍተ ነገሮች ትክክለኛነት (ከቋንቋ፣ ከሥርዓተ ነጥብና ከይዘት ትክክለኛነት) እንዲሁም የታሪኩን ፍሰት መጠበቃቸውን በመፈተሽ እርማት ይስጧቸው፡፡

| | |
|---|---|
| መጀመሪያ | ብሩክ እናቱ ለቅሶ ስለሄዱ ወጥ አልቆበት ራበው፡፡ |
| ከዚያ | ብሩክ ጣፋጭ ሽሮ ወጥ ሰራ፡፡ |
| በመቀጠል | ብሩክ ምሳውን አቅርቦ ሊበላ ሲል እናቱ መጡ፡፡ |
| በመጨረሻ | ብሩክ ምሳውን ከእናቱ ጋር በላ፡፡ |

## ቃላት

### ተግባር ፩

**መምህር፡-**

- ✓ በተማሪ መጽሐፍ ትዕዛዝ ፩ ላይ ላሉት ቃላት ምንባቡን መሰረት በማድረግ ተመሳሳይ ፍቺ እንዲሰጡ ያድርጉ፡፡
- ✓ የሰጡትን ምላሽ ከጓደኞቻቸው ጋር እንዲተያዩና እርስ በርስ እንዲተራረሙ ያድርጉ፡፡
- ✓ ትክክለኛውን እርማት ይስጧቸው፡፡

**የተግባር ፩ መልስ**

1. ንጋት
2. ተመግቦ
3. ተመልክቼ
4. ትንሽ
5. ውሃ ጨመረ

(ሌሎች ተዛማጅ ፍቺዎችን ሊሰጡ ይችላሉ።)

## ተግባር ፪

**መምህር፡-**

- ✓ በተማሪ መጽሐፍ በተግባር ፪ የተዘረዘሩ ቃላት በምሳሌው መሰረት ለያይተው እንዲፅፉ ያድርጉ።
- ✓ ተግባሩን ለማቅለል ይመች ዘንድ የተለያዩ ምሳሌዎችን ይስጧቸው።
- ✓ ተማሪዎች በታዘዙት መልኩ እየሰሩ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ተግባሩን ሲሰሩ እየተዘዋወሩ ይቃኟቸው።
- ✓ ሰርተው እንደጨረሱም የሰሩትን ሥራ ይዩላቸው። በሚከተለው መልኩ ማስተካከያ ይስጧቸው።

መልስ፡-

1. እንደ-ፃፈ
2. የ-ተቆጣ
3. ከ-መጣ
4. ስለ-መጣ
5. ለ-እናት

## ተግባር ፫

**መምህር፡-**

- ✓ በተማሪ መጽሐፍ በተግባር ፫ የተቀመጡትን ምስሎች ከትክክለኛ መጠሪያቸው ጋር እንዲያዛምዱ ያድርጉ፡፡
- ✓ በክፍል ውስጥ አይነ ስውር ተማሪዎች ካሉ የምስሎቹን ሁኔታ በድምፅ ይንገሯቸውና ስማቸውን እንዲጠሩ ያድርጉ፡፡
- ✓ በትክክል ማዛመዳቸውን በማየት እርማት ይስጧቸው፡፡

## ንባብ

## የተመጣጠነ ምግብ

**መምህር፡-**

### ተግባር ፩

- ❖ በተማሪ መጽሐፍ ላይ ያሉትን የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች ያሰሯቸው፡፡
- ❖ ተማሪዎች ለሚሰጧቸው ምላሾች ማበረታቻ ይስጧቸው፡፡
- ❖ በተማሪዎች መጽሐፍ ላይ ያለውን የተመጣጠነ ምግብ የሚለውን ምንባብ ተማሪዎቹ እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡
- ❖ በንባብ ጊዜ የሚሰሩ ጥያቄዎችን ምላሽ ይሰጡ ዘንድ ያበረታቷቸው፡፡
- ❖ ተማሪዎች የተመጣጠነ ምግብ የሚለውን ምንባብ በግል አንብበው ሲጨርሱ ከምንባቡ የተረዱትን ሐሳብ ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡

## አንብቦ መረዳት

- ❖ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን በምንባቡ መሰረት እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡
- ❖ ለሰጡት ምላሽም እርማት ይስጧቸው፡፡

የተግባር ፩ መልስ

1. እውነት
2. ሐሰት
3. እውነት

## 🗝 ቃላት

ተግባር ፩

- ተማሪዎች በመማሪያ መፅሃፋቸው ላይ ያሉትን ቃላት በመደብ በመደብ እንዲያስቀምጡ ይደግፏቸው፡፡
- ምሳሌ በመስጠት ተግባሩን ተረድተው እንዲሰሩ ያድርጉ፡፡
- በሚከተለው መልኩ እርማት ይስጧቸው፡፡

| ድርጊት የሚያሳዩ | ለምግብ መጠሪያ የሚሆኑ | መጠንን የሚገልፁ |
|---|---|---|
| 1. ሰራች | 1. ተጋቢኖ | 1. ረጅም |
| 2. ጠጣ | 2. ዳቦ | 2. ቀጭን |
| 3. ጎረሰች | 3. እንጀራ | 3. አጭር |
| 4. በላ | 4. ወጥ | 4. ወፍራም |

## ተግባር ፪

መምህር፡-

- በተማሪ መፅሃፍ ውስጥ ተግባር ፪ ላይ የቀረቡት ቃላት የምግብ አዘገጃጀት ጋር በተዘዋዋሪ ዝምድና ያላቸው ቃላት ናቸው፤ ቃላቱን ከተስማሚ ቃላት ጋር እንዲያጣምሩ ያድርጉ፡፡
- ሌሎች ተጨማሪ ተግባርም ይስጧቸው፡፡
- ለሰጡት ምላሽም እርማት ይስጧቸው፡፡

### የተግባር ፪ መልስ

| | | |
|---|---|---|
| 1. ሀ | 3. ለ | 5. ሀ |
| 2. ለ | 4. ለ | 6. ሀ |

## ተግባር ፫

መምህር፡-

- በተማሪ መፅሃፍ ውስጥ ተግባር ፫ ላይ የቀረቡትን ድርጊት አምልካች ምስሎችን ከቃላቱ ጋር እንዲያዛምዱ ያድርጉ፡፡
- ሌሎች ድርጊት አመልካች ምስሎችን በማሳየት እንዲመልሱ ያድርጉ፡፡
- ለሰጡት ምላሽም እርማት ይስጧቸው፡፡

## ➢ ጽሕፈት

ተግባር ፩

መምህር፡-

- የተመጣጠነ ምግብ ከሚለው ምንባብ ውስጥ ቢያንስ ሶስት ዓረፍተ ነገሮችን እንዲመሰርቱ ይገዟቸው፡፡
- ልዩ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ተግባሩን እንደሚመቻቸው አድርገው እንዲሰሩት ይደግፏቸው፡፡
- ለሰጡት ምላሽም እርማት ይስጧቸው፡፡

ተግባር ፪

መምህር፡-

- በመማሪያ መፅሃፉ ውስጥ ልዩ ልዩ ቃላት ቀርበዋል፤ቃላቱን መሰረት በማድረግ ተማሪዎቹ ዓረፍተ ነገሮችን እንዲሰሩ ያድረጉ፡፡
- ተማሪዎች የሰሯቸውን ዓረፍተ ነገሮች እርስበርስ እየተለዋወጡ እንዲተራረሙ ያግዟቸው፡፡
- ልዩ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ተግባሩን እንደሚመቻቸው አድርገው እንዲሰሩት ይደግፏቸው፡፡
- ሌሎች ቃላትን በመስጠት ዓረፍተ ነገሮችን እየመሰረቱ እንዲለማመዱ ያድርጉ፡፡ እርማትም ይስጧቸው፡፡

## ተግባር ፫

መምህር፡-

- የሚከተለውን አጭር የበዓል ታሪክ በተመጠነ ድምፅና ፍጥነት ለተማሪዎቹ ያንብቡላቸው፡፡
- በመቀጠል በተማሪዎች መፅሃፍ ትዕዛዝ ፫ ላይ በተቀመጠው አካሔድ መሰረት ራሳቸው ታሪክ እንዲፅፉ ይደግፏቸው፡፡
- ተማሪዎች ሲፅፉ እየተዘዋወሩ ይቃኟቸው፤ ማስተካከያ ስጧቸው፡

### አረፋ

ልክ የዛሬ ሁለት ዓመት በአረፋ በዓል እለት ጓደኛዬ ሁሴን ቤት ነበርኩ፡፡ የተለያዩ ምግቦች ተሰርተው በሚያምር ሁኔታ ተደርድረዋል፡፡ ሁሴንና ቤተሰቡ መስጊድ ደርሰው እስኪመጡ ድረስ ቤት እንድሆን ነግረውኝ ሔዱ ፤ ሰግደውም ተመለሱ፡፡ በቴምር አፍጥረው የተደረደረውን ምግብ መመገብ ጀመርን፡፡ ከዚያም በግ በማረድ ሶስት ቦታ ተመደበ፤ አንደኛውን ለራሳቸው፤ አንዱን ለምስኪኖች፤ ሌላኛውን ደግሞ ለቤተሰብ ግብዣ በማድረግ ከፋፈሉት፡፡ የራሳቸውን በጋራ ጠባብሰው ከበሉ በኋላ ለምስኪኖች ሊሰጡ ሔዱ፡፡ ለእኔም ያዘጋጁልኝን ምግብ እየተመገብኩ ህብረትና ፍቅራቸውን ከልቤ አደነቅሁ፡፡ በመጨረሻ ለቤተሰብ ግብዣ ያዘጋጁትን ምግብ ወዳጅ ዘመዶቻቸውን ጠርተው ቡና በማፍላት በጋራ በዓሉት አከበሩ፡፡ ይህ ተግባራቸው እጅግ ደስ የሚልና አስተማሪ በመሆኑ ሁሌም በየአመቱ አረፋ ሲመጣ ጓደኛዬ ሁሴንን አስታውሰዋለው፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ “ተጋቢና” የሚለውን ምንባብ ተማሪዎቹ እንዲያዳምጡ ተደርገዋል፡፡ “የምግብ አዘገጃጀት” የሚለውን ምንባብ እንዲያነቡ፤የአንብቦ መረዳት፤ የቃላት፤ የፅህፈት…ተግባራት እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡

ከላይ በተጠቀሱት ተግባራት ተማሪዎች በዋናነት የማዳመጥ፣ የመናገር፣ የማንበብና የመጻፍ ክህሎታቸው እንዲዳብር ይፈለጋል፡፡ ይህንንም ለመመዘን በተማሪው መጽሐፍ የማጠቃለያ መልመጃዎች ቀርበዋል፡፡ እነዚህን ትግበራዎች ተማሪዎች እንዲተገብሩ በማድረግ የተማሪዎችን ክህሎት ይፈትሹ፡፡ ወደኋላ የቀሩ ተማሪዎች ካሉ በተለያዩ ተግባራት እንዲያዳብሩ እገዛ ያድርጉላቸው፡፡

## የማጠቃለያ ተግባራት

### ተግባር ፩

**መምህር፡-**

- ተማሪዎች ምሳሌውን መሰረት በማድረግ ለቀረቡላቸው ቃላት ትክክለኛ ተጣማሪ የሚሆኑ ቃላትን በመፈለግ እንዲያጣምሩ ያድርጉ፡፡
- በሚከተለው መልኩ እርማት ይስጧቸው፡፡

መልስ፦-

1. ፀጉር ሰሪ
2. ዶሮ አርቢ
3. መዝሙር ዘማሪ
4. ቀለም ቀቢ
5. ዜና አንባቢ

ተግባር ፪

መምህር፦-

በሰንጠረዡ ውስጥ የተለያዩ ፊደላት ቀርበዋል፤ ፊደሎችን ወደላይ፣ ወደታች፣ ወደጎን እንዲሁም አግድም በማገናኘት ቃላትን እንዲመሰርቱ ያድርጉ።

➢ በሚከተለው መልኩ እርማት ይስጧቸው።

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| መ | ጋ | ዝ | ቅ | ጂ |
| ጥ | ዘ | ን | ባ | እ |
| ረ | ሃ | ብ | ት | ህ |
| ጊ | ታ | ር | ጉ | ል |
| ያ | ቤ | ተ | ሰ | ጠ |

ሊመሰረቱ የሚችሉ ቃላት በከፊል

1. መጥረጊያ
2. መጋዝ
3. ዝንብ
4. ቅባት
5. ቅጅ
6. እህል
7. ተርብ
8. ጊታር
9. ብር
10. ረሃብ
11. ሰጠ
12. ንብ
13. ትጉ
14. ሃብት
15. ጋዝ

(ሌሎች ቃላትም ሊመሰረቱ ይችላሉ)

# አማርኛ
## ፪ኛ ክፍል

## ምዕራፍ ዘጠኝ
## ዲጅታል ቁስ

18
ክፍለ ጊዜ

**የምዕራፉ አላማዎች**

ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ መጠናቀቅ በኋላ፡-

- ከአዳመጡት የምንባብ ጽሑፍ ውስጥ ዋናውን መልዕክት ያደራጃሉ፡፡
- ከአዳመጡት ምንባብ ውስጥ ለወጡ ቃላት ተመሳሳይ ፍቺ ይሰጣሉ፡፡
- ለቃላት ዐውዳዊ ፍቺ ይሰጣሉ፡፡
- ቃላትን ከቅጥያዎች ጋር ያነባሉ፡፡
- ዓረፍተ ነገር በትክክል ይጽፋሉ፡፡

**የምዕራፉ ይዘቶች**

- ማዳመጥና መናገር
- የንግግር ድምፅ ግንዛቤ
- የትምዕርተ ድምፅ ግንዛቤ
- የቃላት ጥናት
- ማፍለቅና መረዳት
- ድምፅን የመገንዘብ ችሎታ
- ንባብ
- ፅህፈት
- ማፍለቅና መረዳት
- ድምፀት

## ማዳመጥ

**መምህር፡-**

- የዕለቱን የትምህርት ዓላማ ያስተዋውቁ፡፡ ቅድመ ማዳመጥ ተግባርን ከሶስት እስከ አምስት ደቂቃ በመጠቀም ያሰሯቸው፡፡
- ምን እንደሚያነቡላቸው ተማሪዎች የሚገምቱበት ቻርት ያዘጋጁላቸው፡፡
- ተማሪዎች ለቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች የሰጧቸውን ምላሾች በመገመቻ ቻርት ላይ እንዲያሰፍሩ ይዘዟቸው፡፡
- መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ካሉ ጽሑፉን በወረቀት በማዘጋጀት ያቅርቡላቸው፡፡
- ለተማሪዎች ስለምን እንደሚያነቡላቸው ይግለጹላቸው፡፡
- እንደተማሪዎቹ ሁኔታ ምንባቡን በተመጠነ ድምፅና ፍጥነት ያንብቡላቸው፡፡
- በንባብ ጊዜ ላይ ያለውን ጥያቄ ለተማሪዎች ያቅርቡላቸው፡፡ ምላሻቸውን ይቀበሏቸው፡፡

## መረጃ ማግኛ ቁሶች

መረጃ ለሰው ልጅ አስፈላጊ ከሆኑ ነገሮች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ በመረጃ አማካኝነት ዓለምን ማስተሳሰርና ህይወትን ቀላል ማድረግ ይቻላል፡፡ የሰው ልጆች መረጃን በተለያዩ መንገዶች ያገኛል፡፡ ከእነዚህም ውስጥ በድምጽ ፣ በጽሑፍ ፣ በድምጽና በምስል (በቪዲዮ) በመሳሰሉት መረጃ ሊያገኝ ይቸላል፡፡ በድምጽ የምናገኘው መረጃ በስልክ ፣ በሬዲዮና በመሳሰሉት ይቅርባል፡፡ በጽሑፍ ደግሞ በጋዜጣ፣ በደብዳቤ … ሊቀርብ ሲችል በድምጽና በምስል የሚቀርቡት በቴሌቪዥን፣ በላፕቶፕ በስልክና በመሳሰሉት እናገኛለን፡፡መረጃ የምናገኝባቸው ቁሶች በድሮና በአሁኑ ዘመን የተለያዩ ናቸው፡፡

ተማሪዎች በድሮ ዘመን መረጃ እናገኝባቸው የነበሩ ቁሶች አነማን ናቸው? በአሁን ዘመንስ?

በድሮ ዘመን የመረጃ ልውውጥ የሚካሄደው በጋዜጣ፣ በደብዳቤና በመሳሰሉት ነበር፡፡ በተጠቀሱት ቁሶች መረጃ ለማግኘት በተፈለገው ጊዜ ፈጥኖ ላይገኝ ይችላል፡፡ ሁሉም ቦታዎች ለማዳረስም ያዳግታል፡፡ አሁን ባለንበት ዘመን ይህ ችግር ተፈቷል፡፡ በኢሜል፣ በቴሌ ግራም፣ በፌስ ቡክ፣ በቲዩተር ወዘተ  አማካኝነት ዓለም ላይ እየሆነ ያለውን ነገር በሴኮንዶች እናገኛለን፡፡ ከላይ የተጠቀሱትን መረጃዎች ለማግኘት የምንጠቀምባቸው ዲጂታል ቁሶች እንደ ቴሌቪዥን፣ ራዲዮ፣ ስልክ፣ ታብሌት፣ ላፕቶፕ፣ የመሳሰሉት ናቸው፡፡ እነዚህ ቁሶች ህይወትን በማቅለል ረገድ ትልቅ ድርሻ ቢኖራቸውም በአግባቡ ካልተጠቀምንባቸው ጉዳታቸው ብዙ ነው፡፡

ተግባር ፩

መምህር፡-

- ተማሪዎች በቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች መሰረት ያሰፈሯቸውን ግምቶች ከአዳመጡት ምንባብ ጋር መዛመዱን እንዲገመግሙ እድል ይስጧቸው፡፡
    - ጥንድ ጥንድ በመሆን የአንዳቸውን ግምት ሌሎቹ እንዲገመግሙ ያድርጉ፡፡
    - የሰጡት ግምት ከተደመጠው ሀሳብ ጋር ለተዛመደላቸው ተማሪዎች የማበረታቻ ቃላትን በመጠቀም ያበረታቷቸው፡፡
    - ምስሉ ከተደመጠው ተግባር ጋር ያለውን ግንኙነት በተመለከተ ተማሪዎች ሀሳብ እንዲሰጡ እድል ይስጧቸው፡፡

- በተማሪ መጽሐፉ ላይ የተሰጡትን የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች ያሰሯቸው፡፡
- ተማሪዎች ከሰጡት ምላሽ በመነሳት እርማትም ይስጧቸው፡፡
- የማዳመጥ ችሎታቸውን የተሻለ ለማሳደግ የተለያዩ የተቀረጹ ንግግሮችን ወይም ታሪኮችን በመርጃ መሳሪያነት በመጠቀም የመማር ማስተማር ሂደቱን ይደግፉ፡፡

## ተግባር ፪

መምህር፡-

- የመረጃ ማግኛ ቁሶችን ጥቅምና ጉዳት በተመለከተ ቡድን መስርተው እንዲወያዩ ያመቻቹላቸው፡፡
    - ከአራት እስከ ስድስት አባላት ያለው ቡድን እንዲመሰርቱ ያድርጉ፡፡
    - የቡድኑ መሪና ጸሐፊ እንዲመርጡ ያግዟቸው፡፡
    - የቡድን መሪውንና ጸሐፊውን ድርሻ ይንገሯቸው፡፡ (የቡድኑ መሪ የአወያይነት ሚና እንዲጫወትና በመጨረሻም የሚያቀርብ እንደሆነ፤ ጸሐፊው ደግሞ በውይይቱ የተነሱ ሀሳቦችን በአጭር በአጭር እንዲይዝ ይንገሯቸው፡፡)
    - የሚወያዩበት ርዕሰ ጉዳይ ግልጽ እንዲሆንላቸው መነሻ ሀሳብና ምሳሌ ይስጧቸው፡፡
    - ከዚያም በየቡድናቸው እንዲወያዩ ያድርጉ፡፡
    - የውይይቱን ሂደት እየተዘዋወሩ በመቃኘት የቡድኖችን እንቅስቃሴ ይገምግሙ፡፡
    - ደከም ያለ ተሳትፎ ያለው ቡድን ካለ እገዛ ያድርጉላቸው፡፡

- ከዚያም በቡድን መሪያቸው አማካኝነት ሁሉም ቡድኖች ሀሳቦቻቸውን ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያቀርቡ ያመቻቹላቸው፡፡

❖ የየቡድኖቹ ሀሳብ ከቀረበ በኋላ ከሰጡት ሀሳብ በመነሳት ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡

❖ ተግባሩን ሲያሰሩ የአካቶ ትምህርትን የተማሪዎቹን ሁኔታ ባማከለ መልኩ ይተግብሩ፡፡

❖ እርዳታ የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ለማካተትና ፈጣኖችንም ለማገዝ ተጨማሪ ተግባር ይስጧቸው፡፡ ተግባሩ ሬዲዮ ወይም ቴሌቪዥን በማዳመጥ ያዳመጡትን ሀሳብ እንዲናገሩ ማድረግ ሊሆን ይችላል፡፡ (እንደተማሪዎቹና መማሪያ ክፍሎች ሁኔታ ቤታቸው እንዲሰሩ የሚሰጧቸውን ተግባር እንዳመችነቱ ያዘጋጁ፡፡)

## ⊶ ቃላት

### ተግባር ፩

**መምህር፡-**

❖ ተማሪዎች ከማዳመጥ ምንባቡ የወጡ ቃላትን ጥንድ ጥንድ በመሆን ፍቺ እንዲሰጡ ያድርጉ፡፡

❖ የቃላቱን ዐውድ በደንብ እንዲረዱት እንዳስፈላጊነቱ ቃላቱ ያሉበትን ዓረፍተ ነገሮች ለተማሪዎች ቢያነቡላቸው ጥሩ ነው፡፡

❖ ተግባሩን ከመስራታቸው በፊት ሳይቸገሩ ይሰሩ ዘንድ የተለያዩ ምሳሌዎችን ይስጧቸው፡፡

❖ በመጨረሻም የሰጡትን ምላሽ ትክክለኛነት በመመልከት እርማት ይስጧቸው፡፡

❖ ሌሎች ተጨማሪ ቃላትንም በመስጠት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ እንዲሰጡ የቤት ሥራ ይስጧቸው፡፡

## ተግባር ፪

**መምህር፡-**

- በተማሪ መጽሐፍ ትዕዛዝ ፪ ላይ በምስል የቀረቡትን ዲጂታል ቁሶች ከስያሜዎቻቸው ጋር እንዲያዛምዱ ይዘዟቸው፡፡
- ተግባሩን በታዘዙት መሰረት እየሰሩ መሆናቸውን እየዞሩ ይከታተሉ፡፡
- በተጨማሪም ተግባሩን የበለጠ እንዲያዳብሩት ስዕሎችን፣ ፍላሽ ካርዶችን፣ ባለቀለም ወረቀቶች፣ ቅርፃ ቅርፆችን፣ ካርቱኖችን፣... ይጠቀሙ፡፡

## ንባብ

## የጊዜ ብክነት

**መምህር፡-**

### ተግባር ፩

- በተማሪ መጽሐፍ ላይ ያሉትን የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች ያሰሯቸው፡፡
- ተማሪዎች ለሚሰጧቸው ምላሾች ማበረታቻ ይስጧቸው፡፡
- በተማሪ መጽሐፍ ላይ ያለውን “የጊዜ ብክነት” የሚለውን ምንባብ ተማሪዎቹ እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡
- በንባብ ጊዜ የሚሰሩ ጥያቄዎችን ምላሽ ይሰጡ ዘንድ ያበረታቷቸው፡፡
- የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን በምንባቡ መሰረት እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡
- ለሰጡት ምላሽም እርማት ይስጧቸው፡፡

ተግባር ፪

- ተማሪዎች ሶስት ወይም አራት አባላት ያሉት ቡድን እንዲመሰርቱ ያድርጉ፡፡
- የቡድን አወያያ (መሪ) እዲመርጡ ያድርጉ፡፡
- የቡድን አባላቱ የምንባቡን መልዕክት በተመለከተ ውይይት እንዲያደርጉ ያመቻቹ፡፡
- የምንባቡን ዋና ሀሳብ በሶስት ዓረፍተ ነገሮች ጠቅለል አድርገው እንዲጽፉ ያድርጉ፡፡
- ሁሉም ቡድኖች በታዘዙት መልኩ መስራታቸውን ለማረጋገጥ ቅኝት ያድርጉ፡፡
- ከዚያም ከቡድን አባላቱ መካከል አንድ ተማሪ በጽሁፍ ያዘጋጁትን የቡድኑን ሀሳብ ለክፍል ጓደኞቹ እንዲያቀርብ ያድርጉ፡፡
- ሁሉም ቡድኖች ሀሳቦቻቸውን ለክፍል ጓደኞቻቸው ከገለጹ በኋላ እርስዎ ጠቅለል ያለ ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡

## ቃላት

ተግባር ፩

መምህር፡-

- በተማሪ መማሪያ መጽሐፍ ትዕዛዝ ፩ ላይ ያለውን የማዛመድ ተግባር የክፍል ሥራ ይስጧቸው፡፡
- የማዛመድ ተግባሩን ከሰሩን በኋላ የብጤ እርማት እንዲያካሂዱ ያመቻቹላቸው፡፡
- ለሰጧቸው የክፍል ሥራ እርማት ይስጧቸው፡፡

**የተግባሩ ፩ መልስ**

1. ሐ
2. ሀ
3. ለ
4. ሠ
5. መ

**ተግባር ፪**

**መምህር፡-**

- በተማሪ መጽሐፍ ውስጥ ተግባር ፩ ላይ የቀረቡት ቃላት “የጊዜ ብክነት” ከሚለው ምንባብ የወጡ ስለሆኑ በምንባብ ውስጥ ባላቸው ዐውድ ተማሪዎች እንዲፈቷቸው ምሳሌ በመስጠት ያሳዩዋቸው፡፡
- ተማሪዎች ምንባቡን መሰረት አድርገው ቃላቱን እየፈቱ መሆናቸውን ይከታተሉ፡፡
- ለሰጡት ምላሽም እርማት ይስጧቸው፡፡

## መነጠልና ማጣመር

**ተግባር ፩**

**መምህር፡-**

- ✓ በቃል መጀመሪያ ላይ ሊመጡ ስለሚችሉ ቅጥያዎች በልጆቹ ደረጃ መጥነው ያስረዷቸው፡፡ የማብራሪያ ዓላማ ስለቅጥያዎቹ አይነትና አገልግሎት ማሳወቅ ሳይሆን መነጠል እንዲችሉ ለማድረግ ነው፡፡
- ✓ ማብራሪያው ለተማሪዎቹ ግልጽ ይሆን ዘንድ በተለያዩ አስረጅዎች ይደገፍ፡፡

- ✓ በተማሪ መጽሐፍ ላይ "ስነ-፣ ልበ- እና ቤተ-" በሚሉ ቅድመ ቅጥያዎች ከተዘረዘሩ ቃላት ጋር ተስማሚያቸውን በመምረጥ አጣምረው እንዲጽፉና እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ ተግባሩን በሚገባ ይሰሩት ዘንድ ስለ አሰራሩ ማብራሪያ እና በቂ ምሳሌ ይስጧቸው፡፡
- ✓ ተግባሩን በሚገባ እንዲሰሩት በቂ ምሳሌዎችን ይስጧቸው፡፡
- ✓ ተማሪዎች የሰሩትን ተግባር በማየት ለተሳሳቱት እርማት፤ በትክክል ለሰሩት የማበረታቻ ቃላትን ተጠቅመው ያበረታቷቸው፡፡
- ✓ ትምህርቱን ለማበልጸግ በመርጃ መሳሪያነት ስዕል፣ የቃላት ካርድ፣ ባለቀለም ወረቀት፣ ካርቶን፣ ጥቁር ሰሌዳ ... እንደ አስፈላጊነቱና እንደመማሪያ ክፍሉ አመችነት በመምረጥ ይጠቀሙ፡፡
- ✓ ተግባሩን በትክክል መሥራታቸውን ለመመዘን ተጨማሪ የቤት ስራ ይስጧቸው፡፡

**ተግባር ፱**

**መምህር፡-**

- ✓ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ለማጣመር ተግባር የቀረቡ ቃላትን አጣምረው እንዲጽፉና እዲያነቡ ያድርጉ፡፡
- ✓ አጣምረው የጻፏቸውን ለማንበብ ሁለት ሁለት ተማሪዎችን በየተራ እያስነሱ አንደኛው ተማሪ ከመማሪያ መጽሐፉ ተነጣጥለው የተጻፉትን ሲያነብ ሌላኛው ተማሪ ደግሞ ተጣምረው የተጻፉ ቃላትን እንዲያነብ ያድርጉ፡፡
- ✓ ነጣጥለውና አጣምረው ሲያነቡ የሚኖሩ ስህተቶችን በመመልከት ቃላዊ ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡

✓ ተግባሩን በሚገባ ላልተገበሩ ተማሪዎች ተጨማሪ ተግባር ይስጧቸው፡፡ ለፈጣን ተማሪዎች ደግሞ የመጀመሪያና የመጨረሻ ቅጥያ ያላቸውን ቃላት በመስጠት እንዲነጣጥሉና እንዲያጣምሩ ያግዟቸው፡፡

## አቀላጥፎ ማንበብ

መምህር፡-

- ተማሪዎች "የጊዜ ብክነት"የሚለውን ምንባብ በግላቸው እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡
- ተማሪዎች ምንባቡን ከማንበባቸው በፊት እንዴት ማንበብ እንዳለባቸው ለማሳየት የተመረጠውን ምንባብ አንድ ጊዜ በጥሩ የአነባበብ ስልት ያንብቡላቸው፡፡
- ከዚያም በአንቀጽ እየተከፋፈሉ እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡
- የመከታተያ ቅጽ በሌሌዳ ላይ ወይም በቻርት አዘጋጅተው በሚታይ ቦታ ያድርጉላቸው፡፡
- የመከታተያ ቅጹን መሰረት አድርገው እርስ በርስ ደቂቃ በመያዝ የንባብ ፍጥነትንና በአቀላጥፎ ማንበብ ወቅት የሚጠበቁ ብቃቶችን እንዲተገብሩ ያድርጓቸው፡፡
- ተግባሩን በመከታተያና በመገምገሚያው ቅጽ መሰረት በመከታተል ግብረመልስ ይስጡ፡፡

### ተግባር ፪

መምህር፡-

✓ በአቀላጥፎ ማንበብ ስር በትዕዛዝ ፪ ያለውን ተግባር ለተማሪዎቹ ያሰሯቸው፡፡

- አራት ነጥብ፣ የጥያቄ ምልክትና ቃለ አጋኖ በዓረፍተ ነገር ውስጥ ምን አይነት ድምጸት ሊኖራቸው እንደሚችል ለተማሪዎች ይክልሱላቸው፡፡

- ሀሳቡ የበለጠ የተብራራ ይሆን ዘንድ የተለያዩ አስረጂዎችን በመጠቀም ያስረዷቸው፡፡
- ከዚያም በሰጧቸው ምሳሌ መሰረት በተግባር ሁለት የቀረቡትን ዓረፍተ ነገሮች አቀላጥፈው እንዲያነቡ ያድርገጓቸው፡፡

✓ ዓረፍተ ነገሮቹን የተለያዩ ተማሪዎች እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡

✓ እጅ የማያወጡ (ለማንበብ ፍቃደኛ ያልሆኑ) ተማሪዎች ካሉም እነሱም እንዲሳተፉ ያበረታቷቸው፡፡

✓ የአነባበባቸውን ትክክለኛነት አስመልክቶ እርማት ይስጧቸው፡፡

✓ የተማሪዎችን የአቀላጥፎ ማንበብ ሁኔታ እየገመገሙ የተሻለ የማንበብ ለውጥ ያመጡ ተማሪዎችን ያበረታቷቸው፡፡

## ጽሕፈት

### የቃል ጽሕፈት

መምህር፡-

✓ የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች እያነበቡላቸው በደብተራቸው እንዲፅፉ ያድርጓቸው፡፡

1. ዓለም አንድ መንደር ሆናለች፡፡
2. ዲጂታል ቁሶች ህይወትን ያቀላሉ፡፡
3. ህጻናት ለመምህራቸውና ለወላጆቻቸው መታዘዝ አለባቸው፡፡

✓ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ካሉ በወረቀት ፅፈው ይስጧቸው፡፡

✓ በትክክል መጻፋቸውን እየዞሩ ይከታተሏቸው፤ ግብረ መልስም ይስጧቸው፡፡

**የመጽሔት ምላሽ**

**መምህር፡-**

- በየዕለቱ በክፍል ውስጥ ከሚያከናውኑት ተግባር ሁለቱን እንዲመዘግቡ ያድርጉ፡፡
- ተማሪዎች ባለፈው ክፍለ ጊዜ ከተማሩት ትምህርት ውስጥ ሁለቱን ተግባር በአራት አጫጭር ዓረፍተ ነገሮች እንዲጽፉ ያበረታቷቸው፡፡
- ዓረፍተ ነገሮችን ሲጽፉ ሥርዓተ ነጥቦችን በአግባቡ እንዲጽፉ ያበረታቷቸው፡፡
- የጻፏቸውን ዓረፍተ ነገሮች ከሥርዓተ ነጥቦች አጠቃቀም፣ ከዓረፍተ ነገር አወቃቀር እና ከፊደል አጻጻፍ ትክክለኛነት አንጻር በመገምገም እርማት ይስጧቸው፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ “መረጃ ማግኛ ቁሶች” የሚለውን ምንባብ ተማሪዎቹ እንዲያዳምጡ ተደርገዋል፡፡ “የጊዜ ብክነት” የሚለውን ምንባብ እንዲያነቡ፤ የአንብቦ መረዳት፤ የቃላት፤የማጣመርና የመነጠል፤ የጽሕፈት…ተግባራት እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡

ከላይ በተጠቀሱት ተግባራት ተማሪዎች በዋናነት የማዳመጥ፣ የመናገር፣ የማንበብና የመጻፍ ክህሎታቸው እንዲዳብር ይፈለጋል፡፡ ይህንንም ለመመዘን በተማሪው መጽሐፍ የማጠቃለያ መልመጃዎች ቀርበዋል፡፡ እነዚህን ትግበራዎች ተማሪዎች እንዲተገብሩ በማድረግ የተማሪዎችን ክህሎት ይፈትሹ፡፡ ወደኋላ የቀሩ ተማሪዎች ካሉ በተለያዩ ተግባራት እንዲያዳብሩ እገዛ ያድርጉላቸው፡፡

## አማርኛ
## ፩ኛ ክፍል

# ምዕራፍ አስር
# የዱር እንስሳት

18
ክፍለ ጊዜ

**የምዕራፉ አላማዎች**

ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ መጠናቀቅ በኋላ፡-

- ከአዳመጡት ምንባብ ዋናውን መልዕክት በፅሑፍ ዘገባ ያቀርባሉ፡፡
- የምንባቡን ሐሳብ ከተጨባጭ ህይወታቸው ጋር ያዛምዳሉ፡፡
- ቃለአጋኖን እና የጥያቄ ምልክትን ይጠቀማሉ፡፡
- አቀላጥፈው ያነባሉ፡፡
- ለደረጃው የሚመጥን ዓረፍተ ነገር ይመሰርታሉ፡፡

**የምዕራፉ ይዘቶች**

- ማዳመጥና መናገር
- የንግግር ድምፅ ግንዛቤ
- የትምዕርተ ድምፅ ግንዛቤ
- የቃላት ጥናት
- ድምፅን የመገንዘብ ችሎታ
- ንባብ
- ፅህፈት
- ማፍለቅና መረዳት
- ድምፀት

## ማዳመጥ

**መምህር፡-**

- የዕለቱን የትምህርት ዓላማ ያስተዋውቁ። ቅድመ ማዳመጥ ተግባርን ከሶስት እስከ አምስት ደቂቃ በመጠቀም ያሰሯቸው።
- ምን እንደሚያነቡላቸው ተማሪዎች የሚገምቱበት ቻርት ያዘጋጁላቸው።
- ተማሪዎች ለቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች የሰጧቸውን ምላሾች በመገመቻ ቻርት ላይ እንዲያሰፍሩ ይዘዟቸው።
- መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ካሉ ጽሑፉን በወረቀት በማዘጋጀት ያቅርቡላቸው።
- ለተማሪዎች ስለምን እንደሚያነቡላቸው ይግለጹላቸው፤ በተጨማሪም ሲያዳምጡ አዳዲስ ቃላት ሲገጥሟቸው እንዲመዘግቡ ያድርጓቸው።
- እንደተማሪዎቹ ሁኔታ ምንባቡን በተመጠነ ድምፅና ፍጥነት ያንብቡላቸው።
- በንባብ ጊዜ ላይ ያለውን ጥያቄ ለተማሪዎች ያቅርቡላቸው፤ ምላሻቸውን ይቀበሏቸው።

# ብልኋ ዝንጀሮ

ዘምዘምና ናትናኤል ቅጠል ለመልቀም ወደ ጫካ ሔዱ።ቅጠል እየለቀሙ እያለ አንዲት ትንሽ ዝንጀሮ ወድቃ አዩ። ሲያነሷትም እግሯ መሰበሩን ተረዱ።በጣም ስላሳዘነቻቸው ወደ ቤታቸው ይዘዋት ሔዱ።

እግሯንም በሸንበቆና በጨርቅ አሰሩላት፡፡ የትንሿ ዝንጀሮ እናት ለልጇ ምግብ ይዛ መጣች፡፡ ልጇ ግን በቦታው የለችም፡፡ ፍለጋ ስትወጣ የእነዘምዘምን ኮቴ ሰማች፡፡ እነሱ እንደወሰዱባት ገመተች፡፡

በጣም ስለተናደደች ወደመንደሩ ገብታ አንድ ህፃን ልጅ ይዛ መሮጥ ጀመረች፡፡ የሰፈሩ ሰዎች ህፃኑን ይዛ ስትሔድ ስላዩዋት ተከተሉዋት፤ ሊደርሱባት ግን አልቻሉም፡፡ ልጁን ይዛ ትልቅ ዛፍ ላይ ወጥታ ቁጭ አለች፡፡ ሰዎቹም ዛፍ ላይ ለመውጣት ቢሞክሩም አቃታቸው፡፡ እሷም ዛፍ ላይ ቁጭ ብላ አልወርድም አለች፡፡

ዘምዘምና ናትናኤል ወደቤት ሔደው ለትንሿ ዝንጀሮ ወተት ሰጧት፡፡ ከዚያም ዞር ዞር ብለው ወላጆቻቸውን ቢፈልጓቸው አጧቸው፡፡ በመደናገጥ ወደ ጎረቤት ሔዱ ግን በአካባቢው ማንም ሰው የለም፡፡ ግራ ገብቷቸው ዝንጀሮዋን ቤት ውስጥ አስቀምጠው መነጋገር ጀመሩ፡፡ ናትናኤል "ምናልባት ቆይተንባቸው ሊፈልጉን ወጥተው ይሆናል ስለዚህ ወደ ጫካ እንሂድ" አለ፡፡

ዘምዘምም በሃሳቡ ተስማምታ እየሔዱ እያለ አባባ መርጊያን አገኟቸው፡፡ ዘምዘምም ለአባባ ሰላምታ ካቀረበች በኋላ የት ሄደው እነደሆነ ጠየቀቻቸው፡፡ አባባም የሆነውን ሁሉ ነገሯት፡፡ ዘምዘምም ድንግጥ ብላ"የዝንጀሮዋ ልጅ ተሰብራ አግኝተናት እርስዎ ባስተማሩን መንገድ ጠግነን ወተት ሰጥተናት ነው የመጣነው" አለቻቸው፡፡ አባባም "ትንሿን ዝንጀሮ ለእናቷ መልሱ አለበለዚ ደቦጭ መሞቱ ነው" አሏቸው፡፡ እነሱም ዝንጀሮዋን ይዘው በመሄድ ዛፉ ስር አስቀመጧት፡፡ ከዚያም ራቅ አሉ፡፡ ዝንጀሮዋም ሰዎቹ በአካባቢው አለነመኖራቸውን አይታ ደቦጭን አስቀምጣ ልጇን ይዛ ወደ ጫካው ገባች፡፡

## አዳምጦ መናገር

### ተግባር ፩

**መምህር፡-**

- ❖ ተማሪዎች በቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች መሰረት ያሰፈሯቸውን ግምቶች ካዳመጡት ምንባብ ጋር መዛመዱን እንዲገመግሙ እድል ይስጧቸው፡፡

. ጥንድ ጥንድ በመሆን የአንዳቸውን ግምት ሌሎቹ እንዲገመግሙ ያድርጉ፡፡

. የሰጡት ግምት ከተደመጠው ሀሳብ ጋር ለተዛመደላቸው ተማሪዎች የማበረታቻ ቃላትን በመጠቀም ያበረታቷቸው፡፡

. በተማሪ መጽሐፉ ላይ የተሰጡትን የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች ያሰሯቸው፡፡

. ተማሪዎች ከሰጡት ምላሽ በመነሳት እርማትም ይስጧቸው፡፡

. የማዳመጥ ችሎታቸውን የተሻለ ለማሳደግ የተለያዩ የተቀረጹ ንግግሮችን ወይምታሪኮችን በመርጃ መሳሪያነት በመጠቀም የመማር ማስተማር ሂደቱንይደግፉ፡፡

## ተግባር ፪

መምህር፡-

- “ብልኋ ዝንጀሮ” በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ደግመው ያንብቡላቸው፡፡
- ሲያነቡላቸው ተማሪዎቹ ዋና ዋና ነጥቦችን እንዲፅፉ ትዕዛዝ ይስጧቸው፡፡
- ከዚያም ያዳመጡትን ምንባብ አጠቃላይ ሐሳብ ተራ በተራ እየተነሱ እንዲናገሩ ያድረጉ፡፡
- እርማትና ማበረታቻ ይስጧቸው፡፡

## 🗝 ቃላት

## ተግባር ፩

መምህር፡-

- ✓ የቃላትን ዐውዳዊ ፍቺ በተመለከተ አጭር ገለፃ ያድርጉላቸው፡፡
- ✓ ምሳሌም ይስጧቸው፡፡
- ✓ በተማሪ መጽሐፍ ትዕዛዝ ፩ ላይ ላሉት ቃላት ምንባቡን መሰረት በማድረግ ዐውዳዊ(አገባባዊ) ፍቺ እንዲሰጡ ያድርጉ፡፡
- ✓ የሰጡትን ምላሽ ከጓደኞቻቸው ጋር እንዲተያዩና እርስ በርስ እንዲተራረሙ ያድርጉ፡፡
- ✓ ዓይነ ስውር ተማሪዎች ካሉ ቃላቱ በቃል እየተነበበላቸው አገባባዊ ፍቺ እንዲሰጡ ያድርጉ፡፡ አካቶ ትምህርትን እንደ ሁኔታው ይተግብሩ፡
- ✓ ትክክለኛውን እርማት ይስጧቸው፡፡ የቤት ስራ ይስጧቸው፡፡

## የተግባር ፩ መልስ

| ቃላት | አውዳዊ ፍቺ |
|---|---|
| 1. ቅጠል | የረገፈ የዛፍ አካል |
| 2. የሰፈሩ | የአካባቢው |
| 3. ወላጆች | ቤተሰቦች (እናት እና አባቶች) |
| 4. መደናገጥ | መርበትበት |
| 5. ጫካ | ደን |
| 6. ወተት | የላም ተዋፅኦ |

(ሌሎች ተዛማጅ ፍቺዎችን ሊሰጡ ይችላሉ።)

## ተግባር ፪

**መምህር፡-**

- ✓ በተማሪ መጽሐፍ በተግባር ፪ የተዘረዘሩ ቃላት የመነሻ ሆሄያትን በሌላ በመተካት ሌላ ቃል እንዲመሰርቱ ያድርጉ።
- ✓ ተግባሩን ለማቅለል ይመች ዘንድ የተለያዩ ምሳሌዎችን ይስጧቸው።
- ✓ ተማሪዎች በታዘዙት መልኩ እየሰሩ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ተግባሩን ሲሰሩ እየተዘዋወሩ ይቃኟቸው።
- ✓ ሰርተው እንደጨረሱም የሰሩትን ሥራ ይዩላቸው። በሚከተለው መልኩ ማስተካከያ ይስጧቸው።

**መልስ፡-**

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 1. ጅብ | ልብ | 2. በሬ | ክሬ/ብሬ | 5. ግመል |
| 3. ቀበሮ | ከበሮ | 4. ጉሬዛ | ቃሬዛ | አመል |

## ተግባር ፫

**መምህር፡-**

✓ በተማሪ መጽሐፍ በተግባር ፫ የተቀመጡትን ምስሎች ከትክክለኛ መጠሪያቸው ጋር እንዲያዛምዱ ያድርጉ።

✓ በክፍል ውስጥ አይነ ስውር ተማሪዎች ካሉ የምስሎቹን ሁኔታ በድምፅ ይንገሯቸውና ስማቸውን እንዲጠሩ ያድርጉ።

✓ ተጨማሪ ምስሎችን በማሳየት የምስሎችን ስም በደብተራቸው እየፃፉ የፅህፈት ክህሎታቸው እንዲጎለብት ያግዟቸው።

# 🕮 ንባብ

## ጠጣ

### ተግባር ፩

**መምህር፡-**

❖ በተማሪ መጽሐፍ ላይ ያሉትን የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች ያሰሯቸው።

❖ ተማሪዎች ለሚሰጧቸው ምላሾች ማበረታቻ ይስጧቸው።

❖ በተማሪዎች መጽሐፍ ላይ ያለውን ጠጣ የሚለውን ምንባብ ተማሪዎቹ እንዲያነቡ ያድርጓቸው።

❖ በመጀመሪያ ምንባቡን በግላቸው በለሆሳስ እንዲያነቡ ካደረጉ በኋላ አንቀፁን ለተማሪዎች በማከፋፈል በክፍል ጓደኞቻቸው ፊት እንዲያነቡ ያድርጉ።

❖ ተማሪዎች ሲያነቡ የሚከተሉትን ነጥቦች ከግምት እንዲያስገቡ ሰሌዳ ላይ ይፃፉላቸው፡

- ሲያነቡ የክፍል ጓደኞቻቸውን በዓይናቸው እንዲቃኙ፤
- የምንባቡን የሐሳብ ፍሰት እንዲጠብቁ፤
- የሚያነቡትን መፅሐፍ በተመጠነ ርቀት እንዲይዙ፤
- ምንባቡን በጣታቸው እንዳይጠቁሙ… ያድርጉ፡፡

❖ በንባብ ጊዜ የሚሰሩ ጥያቄዎችን ምላሽ ይሰጡ ዘንድ ያበረታቷቸው፡፡

❖ ተማሪዎች ጠጣ የሚለውን ምንባብ በታዘዘው መንገድ አንብበው ሲጨርሱ ከምንባቡ የተረዱትን ሐሳብ ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡

## አንብቦ መረዳት

❖ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን በምንባቡ መሰረት እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡

❖ ለሰጡት ምላሽም እርማት ይስጧቸው፡፡

### የተግባር ፩ መልስ

4. ሐሰት
5. ሐሰት
6. ሐሰት

## ቃላት

### ተግባር ፩

- ተማሪዎች በመማሪያ መፅሃፋቸው ላይ ያሉትን በሰንጠረዥ ውስጥ ተዘበራርቀው የተቀመጡትን ፊደላት በመጠቀም ቃላትን እንዲመሰርቱ ይደግፏቸው፡፡
- ምሳሌ በመስጠት ተግባሩን ተረድተው እንዲሰሩ ያድርጉ፡፡
- በሚከተለው መልኩ እርማት ይስጧቸው፡፡

| የተዘበራረቁ ፊደላት | የተመሰረቱ ቃላት | |
|---|---|---|
| ድ ዝ ል ጣ ሮ<br>ብ ን በ ሆ ጠ<br>ዋ ር ላ ቀ ጅ<br>ኩ ጆ ኔ ነ ዝ<br>ያ ጭ አ ሳ | ጠጣ | አንበሳ |
| | ድኩላ | ዋልያ |
| | ዝንጀሮ | ቀበሮ |
| | ቀጭኔ | ነብር |
| | ድብ | ጅብ... |

## ተግባር ፪

መምህር፡-

- በተማሪ መፅሃፍ ውስጥ ተግባር ፪ ላይ የቀረቡትን ፊደላት በመጠቀም ሌሎች አዳዲስ ቃላትን እንዲመሰርቱ ይደግፏቸው፡፡
- ሌሎች ተጨማሪ ተግባርም ይስጧቸው፡፡
- ለሰጡት ምላሽም እርማት ይስጧቸው፡፡
- ተጨማሪ የክፍልና የቤት ስራ ይስጧቸው፡፡

## የተግባር ፪ መልስ

| | |
|---|---|
| ከ | ከበሮ፣ ከረሜላ፣ ከረቫት... |
| ቀ | ቀበሮ፣ ቀበሌ፣ ቀን |
| መ | መስኮት፣ መኪና፣ መፅሐፍ |
| አ | አባት፣ አሳ፣ አስኳል |
| ደ | ደሴት፣ ደብተር፣ ደርዘን |

(ሌሎች ቃላትን እንዲመሰርቱ ያበረታቷቸው፡፡)

## አቀላጥፎ ማንበብ

መምህር፦

- “ጦጣ” የሚለውን ምንባብ አቀላጥፈው እንዲያነቡ ይደግፏቸው።
- ተማሪዎች ሲያነቡ፦
    - ደቂቃ በመመዝገብ ለውጣቸውን ይከታተሉ..
    - በሚከተለው ሰንጠረዥ መሰረት አቀላጥፎ ማንበቡን እንዲከውኑ ያስተባብሯቸው።

| የመገምገሚያ መስፈርት | | በመጀመሪያ ንባብ | በሁለተኛ ንባብ |
|---|---|---|---|
| ሀ. | በስህተት የተነበቡ ፊደላት ብዛት | | |
| ለ. | ተነጥለው የተነበቡ ቃላት ብዛት | | |
| ሐ. | በንባብ ጊዜ የተደገሙ ቃላት ብዛት | | |
| መ. | ተገቢ እረፍት ያልተደረገባቸው ስርዓተ ነጥቦች ብዛት | | |
| ድምር | | | |

## ጽሕፈት

### ተግባር ፬

መምህር፦

- በተማሪዎች መማሪያ መፅሃፍ ላይ በተቀመጠው ትዕዛዝ መሰረት የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች በሰሌዳው ላይ ይፃፉላቸውና ተማሪዎቹም ወደ ደብተራቸው በማስፈር ተገቢ ስርዓተ ነጥቦችን እንዲያሟሉ ያድርጉ፡
- ሲፅፉ በቅንፍ ውስጥ ያለው መልስ ስለሆነ ይለፉት

1. በግ ፀጉራማ የቤት እንስሳ ነው(።)
2. ንብ ማር ትሰራለች(።)
3. አህያ ለማዳ እንስሳ ነች(።)
4. ነብር የት አገር ይገኛል(?)
5. ምስጋናው ውሻ ሲጮህበት እናቴ ድረሽ ብሎ ጮኸ(!)

## የማጠቃለያ ተግባር

### ተግባር ፩

መምህር፡-

- በመማሪያ መፅሃፋቸው ላይ ከቀረቡ ልዩ ልዩ ተግባራት ውስጥ ፅሁፍን አንብበው የተጠየቁትን መመለስ ነው፤ይህንን ለማሰራት ፅሑፉን አንብበው መልሱን ከምክንያት ጋር እንዲሰጡ ማድረግ፡፡
- ሌሎች ልብ አንጠልጣይና አመራማሪ ታሪኮችን በመስጠት እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡
- የልዩ ፍላጎት ተማሪዎችንም በአማከለ(በአካተተ) መንገድ ተግባራቱን ያሰሯቸው፡፡
- እርማት ይስጧቸው፡፡

### ተግባር ፪

በመማሪያ መፅሐፍ ላይ እንደተቀመጠው ተማሪዎች የተለያዩ ምንጮችን በማገናዘብ ስለ አንድ ቤት እንስሳ ባህርይ እና ሁኔታ ፅፈው ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያነቡ ያበረታቷቸው፡፡

### ተግባር ፫

መምህር፡-

- በመማሪያ መፅሃፍ በተግባር ፫ ላይ የቀረበውን ተግባር በትእዛዙ መሰረት እንዲሰሩ ያድርጉ፡፡

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ዶሮ | ድኩላ | ድመት | ላም | የሜዳ አህያ |
| ሰጎን | በሬ | ቀበሮ | ዝሆን | በግ |

| የቤት እንስሳት | የዱር እንስሳት |
|---|---|
| ዶሮ | ቀበሮ |
| በሬ | ሰጎን |
| ድመት | ድኩላ |
| ላም | ዝሆን |
| በግ | የሜዳ አህያ |

- እነዚህን ትግበራዎች ተማሪዎች እንዲተገብሩ በማድረግ የተማሪዎችን ክህሎት ይፈትሹ፡፡
- ወደኋላ የቀሩ ተማሪዎች ካሉ በተለያዩ ተግባራት እንዲያዳብሩ እገዛ ያድርጉላቸው፡፡

# አማርኛ ቋንቋ(የመጀመሪያ) ሁለተኛ ክፍል አንደኛ መንፈቅ አመት መርኃ ትምህርት

**ምዕራፍ አንድ፡- ልብስ (18 ክፍለጊዜ)**

**የሚጠበቀው ውጤት**

**ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች:**

- ያዳመጡትን ምንባባብ አጠቃላይ ሃሳብ ይለያሉ
- ከተሰጣቸው ጽሁፍ ውስጥ ዋናውን ሃሳብ ይለያሉ
- ለተለመዱ ቃላት ፍቺ ይሰጣሉ
- ባለሶስት ሆሄ ቃላትን ያጣምራሉ ይነጥላሉ
- ሆሂያትን አቀናጅተው ይጽፋሉ

| ብቃት | ይዘት | የመማር ስልቶችና መርጃ መሳሪያ | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ➢ ያዳመጡትን ጽሁፍ አጠቃላይ ሃሳብ ይለያሉ<br>➢ ከተሰጣቸው ጽሁፍ ውስጥ ዋናውን ሃሳብ ይለያሉ<br>➢ ለተለመዱ ቃላት ፍቺ ይሰጣሉ<br>➢ ባለሶስት ሆሄ ቃላትንያጣምራሉ ይነጥላሉ<br>➢ ሆሂያትን | ➢ **ማዳመጥና መናገር**<br>➢ **የንግግር ድምጽ ግንዛቤ**<br>➢ **የትዕምርት ድምጽ ግንዛቤ**<br>➢ **የቃላት ጥናት፡-** የተለመዱ ቃላት (ትምህርታዊ)<br>➢ **ማንበብ፡-** ፍጥነት፣ትክክልኝነት፣ አገላለጽ፣መረዳት<br>➢ **የጽህፈት ትክክለኝነት** | **መምህር** የእለቱን የትምህርት ርእስ ያስተዋውቁ፡፡ተማሪዎች ከሚያዳምጡት ምንባብ ላይ የሚመልሱትን የተወሰኑ ጥያቄዎችን በጥቁር ሰሌዳው ላይ ይጻፉላቸው፡፡<br>**መምህር** የእለቱን የትምህርት ርእስ ያስተዋውቁና በተለመዱ ቃላት ላይ ውይይት ያድርጉ፡፡ መምህር ምንባቡን ድምጾትን ከፍ አደርገው ያንብቡላቸው፡፡ በመጽሃፋቸው ላይ የሚገኘውን የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን ያሰሩ፡፡<br>**ማጣመር እና መነጠል**<br>ተማሪዎች በቃል ውስጥ ያሉ ሆሂያትን በመነጣጠል ያንብቡ ፡፡ በፍጥነት እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡( መምህር ቃላትን በማጣመር እና ድምጾችን በመነጣጠል ያሳዩአቸው)<br>ተማሪዎች ቃላትን እና በቃሉ ውስጥ ያሉ ፊደሎችን ድምጻቸውን ከፍ | ➢ የጽሁፍና የቃል ጥያቄ መጠየቅ<br>➢ አካላዊ ምላሽ<br>➢ ተማሪዎች ለሚያሳዩት አካላዊጥያቄ በተናጠል ምላሽ መስጠት<br>➢ ኢ-መደበኛ ቁጥጥር<br>➢ ምልከታ<br>➢ እይታዊ |

| ብቃት | ይዘት | የመማር ስልቶችና መርጃ መሳሪያ | ምዘና |
|---|---|---|---|
| አቀናጀተው ይጽፋሉ | ➢ **ድምጸት** | አድርገው ይጥሩ<br>**መስተካከል**<br>*ሀ.* **ማጥፋት**<br>**ተማሪዎች** ቃል ያዳምጡና የመጀመሪያውን ሆሄ አጥፍተው እንዲሉ ያድርጉ<br>**ለ.መጨመር**<br>**ተማርዎች** ቃል ያዳምጡና በመቀያየር ፊደል ወይም ድምጽ ይጨምሩ። ተማሪዎች ያዳመጡና ሆሂያቱን በመቀያየር ሌላ ቃል ይመስርቱ።(ሆሄ የተቀረጸባቸው ስእሎች፣ፍላሽ ካርድ፣ ባለቀለም ወረቀት፣ ቅርቃቅጽ፣ካርቶን ፣ ጥቁር ሰሌዳ ወዘተ. ይጠቀሙ)<br>**ጽሁፍን ማገናኘት**<br>**መምህር** በስእል የቀረቡ ጽሁፎችን ስእለሁን ከጽሁፉ በማገናኘት ያንብቡላቸው። ተማሪዎችም ስእላዊ ጽሁፉን ስእሉን ከጽሁፉ ጋር እያዘመዱ ማንበብ ይለማመዱ።(ሆሄ የተቀረጸባቸው ስእሎች፣ፍላሽ ካርድ፣ ባለቀለም ወረቀት፣ ቅርቃቅጽ፣ካርቶን ፣ ጥቁር ሰሌዳ ወዘተ. ይጠቀሙ)<br>**የተለመዱ ቃላት**<br>ለተለመዱ ቃላት በፍጥነት ምላሽ የመስጠት አቅምን ለማዳበር ይለማመዱ። የቃላቱን አውዳዊ ፍችና ከአውድ ውጪ ያለውን ይለዩ።<br>**የቃል ጽህፈት**<br>**መምህር** ቃላትን በምልክት ይንገሩዋቸው ተማሪዎች በትክክል ይጻፉ።ተማሪዎች የሚያዳምጡትን ቃላት በትክክል ይጻፉ | ውክልና<br>➢ ሚና በመቀያየር ሃላፊነት መውሰድ<br>➢ ማጠቃለያ ውጤት<br>➢ አቀራረብ<br>➢ ስልታዊ አቀራረብ<br>➢ የጽሁፍና የቃል ጥያቄ መጠየቅ |

| ብቃት | ይዘት | የመማር ስልቶችና መርጃ መሳሪያ | ምዘና |
|---|---|---|---|
| | | **የግድግዳ ላይ ቃላት**<br>መምህር ቃላትን በመጻፍ በግድግዳ ላይ ይለጥፉላቸው። ተማሪዎች በግድግዳ ላይ የተለጠፈውን ቃል በመመልከት ከፍቺው ጋር ያዛምዱ።<br>**ደጋግሞ ማንበብ**<br>**ተማሪዎች** ደጋግመው ያንብቡ ግብረመልስ ከመምህሩ ፣ከጓደኞቻቸው እና ከቤተሰብ ይሰጣቸው<br>**በሰአት የተገደበ ደጋግሞ ንባብ**<br>**ተማሪዎች** አጫጭር ጽሁፎችን ሰአት ተይዞላቸው ያንብቡ፣ በድጋሚ በማንበብ የንበብ ፍጥነታቸው መሻሻሉን ሰአታቸውን በቻርት ላይ በመመዝገብ ይከታተሉ<br>**ድምጽን ከሆሄ ማዛመድ፣** ቃላት፣አረፍተ ነገር<br>**ስርአተ ነጥብ**<br>አገላለጽ ማሳደግ፣ መምህር ሰለሰርአተ ነጥብ ጠቃሜታ በግልጽ ውይይት ያድርጉ፣ ምልክቶች እንዴት ስሜትን እና አገላለጾችን አጉልተው እንደሚገልጹ ያሳዩ።<br>ተማሪዎችን በጥንድ ያስቀመጧቸውን ስርአተ ነጥብ ያለበት አጭር ጽሁፍ ይስጧቸው(አራት ነጥብ፣የጥያቄ ምልክት) ከዛ ሰርአተ ነጥቦቹን የስወግዱ። ተማሪዎቹን በመቀያየር ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ያንብቡ። መምህር እነዚህን ጥያቄዎች ይጠይቋቸው ያለ ስርአተ ነጥብ ማንበብ ቀላል ነው ከባድ? ለምን ይመስላችኋል ?የስርአተ ነጥብ አገልግሎት ምን ይመስላችኋል ?ምን ይጠቅሙናል? በመቀጠል በጥንድ ሆነው አራት ነጥብ ያስገቡ።በመቀጠል ለክፍሉ ተማሪዎች በጠቅላላ | |

| ብቃት | ይዘት | የመማር ስልቶችና መርጃ መሳሪያ | ምዘና |
|---|---|---|---|
| | | ድምጸን ከፍ አድርገው በማንበብ ግብረ መልስ ይስጡ ወይም ጽሁፉን በጥቁር ሰሌዳ ላይ በመጻፍ ተማሪዎች እየወጡ ስርአተ ነጥቦችን ያስቀምጡ፡፡<br>**የቡድን ጽህፈት**<br>**መምህር** ምሳሌ በመስጠት እና በማመቻቸት ተማሪዎች በቡድን ታሪክ ይጻፉ | |

**ምዕራፍ ሁለት ፡- ወቅቶች(18ክፍለ ጊዜ)**

**የሚጠበቀው ውጤት**

**ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-**

- ጽሁፉን በማዳመጥ የተለየውን ሃሳብ ያወጣሉ
- የምንባቡን ይዘት በቃላቸው ይናገራሉ
- ከወቅት ጋር ለተገናኙ ቃላት ፍቺ ይሰጣሉ
- ድምጾችን ያጣምራሉ ይነጥላሉ
- ባለ አራት ፊደል ተዘውታሪ ቃላትን ይጽፋሉ
- አራት ነጥብን ይለያሉ

| ብቃት | ይዘት | የመማር ስልትና መርጃ መሳሪያ | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ➢ ጽሁፉን በማዳመጥ ዋና ሃሳብ ይለያሉ<br>➢ የምንባቡን ይዘት በቃላቸው ይናገራሉ<br>➢ ለቃላት ፍቺ ይሰጣሉ<br>➢ ከምንባብ ለወጡ | ➢ **ማዳመጥና መናገር**<br>➢ **የንግግር ድምጽ ግንዛቤ**<br>➢ **የትዕምርት ድምጽ ግንዛቤ**<br>➢ **የቃላት ጥናት፡-** የተለመዱ ቃላት(ትምህርታዊ)<br>.ያቃላት እድገት | **መምህር** ተማሪዎችን ስለርእሱ የቀደመ እውቀታቸውን በመጠየቅ ያነቃቁዋቸው፡፡ ከሚያዳምጡት ምንባብ የተወሰነውን ሃሳብ ይንገሯቸው ተማሪዎችም ያዳምጡና የጎደለወን ሃሳብ ያሟላሉ ፡፡ተማሪዎች ከወቅት ጋር የተገናኙ ቃላትን ይለዩ( ምሳሌ፡- የሳምንቱ ቀናት፣የአመቱ ወራት፣ወቅቶች ክረምት፣በጋ፣መከር...) ለአከባቢ አየር ንብረት ትኩረት የተለየ ይሰጠው፡፡<br>**ማጣመር እና መነጠል**<br>ተማሪዎች በቃል ውስጥ ያሉ ሆሂያትን በመነጣጠል ያንብቡ ፡፡ በፍጥነት እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡( መምህር ቃላትን በማጣመር እና ድምጾችን | ➢ የጽሁፍና የቃል ጥያቄ መጠየቅ<br>➢ አካላዊ ምላሽ<br>➢ ተማሪዎች ለሚያሳዩት አካላዊጥያቄ በተናጠል ምላሽ መስጠት |

| ብቃት | ይዘት | የመማር ስልትና መርጃ መሳሪያ | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣሉ<br>➢ ድምጾችን ይነጥላሉ ያጣምራሉ ስለትን<br>➢ ስለትንሽ መንደር ይተርካሉ | ➢ **ማንበብ:-** **ፍጥነት፣ትክክለኝነት፣አገላለጽ፣**<br>**መረዳት**<br>➢ **ጽህፈት:-** **ትክክለኝነት**<br>➢ **ድምጸት** | በመነጣጠል ያሳዩአቸው)<br>ተማሪዎች ቃላትን እና በቃሉ ውስጥ ያሉ ሆሂያትን በመነጠል ያንብቡ<br>**መስተካከል**<br>ሀ. **ማጥፋት** ተማሪዎች ቃል ያዳምጡና የመጀመሪያውን ሆሄ አጥፍተው እንዲሉ ያድርጉ<br>ለ.**መጨመር** ተማርዎች ቃል ያዳምጡና በመቀያየር ፊደል ወይም ድምጽ ይጨምሩ፡፡ ተማሪዎች ያዳመጡና ሆሂያቱን በመቀያየር ሌላ ቃል ይመስርቱ :(ሆሄ የተቀረጸባቸው ስእሎች፣ፍላሽ ካርድ፣ ባለቀለም ወረቀት፣ ቅርቃቅጽ፣ካርቶን ፣ ጥቁር ሰሌዳ ወዘተ. ይጠቀሙ)<br>**የተለመዱ ቃላት**<br>ተማሪዎች በፍጥነት በአውድ ውስጥና ከአወድ ውጪ ለይተው አውቅና መስጠት፡፡<br>**በቃል መጻፍ**<br>**ተማሪዎች** ቃላትን በማዳመጥ ቀላትን ለመጻፍ ሙከራ ያደርጋሉ<br>**የግድግዳ ቃላት:-**<br>**መምህር** ቃላት ይጻፍላቸውና ለመርጃነት በግድግዳ ላይ ለጥፉላቸው፡፡<br>**ደጋግሞ በቃል ማንበብ**<br>**ተማሪዎች** ደጋግመው ያንብቡ ግብረመልስ ከመመህሩ ፣ከጓደኖቻቸው እና ከቤተሰብ ይሰጣቸው፡፡<br>**በሰአት የተገደበ ደጋግሞ ንባብ**<br>**ተማሪዎች** አጫጭር ጽሁፎችን ሰአት ተይዞላቸው ያንብቡ፣ በድጋሚ በማንበብ የንባብ ፍጥነታቸው መሻሻሉን ሰአታቸውን በቻርት ላይ | ➢ ኢ-መደበኛ ቁጥጥር<br>➢ ምልከታ<br>➢ እይታዊ ውክልና<br>➢ ሚና በመቀያየር ሃላፊነት መውሰድ<br>➢ ማጠቃለያ ውጤት<br>➢ አቀራረብ ስልታዊ አቀራረብ<br>➢ የጽሁፍና የቃል ጥያቄ መጠየቅ |

| ብቃት | ይዘት | የመማር ስልትና መርጃ መሳሪያ | ምዘና |
|---|---|---|---|
| | | በመመዝገብ ይከታተሉ ።<br>ድምጽን ከሆሄ ማዛመድ፣ ቃላት፣አረፍተ ነገር<br>**የአረፍተ ነገር ለዛ**<br>አንድን አረፈተ ነገር ደጋግሞ ያንብቡ ። በዚህ ወቅት ለተለያዩ ቃላት ትኩረት ይስጡ።<br>**ስርአተ ነጥብ**<br>አገላለጽ ማሳደግ፣ መምህር ስለስርአተ ነጥብ ጠቃሜታ በግልጽ ውይይት ያድርጉ፣እነዚህ ምልክቶች እንዴት ስሜትን እንደሚገልጹና አገላለጽን እንደሚያሳድጉ ያሳዩ።<br>ተማሪዎችን በጥንድ ያስቀምጧቸውና ስርአተ ነጥብ ያለበት አጭር ጽሁፍ ይስጧቸው(አራት ነጥብ፣የጥያቄ ምልክት) ከዛ ሰርዓተ ነጥቦቹን ያስወግዱ።<br>ተመሪዎቹ በመቀያየር ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ያንቡ። መምህር እነዚህን ጥያቄዎች ይጠይቋቸው ያለ ስርአተ ነጥብ ማንበብ ቀላል ነው ከባድ? ለምን ይመስላችኋል ?የስርአተ ነጥብ አገልግሎት ምን ይመስላችኋል ?ምን ይጠቅሙናል? በመቀጠል በጥንድ ሆነው አራት ነጥብ ያስገቡ።በመቀጠል ለክፍሉ ተማሪዎች በጠቅላላ ድምጽን ከፍ አድርገው በማንበብ ግብረ መልስ ይስጡ ወይም ጽሁፉን በጥቁር ሰሌዳ ላይ በመጻፍ ተማሪዎች እየወጡ ስርአተ ነጥቦችን ያስቀምጡ።<br>**የቡድን ጽህፈት** መምህር ምሳሌ በመስጠት እና በማመቻቸት ተማሪዎች በቡድን ታሪክ ይጻፉ | |

**ምእራፍ ሶስት፡- ታሪኮች (18 ክፍለጊዜ)**

**የሚጠበቀው ውጤት**

**ከዚህ ምዕራፍ መጠናቀቅ በኋላ ተማሪዎች፡**

- ያዳመጡት ምንባብ አጠቃላይ ሃሳብ ለይተው ቃላዊ ዘገባ ያቀርባሉ
- ካነበቡት ጽሁፍ ወስጥ አጠቃላይ ሃሳቡን ይጽፋሉ
- በአረፍተነገር ውስጥ አራት ነጥብን ይጠቀማሉ
- ባለአራት ፊደል ተዘውታሪ ቃላትን ይጽፋሉ
- ቃልአጋኖን እና የጥያቄ ምልክትን ይጠቀማሉ

| ብቃት | ይዘት | የመማር ብቃት እና መርጃ መሳሪያ | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ➢ ያዳመጡት ምንባባብ ዋና ሃሳብ ለይተው ቃላዊ ዘገባ ያቀርባሉ<br>➢ ከጽሁፍ ውስጥ አጠቃይ ሃሳብ ይጽፋሉ<br>➢ ቃልአጋኖን እና የጥያቄ ምልክትን ይጠቀማሉ | ➢ **ማዳመጥና መናገር**<br>➢ **የንግግር ድምጽ ግንዛቤ**<br>➢ **የትእምርት ድምጽ ግንዛቤ**<br>➢ **የቃላት ጥናት**፡- የተለነዱ ቃላት(ትምህርታዊ)<br>• የቃላት እድገት<br>• የስያሜ ሃሳብ<br>➢ **ማፍለቅና መረዳት**<br>➢ **ማንበብ፡-** ፍጥነት፣ትክክልኝነት፣አገ | **መምህር** ተማሪዎችን ስለርእሱ የቀደመ እውቀታቸውን በመጠየቅ ያነቃቁዋቸው፡፡ ድምጸን ከፍ አድርገው ያንብቡ ተማሪዎች በቃላቸው ዘገባ ያቅርቡ፡፡መምህር **ተማሪዎችን** ስለርእሱ የቀደመ እውቀታቸውን ይጠይቁ፡፡ ድምጸን ከፍ አድርገው ያንብቡ፡፡ ተማሪዎች በጽሁፍ አጭር መልስ ይስጡ፡፡<br>**መስተካከል** ፡- መምህር ለተማሪዎች ቃላትን እንደሚጨምሩና እንደሚያጠፉ (በድምጸ እና ፊደላት) ይንገሩ፡፡<br>**ሀ.ማጥፋት**<br>ተማሪዎች ቃል ያዳምጡና የመጀመሪያውን ሆሄ አጥፍተው እንዲሉ ያድርጉ<br>**ለ.መጨመር** | ➢ የጽሁፍና የቃል ጥያቄ መጠየቅ<br>➢ አካላዊ ምላሽ<br>➢ ተማሪዎች ለሚያሳዩት አካላዊጥያቄ በተናጠል ምላሽ መስጠት<br>➢ ኢ-መደበኛ ቁጥጥር<br>➢ ምልከታ<br>➢ እይታዊ ውክልና<br>➢ ሚና በመቀያየር ሃላፊነት |

| ብቃት | ይዘት | የመማር ብቃት እና መርጃ መሳሪያ | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ➢ ባላራት ፊደል ተዘውታሪ ቃላት ይጽፋሉ | ላለጽ፣ መረዳት<br>➢ **ጽህፈት፡- ትክክለኝነት**<br>➢ **ድምጸት** | **ተማሪዎች** ቃል ያዳምጡና በመቀያየር ፊደል ወይም ድምጽ ይጨምሩ፡፡<br>**ሐ.መለዋወጥ**<br>**ተማሪዎች** ያዳመጡና ሆሂያቱን በመቀያየር ሌላ ቃል ይመስርቱ፡፡<br>**ማፍለቅ**<br>**መምህር** ቃላትን መስርተው ያሳዩ፣ እያንዳንዱን ድምጽ ይጥሩ ከዚያም ድምጾቹን አጣምረው ይጥሩ፡፡(ድምጽን ከሆሄ አቀናጅተው ይጠቀሙ) ተማሪወችም ድምጾችን መጥራትና ማጣመር ይለማመዱ፡፡ (ሆሄ የተቀረጸባቸው ስእሎች፣ፍላሽ ካርድ፣ ባለቀለም ወረቀት፣ ቅርቃቅጽ፣ካርቶን ፣ ጥቁር ሰሌዳ ወዘተ. ይጠቀሙ)<br>**ጽሁፍን ማገናኘት**<br>**መምህር** በስእል የቀረቡ ጽሁፎችን ስእዕሉን ከጽሁፉ በማገናኘት ያንብቡላቸው፡፡ቃል በመመልከት ከፍቺው ጋር ያዛምዱ፡፡<br>**ደጋግሞ በቃል ማንበብ**<br>**ተማሪዎች** ደጋግመው ያንብቡ ግብረመልስ ከመመህሩ ፣ከጓደኖቻቸው እና ከቤተሰብ ይሰጣቸው ፡፡ተማሪዎች አጫጭር ጽሁፎችን ሰአት ተይዞላቸው ያንብቡ፣ በድጋሚ በማንበብ የንበብ ፍጥነታቸው መሻሻሉን ስአታቸውን በቻርት ላይ በመመዝገብ ይከታተሉ ፡፡ | መውሰድ<br>➢ ማጠቃለያ ውጤት<br>➢ አቀራረብ<br>➢ ስልታዊ አቀራረብ<br>➢ የጽሁፍና የቃል ጥያቄ መጠየቅ |

| ብቃት | ይዘት | የመማር ብቃት እና መርጃ መሳሪያ | ምዘና |
|---|---|---|---|
| | | **አረፍተነገር አነባበብ**<br>አንድን አረፍተነገር በተለያ የአነባበብ ስልት ማንበብ፤በዚህ ጊዜ የተለያዩ ቃለትን ጎላ አድርጎ ማንበብ፡፡<br>ምጽን ከሆሄ ማዛመድ፣ ቃላት፣አረፍተ ነገር<br>**ስርአተ ነጥብ**<br>አገላለጽ ማሳደግ፣ መምህር ሰለሰርአተ ነጥብ ጠቃሜታ በግልጽ ውይይት ያድድርጉ፣እነዚህ ምልክቶች እንዴት ስሜትን እንደሚገልጹና አገላለጽን አንደሚያሳድጉ ያሳዩ፡፡<br>**የቡድን ጽህፈት**<br>**መምህር** ምሳሌ በመስጠት እና በማመቻቸት ተማሪዎች በቡድን ታሪክ ይጻፉ፡፡ | |

**ምዕራፍ አራት ፡- የአትክልት ቦታ (18 ክፍለ ጊዜ)**

**የሚጠበቀው ውጤት**

**ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች:**

- ያዳመጡት ምንባብ ዋናውን ሃሳብ ይለያሉ
- ካነበቡት ጽሁፍ ውስጥ ዋናውን ሃሳብ በጽሁፍ ይገልጻሉ
- ቃልአጋኖን እና የጥያቄ ምልክትን ይለያሉ

| ብቃት | ይዘት | የመማር ስልትና መርጃመሳርያ | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ➢ ያዳመጡት ምንባብ ዋናውን ሃሳብ ይለያሉ<br>➢ ካነበቡት ጽሁፍ ውስጥ ዋናውን ሃሳብ በጽሁፍ ይገልጻሉ<br>➢ ቃልአጋኖን እና የጥያቄ ምልክትን ይለያሉ<br>➢ ከቃል ውስጥ ድምጾችን ይነጥላሉ ያጣምራሉ | ➢ **ማዳመጥና መናገር**<br>➢ **የንግግር ድምጽ ግንዛቤ**<br>➢ **የትእምርት ድምጽ ግንዛቤ**<br>➢ **የቃላት ጥናት:-**<br>የተለመዱ ቃላት (ትምህርዊ<br>- የቃላት እድገት<br>➢ **ማፍለቅና መረዳት** | **መምህር** ተማሪዎችን ስለርእሱ የቀደመ እውቀታቸውን በመጠየቅ ያነቃቁዋቸው። መምህር ምን እነደሚያነቡላቸው የንገሩአቸው። የሚገምቱበት ቻርት ያዘጋጁ። ተማሪዎቹም ከምንባቡ ያገኙትን መረጃ በቻርቱ ለይ ይመዝግቡ።<br>**ማጣመር እና መነጠል**<br>ተማሪዎች በቃል ውስጥ ያሉ ሆሂያትን በመነጣጠል ያንብቡ ። በፍጥነት እንዲያነቡ ያድርጉ። (መምህር ቃላትን በማጣመር እና ድምጾችን በመነጣጠል ያሳዩአቸው)<br>ተማሪዎች ቃላትን እና በቃሉ ውስጥ ያሉ ሆሂያትን በመነጠል ያንብቡ<br>**መስተካከል**<br>**ሀ. ማጥፋት**<br>ተማሪዎች ቃል ያዳምጡና የመጀመሪያውን ሆሄ አጥፍተው እንዲሉ ያድርጉ<br>**ለ.መጨመር**<br>ተማሪዎች ቃል ያዳምጡና በመቀያየር ፊደል ወይም ድምጽ ይጨምሩ። | ➢ የጽሁፍና የቃል ጥያቄ መጠየቅ<br>➢ አካላዊ ምላሽ<br>➢ ተማሪዎች ለሚያሳዩት አካላዊጥያቄ በተናጠል ምላሽ መስጠት<br>➢ ኢ-መደበኛ ቁጥጥር<br>➢ ምልከታ<br>➢ እይታዊ ውክልና<br>➢ ሚና በመቀያየር ሃላፊነት መውሰድ<br>➢ ማጠቃለያ ውጤት |

| ብቃት | ይዘት | የመማር ስልትና መርጃመሳርያ | ምዘና |
|---|---|---|---|
| | ➢ **ማንበብ፡** ፍጥነት፣ትክክልኝነ ት፣አገላለጽ፣ መረዳት<br>➢ **ጽህፈት:-** **ትክክለኝነት**<br>➢ **ድምጸት** | **ሐ.መለዋወጥ**<br>ተማሪዎች ያዳመጡና ሆሂያቱን በመቀያየር ሌላ ቃል ይመስርቱ<br>**ማፍለቅ**<br>**መምህር** ቃላትን መስርተው ያሳዩ፣ እያንዳንዱን ድምጽ ይጥሩ ከዚያም ድምጾቹን አጣምረው ይጥሩ፡፡ (ድምጽን ከሆሄ አቀናጅተው ይጠቀሙ) ተማሪዎችም ድምጾችን መጥራትና ማጣመር ይለማመዱ፡፡ (ሆሄ የተቀረጸባቸው ስእሎች፣ፍላሽ ካርድ፣ ባለቀለም ወረቀት፣ ቅርቃቅጽ፣ካርቶን ፣ ጥቁር ሰሌዳ ወዘተ. ይጠቀሙ)<br>**ጽሁፍን ማገናኘት**<br>**ተማሪዎች** በስእል የቀረቡ ጽሁፎችን ከጽሁፉ ማገናኘት ይለማመዱ<br>**ደጋግሞ በቃል ማንበብ**<br>**ተማሪዎች** ደጋግመው ያንብቡ ግብረመልስ ከመምህሩ ፣ከጓደኖቻቸው እና ከቤተሰብ ይሰጣቸው ፡፡<br>**በሰአት የተገደበ ደጋግሞ ንባብ**<br>**ተማሪዎች** አጫጭር ጽሁፎችን ሰአት ተይዞላቸው ያንብቡ፣ በድጋሚ በማንበብ የንበብ ፍጥነታቸው መሻሻሉን ሰአታቸውን በቻርት ላይ በመመዝገብ ይከታተሉ<br>**አረፍተነገር አነባበብ**<br>አንድን አረፍተነገር በተለያ የአነባበብ ስልት ማንበብ፤በዚህ ጊዜ የተለያዩ ቃለትን ጎላ አድርጎ ማንበብ፡፡<br>ድምጽን ከሆሄ ማዛመድ፣ ቃላት፣አረፍተ ነገር<br>**ስርአተ ነጥብ** | ➢ አቀራረብ. አቀራረብ<br>➢ ስልታዊ አቀራረብ<br>➢ የጽሁፍና የቃል ጥያቄ መጠየቅ |

| ብቃት | ይዘት | የመማር ስልትና መርጃመሳርያ | ምዘና |
| --- | --- | --- | --- |
| | | አገላለጽ ማሳደግ፣ መምህር ስለሰርአተ ነጥብ ጠቃሜታ በግልጽ ውይይት ያድድርጉ፣እነዚህ ምልክቶች እነዴት ስሜትን እንደሚገልጹና አገላለጽን አንደሚያሳድጉ ያሳዩ። <br> **የቡድን ጽህፈት** <br> **መምህር** ምሳሌ በመስጠት እና በማመቻቸት ተማሪዎች በቡድን ታሪክ ይጻፉ | |

**ምዕራፍ አምስት ፡- የአከባቢ ንጽህና አጠባበቅ (18 ክፍለ ጊዜ)**

**የሚጠበቀው ውጤት**

**ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች:**

- ካአዳመጡት ምንባብ ለወጡ ቃላት ፍቺ ይሰጣሉ፡፡
- ከምንባቡ ውስጥ ልዩ የሆነውን ሃሳብ ያወጣሉ፡፡
- ቃልአጋኖን እና የጥያቄ ምልክትን ይለያሉ፡፡
- በነጠላ አረፍተነገሮች መጨረሻ አራትነጥብ ያስገባሉ፡፡

| ብቃት | ይዘት | የመማር ስልቶችና መርጃ መሳሪያ | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ➢ ካአዳመጡት ምንባብ ለወጡ ቃላት ፍቺ ይሰጣሉ<br>➢ ከጽሁፍውስጥ ልዩ የሆነውን ዝርዝር ሃሳብ ይለያሉ<br>➢ ቃልአጋኖን እና የጥያቄ ምልክትን ይለያሉ<br>➢ በነጠላ | ➢ **ማዳመጥና መናገር**<br>➢ **የንግግር ድምጽ ግንዛቤ**<br>➢ **የትዕምርት ድምጽ ግንዛቤ**<br>➢ **የቃላት ጥናት፡-** የተለመዱ ቃላት(ትምህርታ)<br>- የቃላት እድገት<br>- የስያሜ ሃሳብ<br>➢ **ማፍለቅና መረዳት**<br>➢ **ማንበብ፡-** | **መምህር** ተማሪዎችን ስለርእሱ የቀደመ እውቀታቸውን በመጠየቅ ያነቃቁዋቸው፡፡መምህር ምን እንደሚያነቡላቸው ተማሪዎች የሚገምቱበት ቻርት ያዘጋጁ፡፡ ተማሪዎቹም ከምንባቡ የገኙትን መረጃ በቻርቱ ለይ ይመዝግቡ፡፡<br>**ማጣመር እና መነጠል**<br>**ተማሪዎች** በቃል ውስጥ ያሉ ሆሂያትን በመነጣጠል ያንብቡ ፡፡ በፍጥነት እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡( መምህር ቃላትን በማጣመር እና ድምጸችን በመነጣጠል ያሳዩኣቸው)<br>ተማሪዎች ቃላትን እና በቃሉ ውስጥ ያሉ ሆሂያትን በመነጠል ያንብቡ፡፡<br>**መስተካከል**<br>**ሀ. ማጥፋት**<br>**ተማሪዎች** ቃል ያዳምጡና የመጀመሪያውን ሆሄ አጥፍተው እንዲሉ | .የጽሁፍና የቃል ጥያቄ መጠየቅ<br>. አካላዊ ምላሽ<br>. ተማሪዎች ለሚያሳዩት አካላዊጥያቄ በተናጠል ምላሽ መስጠት<br>.ኢ-መደበኛ ቁጥጥር<br>.ምልከታ<br>. እይታዊ ውክልና<br>. ሚና በመቀያየር ሃላፊነት መውሰድ<br>. ማጠቃለያ ውጤት<br>. አቀራረብ. አቀራረብ |

| ብቃት | ይዘት | የመማር ስልቶችና መርጃ መሳሪያ | ምዘና |
|---|---|---|---|
| አረፍተነገሮች መጨረሻ አራትነጥብ ያስገባሉ | ፍጥነት፣ትክክልኝነት፣አገ ላለጽ፣መረዳት<br>➢ **ጽህፈት፡-** ትክክለኝነት<br>➢ **ድምጸት** | ያድርጉ<br>**ሰ.መጨመር**<br>ተማሪዎች ቃል ያዳምጡና በመቀያየር ፊደል ወይም ድምጽ ይጨምሩ፡፡<br>**ሐ.መለዋወጥ**<br>**ተማሪዎች** ያዳመጡና ሆሂያቱን በመቀያየር ሌላ ቃል ይመስርቱ<br>**ማፍለቅ**<br>**መምህር** ቃላትን መስርተው ያሳዩ፣ እያንዳንዱን ድምጽ ይጥሩ ከዚያም ድምጾቹን አጣምረው ይጥሩ፡፡(ድምጽን ከሆሄ አቀናጅተው ይጠቀሙ) ተማሪወችም ድምጾችን መጥራትና ማጣመር ይለማመዱ፡፡<br>**የቃል ጽህፈት**<br>**መምህር** ከግድግዳ ላይ ቃላትን እያዩ ያንብቡ፤ ተማሪዎች አዳምጠው በትክክል ይጻፉ(ሆሄ የተቀረጸባቸው ስእሎች፣ፍላሽ ካርድ፣ ባለቀለም ወረቀት፣ ቅርቃቅጽ፣ካርቶን ፣ ጥቁር ሰሌዳ ወዘተ. ይጠቀሙ)<br>**ጽሁፍን ማገናኘት**<br>**ተማሪዎች** በስእል የቀረቡ ጽሁፎችን ከጽሁፉ ማገናኘት ይለማመዱ<br>**ደጋግሞ በቃል ማንበብ**<br>**ተማሪዎች** ደጋግመው ያንብቡ ግብረመልስ ከመመህሩ ፣ከጓደኖቻቸው እና ከቤተሰብ ይሰጣቸው ፡፡ተማሪዎች በጊዜ የተገደበ አጫጭር ጽሁፎችን ያንብቡ፡፡<br>**የአረፍተ ነገር አነባበብ**<br>አንድን አረፍተነገር በተለያ የአነባበብ ስልት ማንበብ፤በዚህ ጊዜ | . ስልታዊ አቀራረብ<br>.የጽሁፍና የቃል ጥያቄ መጠየቅ |

| ብቃት | ይዘት | የመማር ስልቶችና መርጃ መሳሪያ | ምዘና |
|---|---|---|---|
| | | የተለያዩ ቃለትን ጎላ አድርጎ ማንበብ፡፡<br>ድምጽን ከሆሄ ማዛመድ፣ ቃላት፣አረፍተ ነገር<br>**ስርአተ ነጥብ**<br>አገላለጽ ማሳደግ፣ መምህር ስለሰርአተ ነጥብ ጠቃሜታ በግልጽ ውይይት ያድድርጉ፣እነዚህ ምልክቶች እንዴት ስሜትን እንደሚገልጹና አገላለጽን እንደሚያሳድጉ ያሳዩ፡፡<br>**የቡድን ጽህፈት**<br>**መምህር** ምሳሌ በመስጠት እና በማመቻቸት ተማሪዎች በቡድን ታሪክ ይጻፉ | |

# አማርኛ ቋንቋ (የመጀመሪያ)ሁለተኛ ክፍል ሁለተኛ መንፈቅ ዓመት መርሐ ትምህርት

**ምዕራፍ ስድስት፡- ባህላዊ ሙዚቃ** (18 ክፍለ ጊዜ)

**የሚጠበቀው ውጤት**

**ከዚህ ምዕራፍ መጠናቀቅ በኋላ ተማሪዎች�:-**

- ጽሁፍን አዳምጠው ተዘውታሪ ቃላትን በመጠቀም አረፍተነገር ይመሰርታሉ
- ከሚነበበው ጽሁፍ ተዘውታሪ ቃላትን በመለየት ፍቺ ይሰጣሉ
- የጥያቄ ምልክትና ቃልአጋኖ ይጠቀማሉ
- ቃላትን ከመነሻ ቅጥያቸው ጋር አብረው ይጠራሉ

| ብቃት | ይዘት | የመማር ስልት እና መርጃ መሳሪያ | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ➢ ጽሁፍን አዳምጠው ታሪኩን ያደራጃሉ<br>➢ ከሚያነቡት ጽሁፍ ውስጥ ተዘውታሪ ቃላትን በመለየት ፍቺ ይሰጣሉ<br>➢ ቃልአጋኖ እና የጥያቄ ምልክት ይጠቀማሉ<br>➢ ቃላትን ከቅድመ ቅጥያ ጋር ይጠራሉ | ➢ **ማዳመጥና መናገር**<br>➢ **የንግግር ድምጽ ግንዛቤ**<br>➢ **የትዕምርት ድምጽ ግንዛቤ**<br>➢ **የቃላት ጥናት** የተለመዱ ቃላት . የስም | **መምህር** ተማሪዎችን የቀደመ አውቀታቸውን በመጠየቅ እንዲሳተፉ ያድርጉ:: ጽሁፉን ድምጸን ከፍ በማድረግ ያንብቡ:: ተማሪዎቹን በቡድን ያስቀምጡ::ቢያንስ አንድ ሃሳብ ካዳመጡት ጽሑፍ በደብተራቸው ላይ እንዲጽፉ ያድርጉ:: በተጨማሪም በተናጠል ካዳመጡት ጽሁፍ የያዙትን ሃሳብ በማዋጣት አጭር ጽሁፍ እንዲጽፉ ይጠይቋቸው::<br>**ማጣመርና መነጠል**<br>**ተማሪዎች** በቃል ውስጥ ያሉ ድምጾችን ይጥሩከዚያም ‹‹ እነሱን በፍጥነት የበሏች›› (መምህር ሰርቶ በማሳየት ድምጾችን በማገናኘት ትንንሽ ምእላዶችን ያጣምሩ) እና ምእላዶችን ወይም ድምጾችን በመነጣጠል ነጣጥለው ያሳዩ:: ( ስእል ድምጽ /ሆሄ ወይም የቃላት ካርድ ፣ ባለቀለም ወረቀት፣ካርቶን፣ጥቁር ሰሌዳ ወዘተ..)<br>**መለየት**<br>**ተማረዎች** በተመሳሳይ ድምጽ የሚጀመሩ ወይም የሚጨርሱ ቃላትን | ➢ የጽሁፍና የቃል ጥያቄ መጠየቅ<br>➢ አካላዊ ምላሽ<br>➢ ተማሪዎች ለሚያሳዩት አካላዊ ጥያቄ በተናጠል ምላሽ መስጠት<br>➢ ኢ-መደበኛ ቁጥጥር<br>➢ ምልከታ<br>➢ እይታዊ ውክልና<br>➢ ሚና በመቀያየር ሃላፊነት መውሰድ<br>➢ ማጠቃለያ ውጤት |

| ብቃት | ይዘት | የመማር ስልት እና መርጃ መሳሪያ | ምዘና |
|---|---|---|---|
| | እሳቤ .የቃላት እድገት<br>➢ **ማፍለቀ እና መረዳት**<br>➢ **ማንበብ** በትክክል፣ በፍጥነት እና በጥሩ አገላለጽ መረዳት<br>➢ **ጽህፈት፡-** ትክክለኛነት<br>➢ **ድምጸት** | ይለያያሉ<br>**ምት** /ዜማ<br>**ተማሪዎች** ዜማ የሚሰጡ የቃላት ቤተሰቦችን ያዘጋጃሉ<br>**ቃላት ምስረታ**<br>ተማሪዎች ማፍለቅ ይለማመዱ<br>**የተለመዱ ቃላት**<br>**መምህር** ከጽሁፍ ውስጥ ተዘውታሪ ቃላትን ይለዩ፡፡ተማሪዎች በጣም ተዘውታሪ የሆኑ ቃላትን በፍጥነት መረዳትና ባውስ ውስጥና ከአውድ ውጪ መለየት ይችላሉ<br>**የቃል ጽህፈት**<br>**መምህር** ሁለት በቃል አየተነበበላቸው የሚጻፉ አረፍተነገሮችን ያዘጋጁ፡፡( ተማሪዎች አረፍተነገሮቹ ሲነበቡ ያዳምጣሉ) ከዚያም ለመጻፍ ይሞክራሉ፡፡<br>**የግድግዳ ላይ ቃላት** መምህር አዳዲስ ቃላትን በቁርጥራጭ ወረቀት በመጻፍ በግድግዳ ላይ ይለጥፉላቸው፡፡ተማሪዎችም የተጻፈላቸውን በመመልከት አዳዲስ ቃትን ይማራሉ፡፡<br>**የፊደል አጻጻፍ ዝግጅት**<br>የቃት ካርታ፣ቻርት፣ ቃላት ፍለጋ<br>**የመጽሄት ምላሽ**<br>**ተማሪዎች** የንባብ አቅመን ለመገንባት በመጽሄት ግንኙነት ያድርጉ<br>**ጽሁፍን ማገናኘት**<br>ተማሪዎች ጽሁፍ ከሆሂያት ጋር በማገናኘት ይረዳሉ፡፡ | ➢ አቀራረብ |

| ብቃት | ይዘት | የመማር ስልት እና መርጃ መሳሪያ | ምዘና |
|---|---|---|---|
| | | **በሂደት ማጠናቀቅ(ሂደታዊ ትግበራ)**<br>ማሚቶ ንባብ፣የህብረት ንባብ፣ የትብብር ንባብ፣ ጥንድንባብ ፣ ከሌላ ሰው ጋር ማንበብ እና የጸጥታ ንባብን ማንበብ<br>**በሰአት የተገደበ ደጋግሞ ንባብ**<br>**ተማሪዎች** አጫጭር ጽሁፎችን ሰአት ተይዞላቸው ያንብቡ፣ በድጋሚ በማንበብ የንበብ ፍጥነታቸው መሻሻሉን ሰአታቸውን በቻርት ላይ በመመዝገብ ይከታተሉ<br>**ቁርጥራጭ (ክፍልፋይ)**<br>ሀረግ በሃረግ ንባብን መጠቀም<br>**ግመታ**<br>**መምህር** ተማሪዎች ፍንጮችን አይተው ቀጣዩን እንዲገምቱ ያድርጉ<br>**ጥያቄ**<br>**ለተማሪዎች** ጥያቄ የሚያዘጋጁበትን ግዜ ይጧቸው<br>**እተቀያየሩ ድምጽን ከፍ አድርጎ ማንበብ (መስተጋብራዊ የጮክታ ንባብ)**<br>**መምህር** አጭር ታሪክ ያዘጋጁ፡፡ተማሪዎች በቡድን የታሪኩን ክፍሎች ይከፋፈሉና ታሪኩን በማንበብ ይሳተፉ ፡፡ አንዱ ቡድን ድምጹን ከፍ አድርጎ ሲያነብ የተቀረው ደግሞ ዋናውን ሃሳብ ይስጥ፡፡<br>**ደጋግሞ በቃል ማንበብ**<br>**ተማሪዎች** ደጋግመው ያንብቡ ግብረመልስ ከመመህሩ ፣ከጓደኖቻቸው እና ከቤተሰብ ይሰጣቸው ፡፧<br>**በሰአት የተገደበ ንባብ**<br>ተማሪዎች አጫጭር ጽሁፎችን ደጋግመው ያንብቡ፣ ሰአት | |

| ብቃት | ይዘት | የመማር ስልት እና መርጃ መሳሪያ | ምዘና |
|---|---|---|---|
| | | ይያዝላቸው፣ የንባብ ፍጥነታቸው ለውጥ በቻርት ላይ ይመዝገብ<br>**የአርፍተነገር ደጋግሞ ማንበብ፡-** አንድ አረፍተነገር ይነበ<br>**የማጠቃለያ ተግባራት**<br>ማጠቃላል ይለማመዱ እና ከጽሁፍ ያገኙትን ዋና ዋና መረጃዎችን ማዋሃድን የለማመዱ፡<br>**ስርአተ ነጥብ**<br>መምህር ስርአተ ነጥቦች የመግለጽ ችሎታቸው እንዲያድግ ለማገዝ በስርአተ ነጥብ ላይ ግልጽ ውይይት እንዲካሄድ ያድርጉ፡፡ስርአተ ነጥቦች ለውጠየታማ አገላለጽ ሚናቸው ከፍተኛ መሆኑን አበክረው ይግለጹ፤ያሳዩ፡፡<br>**የቡድን ጽህፈት**<br>**መምህር** አርአያ በመሆን ተማሪዎች አንድ ተረክ በቡድን እንዲጽፉ ያመቻቹ፡፡ | |

**ምዕራፍ ሰባት፡-መልካም ስነምግባር (18 ክፍለ ጊዜ)**

**የሚጠበቀው ውጤት**

**ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች ፡-**

- ካዳመጡት ጽሁፍ ውስጥ አዳዲስ ቃላትን በመጠቀም ነጠላ አረፍተነገር ይመሰርታሉ
- ከምንባቡ ለወጡ ቃላት አውዳዊ ፍቺ ይሰጣሉ
- ተመሳሳይ ቅጥያ ያላቸውን ቃላት ይዘረዝራሉ
- በተገቢው ፍጥነት አጫጭር ታሪኮችን ያነባሉ
- የተሰጣቸውን ቃላት በትክክል ይጽፋሉ

| ብቃት | ይዘት | የመማር ስልቶችና መርጃ መሳሪያ | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ➢ ካዳመጡት ጽሁፍ ውስጥ አዳዲስ ቃላትን በመጠቀም ነጠላ አረፍተነገር ይመሰርታሉ<br>➢ ከምንባቡ ለወጡ ቃላት አውዳዊ ፍቺ ይሰጣሉ<br>➢ ተመሳሳይ ቅጥያ ያላቸውን ቃላት | ➢ **ማዳመጥና መናገር**<br>➢ **የንግግር ድምጽ ግንዛቤ**<br>➢ **የትዕምርተ ድመጽ ግንዛቤ**<br>➢ **የቃላት ጥናት** የተለመዱ | **መምህር** ስለርእሱ የቀደመ እውቀታቸውን ተማሪዎችን በማሳተፍ ይጠይቁ፡፡ ጥቂት ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡ ድምጽን ከፍ አድርገው ያንብቡ ፡፡ **ተማሪዎችን** በቡድን ያስቀምጡ ፡፡ ካዳመጡት ጽሁፍ ውስጥ በደብተራቸው ላይ ቢያንስ አንድ ሃሳብ በመያዝ አጭር ጽሁፍ ይጻፉ፡፡<br>**ምት**<br>ተማሪዎች ተመሳሳይ የቃላት ቤተሰቦችን በዜማ ያንብቡ<br>**ቃላት ምስረታ**<br>ተማሪዎች ቃላትን መጻፍ ይለማመዱ<br>**ከአገባቡ ጋር ማገናኘት**<br>**ተማሪዎች** ምለክቶቹን በማንበብ ከጽሁፉ ጋር ያገናኙ፡፡ ስእሎች፣ የቃላት ወይም የፊደላት/ድምጾች ካርድ፣ ባለቀለም ወረቀት ፣ቅርጻቅርጽ፣ካርቶን ፣ጥቁር ሰሌዳ | ➢ የጽሁፍና የቃል ጥያቄ መጠየቅ<br>➢ አካላዊ ምላሽ<br>➢ ተማሪዎች ለሚያሳዩት አካላዊ ጥያቄ በተናጠል ምላሽ መስጠት<br>➢ ኢ-መደበኛ ቁጥጥር<br>➢ ምልከታ |

| ብቃት | ይዘት | የመማር ስልቶችና መርጃ መሳሪያ | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ይዘረዝራሉ<br>➢ በተገቢው ፍጥነት አጫጭር ታሪኮችን ያነባሉ<br>የተሰጣቸውን ቃላት በትክክል ይጽፋሉ | ቃላት (ትምህርታዊ)<br>- የሰያሜ ጽንሰ ሃሳብ<br>➢ **ማፍለቅና መረዳት**<br>➢ **መነጠልና ማጣመር**<br>➢ **የማንበብ** ፍጥነት ፣ትክክለኛነት፣ አገላለጽ፣ መረዳት<br>➢ **በትክክል መጻፍ**<br>➢ **ድምጸትን የመገንዘብ ችሎታ** | ወዘተ.) ይጠቀሙ፡፡<br>**የግድግዳ ላይ ቃላት**<br>ተማሪዎች አዳዲስ ቃላትን በቁርጥራጭ ወረቀት ላይ ይጻፉ፤ ለመርጃነት በግድግዳ ላይ ይለጥፉ፡፡<br>**የፊደል አጣጣል ማቀናበር** የቃላት ካርታ፣የስሜት ገበታ፣ የቃላት አሰሳ<br>**የተለመዱ ቃላት**<br>በጣም ተለመዱ ቃላትን በአውድ ውስጥ ከአወድ ውጪም ፍቺያቸውን በፍጥነት ይለዩ፡፡<br>**በሂደት ማጠናቀቅ፡-** ማሚቶ፣ የህብረት ንባብ፣ የጥንድ ንባብ፣ የዝምታ ንባብ **በሰአት የተገደበ ንባብ**<br>አንድን ምንባብ ሰዐት ይዞ ሁለት ጊዜ ማንበብ እና ለውጡን በቻርት ላይ መመዝገብ፤<br><br>**ቁርጥራጭ (ክፍፍል)** ፡- ተማሪዎች ሀረጋትን ይጠቀሙ፡፡<br>**በርካታ እድሎችን ማቅረብ**<br>የቀደመ እውቀታቸውን ማሳደግ<br>**መተንበይ**<br>ፍንጭ አይተው የሚነበበው ምንባብ ስለምን እንደሆነ ይተነብያሉ<br>**ጥያቄ** ለተማሪዎች ጥያቄ መመስረቻ ጊዜ ይስጧቸው<br>**ቦታ በመቀያየር ድምጽን ከፍ አድርጎ ማንበብ**<br>ተማሪዎች በሚነገረው ታሪክ ላይ ተሳታፊ ይሁኑ<br>(ስእሎች፣ የቃላት ወይም የፊደላት/ድምጾች ካርድ፣ ባለቀለም ወረቀት፣ | ➢ እይታዊ ውክልና<br>➢ ሚና በመቀያየር ሃላፊነት መውሰድ<br>➢ ማጠቃለያ ውጤት<br>➢ አቀራረብ. አቀራረብ |

| ብቃት | ይዘት | የመማር ስልቶችና መርጃ መሳሪያ | ምዘና |
|---|---|---|---|
| | | ቅርጻቅርጽ፣ ካርቶን ፣ጥቁር ሰሌዳ ወዘተ.ይጠቀሙ)<br>**የቃል ጽህፈት**<br>**መምህር** ሶስት ተራ አረፍተነገር በቃል ይመስረቱላቸው (ተማሪዎች ያዳምጡ) በአረፍተነገር ውስጥ ያሉትን እያንዳንዱን ቃል በትክክል ይጻፋ፡፡ ተማሪዎች ያዳምፁ፡፡(ቃላት፣አረፍተነገር እና የግድግዳ ቃላት) ከዚያም ቃላትን በትክክል ይጽፋሉ፡፡<br>**ደጋግሞ በቃል ማንበብ**<br>**ተማሪዎች** ምንባብን ደጋግመው ያንብቡ፣ ለንባብ ጊዜ ይስጧቸው ለውጡን በቻርት ላይ ይጻፉ<br>**የ አረፍተነገር አነባበብ** ፡- አንድ አረፍ ተነገር ያንብቡ<br>ድምጽን ከሆሄ ማዛመድ፣ ቃል ፣ አረፍተነገር<br>**ስርአተ ነጥብ**<br>አገላለጽን ማሳደግ፣መምህር ስለስርአተ ነጥብ ቀለል በለ መልኩ ይግለጹላቸው<br>**በርከት ያለጊዜ**<br>በዚህ ግዜ ለተለያዩ ቃላት ትኩረት ይስጡ<br>**የቡድን ጽህፈት**<br>መምህር ምሳሌ በመሆን እና በማማቻቻ በቡድን አጫጭር ታሪኮችን እንዲጽፉ ያድርጉ፡፡ | |

**ምዕራፍ ስምንት ፦ የምግብ አዘገጃጀት (18 ክፍለ ጊዜ)**

**የሚጠበቀው ውጤት**

**ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች ፦**

- ካዳመጡት ምንባብ ጽሁፍ ውስጥ ዋናውን መልእክት ያደራጃሉ
- ካዳመጡት ምንባብ ለቃላት ተመሳሳይ ፍቺ ይሰጣሉ
- ከምንባብ ውስጥ ተራ አረፍተነገሮችን ይለያሉ
- ተመሳሳይ ቅጥያ ያላቸውን ቃላት ይዘረዝራሉ
- አጫጭር ታሪኮችን አቀላጥፈው ያነባሉ

| ብቃት | ይዘት | የመማር ስልቶች እና መርጃ መሳሪያ | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ➢ ካዳመጡት ምንባብ ጽሁፍ ውስጥ ዋናውን መልእክት በሌላ ቅርጽ ያደራጃሉ<br>➢ ካዳመጡት ምንባብ ለቃላት ተመሳሳይ ፍቺ ይሰጣሉ<br>➢ ከምንባብ ውስጥ ተራ | ➢ **ማዳመጥና መናገር**<br>➢ **የንግግር ድምጽ ግንዛቤ**<br>➢ **የትዕምርተ ድመጽ ግንዛቤ**<br>➢ **የቃላት ጥናት** | **መምህር** የጽሁፍ አደረጃጀት ሁሉንም ደረጃዎች ያሳዩአቸው። ጽሁፉን በቃል ያንብቡና ተማሪዎች የሂደት ግራፉን እንዲሞሉ ያድርጉ።<br>**ማጣመር እና መነጠል**<br>**መምህር** በምንባብ ውስጥ ያሉ ቅጥያ ያላቸውን ቃላት ይለዩ እና በመነጠልና በማጣመር ያሳዩአቸው። ተማሪዎችም ከምንባቡ ውስጥ የወጡ ቅጥያ ያለቸውን ቃት አስታውሰው ይለያሉ።<br>**መለየት**<br>መምህር በመጨረሻ እና መጀመሪያ ላይ የሚመጡ ድምጾችን በመለያየት ያሳዩ ።<br>**ምት** | ➢ የጽሁፍና የቃል ጥያቄ መጠየቅ<br>➢ አካላዊ ምላሽ<br>➢ ተማሪዎች ለሚያሳዩት አካላዊጥያቄ በተናጠል ምላሽ መስጠት<br>➢ ኢ-መደበኛ ቁጥጥር<br>➢ ምልከታ |

| ብቃት | ይዘት | የመማር ስልቶች እና መርጃ መሳሪያ | ምዘና |
|---|---|---|---|
| አረፍተነገሮችን ይለያ<br>➢ ተመሳሳይ ቅጥያ ያላቸውን ቃላት ይዘረዝራሉ<br>➢ አጫጭር ታሪኮችን አቀላጥፈው ያነባሉ | የተለመዱ ቃላት (ትምህርታዊ)<br>- የስያሜ ጽንሰ ሃሳብ<br>➢ **ማፍለቅና መረዳት**<br>➢ **መነጠልና ማጣመር**<br>➢ **የማንበብ ፍጥነት**<br>፣ትክክለኛነት፣አገላለጽ፣ መረዳት<br>➢ **በትክክል መጻፍ**<br>➢ **ድምጸትን የመገንዘብ ችሎታ** | ተማሪዎችተመሳሳይ የቃላት ቤተሰቦችን በዜማ ያንብቡ።<br>**የቃላት ምስረታ**<br>ተማሪዎች ቃላትን መጥራት ይለማመዳሉ።<br>**የግድግዳ ላይ ቃላት**<br>ተማሪዎች አዳዲስ ቃላትን በቁርጥራጭ ወረቀት ላይ ይጻፉ ለመርጃነት በግድግዳ ላይ ይለጥፉ።<br>**ከአገባበብ ጋር ማገናኘት**<br>**ተማሪዎች** ምልክቶቹን በማንበብ ከጽሁፉ ጋር ያገናኙ። ስእሎች፣ የቃላት ወይም የፊደላት/ድምጾች ካርድ፣ ባለቀለም ወረቀት ፣ቅርጻቅርጽ፣ካርቶን ፣ጥቁር ሰሌዳ ወዘተ.) ይጠቀሙ።<br>**በሂደት ማጠናቀቅ፡-** ማሚቶ፣ የህብረት ንባብ፣ የጥንድ ንባብ፣ የዝምታ ንባብ<br>**ደጋግሞ በቃል ማንበብ** ተማሪዎች ምንባቡን ደጋግመው ያንብቡ፣ ለንባብ ጊዜ ይስጧቸው ለውጡን በቻርት ላይ ይጻፉ<br>**ቁርጥራጭ (ክፍፍል)** ፡-ተማሪዎች ሀረጋትን ይጠቀሙ።<br>**መተንበይ** ፍንጭ አይተው የሚነበበው ምንባብ ስለምን እንደሆነ ይተነብያሉ።<br>**ጥያቄ** ለተማሪዎች ጥያቄ መመስረቻ ጊዜ ይስጧቸው። | ➢ እይታዊ ውክልና<br>➢ ሚና በመቀያየር ሃላፊነት መውሰድ<br>➢ ማጠቃለያ ውጤት<br>➢ አቀራረብ<br>➢ ስልታዊ አቀራረብ |

| ብቃት | ይዘት | የመማር ስልቶች እና መርጃ መሳሪያ | ምዘና |
|---|---|---|---|
| | | **ቦታ በመቀያየር ድምጽን ከፍ አድርጎ ማንበብ**<br>ተማሪዎች በሚነገረው ታሪክ ላይ ይሳተፉ።<br>**የተለመዱ ቃላት**<br>**ተማሪዎች** የቃል ክፍሎችን ተጠቅመው አዳዲስ ቃላትን መጥራት ይለማመዳሉ ወይም አዳዲስ ቃለትይመሰርታሉ<br>**ደጋግሞ በቃል ማንበብ**<br>ተማሪዎች ምንባብን ደጋግመው ያንብቡ፣መምህር፣ ገደኛ እና በተሰብ ግብረ መልስ ይስጧቸው<br>**በሰአት የተገደበ የቃል ንባብ**<br>ተማሪዎች አጭር ምንባብ በተደጋጋሚ ያንብቡ፣ንባባቸው ሲያከናውኑ በሰአት ይሁን፣ የንባብ ፍጥነት እድገታቸውን በቻርት ለይ ይመዝግቡ<br>**አረፍተነገር አነባበብ ፡-** አንድ አረፌረተነገር ያንቡ<br>**በርከት ያለጊዜ**<br>በዚህ ግዜ ለተለያዩ ቃላት ትኩረት ይስጡ<br>**የመጽሄት ምላሽ**<br>ተማሪዎች በንባብ በመጽሄት ግንኙነት ድረጉ<br>**የጽህፈት አደረጃጀት**<br>መምህር የቃላት ካርታ ያዘጋጁ ፣ስሜት ገላጭ ቻርትእና ቃላትን መፈለግ ከተመሳሳይ ፍቺ ጋር በማዛመድ ያሳዩ።<br>**የቃል ጽህፈት**<br>መምህር ሶስት ተራ አረፍተ ነገር በቃል ይመስረቱላቸው (ተማሪዎች ያዳምጣሉ) በአረፍተነገር ውስጥ ያሉትን እያንዳንዱን ቃል በትክክል | |

| ብቃት | ይዘት | የመማር ስልቶች እና መርጃ መሳሪያ | ምዘና |
|---|---|---|---|
| | | ይጽፋሉ፡፡ ተማሪዎች ያዳምጣሉ፡፡ (ቃላት፣አረፍተነገር እና የግድግዳ ቃላት) ከዚያም ቃላትን በትክክል ይጽፋሉ፡፡<br>**ማጠቃለያ**<br>ከልምምድ በኋላ ማጠቃለል እና ከጽሁፍ የወጣውን መረጃ ማዛመድ ሆሄን ከድምጽ ጋር ማዛመድ ፣ቃላት፣አረፍተነገር<br>**ስርአተ ነጥብ**<br>አገላለጽን ማሳደግ፣መምህር ስለስርአተ ነጥብ ቀለል ባለ መልኩ ይግለጹላቸው እንዴት ተቀላጥፎ እንደሚነበብ ያሳዩአቸው፡፡<br>**የቡድን ጽህፈት**<br>መምህር ምሳሌ በመሆን እና በማማቻቻ በቡድን አጫጭር ታሪኮችን እንዲጽፉ ያድርጉ፡፡ | |

**ምዕራፍ ዘጠኝ፡ ዲጂታል ቁስ (18 ክፍለጊዜ)**

**የሚጠበቀው ውጤት**

**ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-**

- ካዳመጡት የምንባብ ጽሁፍ ውስጥ ዋናውን መልእክት ያደራጃሉ
- ካዳመጡት ምንባብ ውስጥ ለወጡ ቃላት ተመሳሳይ ፍቺ ይሰጡ
- ለቃላት አውዳዊ ፍቺ ይሰጣሉ
- ቃላትን ከቅጥያዎች ጋር ያነባሉ
- አረፍተነገር በትክክል ይጽፋሉ

| ብቃት | ይዘት | የመማር ስለቶችና መርጃ መሳሪያ | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ➢ ካዳመጡት ምንባብ ጽሁፍ ውስጥ ዋናውን መልእክት ያደራጃሉ<br>➢ ካዳመጡት ጽሁፍ ለወጡ ቃላት ተመሳሳይ ፍቺ ይስጡ | ➢ **ማዳመጥና መናገር**<br>➢ **የንግግር ድምጽ ግንዛቤ**<br>➢ **የትእምርተ ድመጽ ግንዛቤ**<br>➢ **የቃላት ጥናት** የተለመዱ ቃላት (ትምህርታዊ)<br>- የስያሜ ጽንሰ ሃሳብ | **መምህር** ተማሪዎችን የቀደመ እወቀታቸውን ይቀስቅሱ፡፡ ተማሪዎች በቡድን ይቀመጡና ከጽሁፍ ውስጥ የተለየው ክፍል ላይ ያተኩሩ፡፡ከጽሁፉ ውስጥ የሚያገኙትን መረጃ ይሙሉ፡፡ እያንዳንዱ ቡድን ሃሳቦችን በመያዝ እርስ በእርሰ ሃሳብ ይለዋወጡ፡፡<br>**ተቃራኒ ቃላት**<br>መምህረ ተቃራኒ ፍቺ ያላቸውን ቃላት ይለዩ፡፡የግድግዳ ቃላትን ይጻፉላቸውና በግድግዳ ላይ ያንጠልጥሉላቸው፡፡ ተማሪዎች ከተቃራኒ ፍቺያቸው ጋር ያዛምዱ፡፡እንዲሁም ከአውዳዊ ፍቺያቸው ጋር ተዘውታሪ ቃላትን ከቅጥያቸው ጋር ያዛምዱ፡፡<br>**የቃላት ምስረታ**<br>**መምህር** ተማሪዎች ቃላትን መጻፍ ይለማመዱ በጥቁር ሰሌዳ ላይ | ➢ የጽሁፍና የቃል ጥያቄ መጠየቅ<br>➢ አካላዊ ምላሽ<br>➢ ተማሪዎች ለሚያሳዩት አካላዊ ጥያቄ በተናጠል ምላሽ መስጠት<br>➢ ኢ-መደበኛ ቁጥጥር<br>➢ ምልከታ<br>➢ እይታዊ ውክልና<br>➢ ሚና በመቀያየር |

| ብቃት | ይዘት | የመማር ስለቶችና መርጃ መሳሪያ | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ➢ ለቃላት አውዳዊ ፍቺ ይሰጣሉ<br>➢ ቃላትን ከቅጥያዎች ጋር ያነባሉ<br>➢ አረፍተነገር በትክክል ይጽፋሉ | ➢ **ማፍለቅና መረዳት**<br>➢ **መነጠልና ማጣመር**<br>➢ **ማንበብ ፍጥነት** ፣ትክክለኛነት፣አገላለጽ፣ መረዳት<br>➢ **በትክክል መጻፍ**<br>➢ **ድምጸትን የመገንዘብ ችሎታ** | ይጻፋላቸው<br>**የተለመዱ ቃላት**<br>ቃላትን በፍጥነት በመረዳት በአውድ ውስጥ እና ከአውድ ውጪ ያላቸውን ፍቺ ይስጡ።<br>**የግድግዳ ላይ ቃላት**<br>**ተማሪዎች** አዳዲስ ቃላትን በቁርጥራጭ ወረቀት ላይ ይጻፉ ለመርጃነት በግድግዳ ላይ ይለጥፉ<br>**ተማሪዎች** ቃላትን ማፍለቅ ይለማመዱ (ስእሎች፣ የቃላት ወይም የፊደላት/ድምጾች ካርድ፣ ባለቀለም ወረቀት ፣ቅርጻቅርጽ፣ካርቶን ፣ጥቁር ሰሌዳ ወዘተ.) ይጠቀሙ።<br>**ከአገባቡ ጋር ማገናኘት**<br>ተማሪዎች ምልእክቶቹን በማንበብ ከጽሁፉ ጋር ያገናኙ።<br>**በሂደት ማጠናቀቅ-**<br>ማሚቶ፣ የህብረት ንባብ፣ የጥንድ ንባብ፣ የዝምታ ንባብ<br>**በሰአት የተገደበ ንባብ**<br>አንድን ምንባብ ሰዐት ይዞ ሁለት ጊዜ ማንበብ እና ለውጡን በቻርት ላይ መመዝገብ፤<br>**ቁርጥራጭ (ክፍልፋይ)**<br>ተማሪዎች ሀረጋትን ይጠቀሙ።<br>**የመጽሄት ምላሽ**<br>ተማሪዎች በንባብ በመጽሄት ግንኙነት ድረጉ።<br>**የተለያዩ አማራጮችን ይጠቀሙ** | ሃላፊነት መውሰድ<br>➢ ማጠቃለያ ውጤት<br>➢ አቀራረብ. አቀራረብ |

| ብቃት | ይዘት | የመማር ስለቶችና መርጃ መሳሪያ | ምዘና |
|---|---|---|---|
| | | **የጽህፈት አደረጃጀት**<br>መምህር የቃላት ካርታ ያዘጋጁ ፣ስሜት ገላጭ ቻርትእና ቃላትን መፈለግ ከተመሳሳይ ፍቺ ጋር በማዛመድ ያሳዩ<br>**ጥያቄ** ለተማሪዎች ጥያቄ መመስረቻ ጊዜ ይስጧቸው<br>**ደጋግሞ በቃል ማንበብ**<br>ተማሪዎች ምንባብን ደጋግመው ያንብቡ፣ ለንባብ ጊዜ ይስጧቸው ለውጡን በቻርት ላይ ይጻፉ።<br>**ስርአተ ነጥብ**<br>አገላለጽን ማሳደግ፣መመህር ስለስርአተ ነጥብ ቀለል በለ መልኩ ይግለጹለቸው እንዴት ተቀላጥፎ እንደሚነበብ ያሳዩአቸው<br>**በሰአት የተገደበ ንባብ**<br>አንድን ምንባብ ሰዐት ይዞ ሁለት ጊዜ ማንበብ እና ለውጡን በቻርት ላይ መመዝገብ<br>**አረፍተነገር አነባበብ**<br>አንድ አረፈተ ነገር ያንቡ።<br>**በርከት ያለጊዜ**<br>በዚህ ግዜ ለተለያዩ ቃላት ትኩረት ይስጡ<br>**የቃል ጽህፈት**<br>**መምህር** ሶስት ተራ አረፍተነገር በቃል ይመስረቱላቸው(ተማሪዎች ያዳምጡ) በአረፍተነገር ውስጥ ያሉትን እያንዳንዱን ቃል በትክክል ይጻፉ።(ቃላት፣አረፍተነገር እና የግድግዳ ቃላት) ከዚያም ቃላትን በትክክል ይጽፋሉ። | |

| ብቃት | ይዘት | የመማር ስለቶችና መርጃ መሳሪያ | ምዘና |
|---|---|---|---|
| | | **ማጠቃለያ**<br>ከልምምድ በኋላ ማጠቃለል እና ከጽሁፍ የወጣውን መረጃ ማዛመድ ሆሄን ከድምጽ ጋር ማዛመድ ፣ቃላት፣አረፍተነገር<br>**የመጽሄት ምላሽ**<br>መምህር በየእለቱ በክፍል ውሰጥ ከሚያከናውኑት ተግባር ሁለቱን እንዲመዘግቡ ያድርጉ። ተማሪዎች ባለፈው ክፍለጊዜ የተማሩትን እንዲያቀርቡ ያድርጉ።( በመጽሄት ንባብ ይገናኙ) | |

**ምዕራፍ አስር፡ የዱር እንስሳት (18 ክፍለ ጊዜ)**

**የሚጠበቀው ውጤት**

**ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-**

- ካዳመጡት ምንባብ ዋናውን መልእክት በጽሁፍ ዘገባ ያቀርባሉ፡፡
- የምንባቡን ሃሳብ ከተጨባጭ ህይወታቸው ጋር ያዛምዳሉ፡፡
- ቃልአጋኖ እና የጥያቄ መምልክት ይጠቀማሉ፡፡
- አቀላጥፈው ያነባሉ፡፡
- ለደረጃቸው የሚመጥን አረፍተነገር ይጽፋሉ፡፡

| ብቃት | ይዘት | የመማር ስልት እና መርጃ መሳርያ | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ➢ ካዳመጡት ምንባብ ዋናውን መልእክት በጽሁፍ ዘገባ ያቅርባሉ<br>➢ የምንባቡን ሃሳብ ከተጨባጭ ህይወታቸ | ➢ **ማዳመጥእና መናገር**<br>➢ **የንግግር ድምጽ ግንዛቤ**<br>➢ **የትዕምርተድ መጽ ግንዛቤ**<br>➢ **የቃላት ጥናት** የተለመዱ ቃላት | **መምህር** ተማሪዎችን የቀደመ እወቀታቸውን ይቀስቅሱ፡፡ በምንባቡ ውስጥ ስለሚገኝ አንድ እንስሳ አረፍተ ነገር ጽፈው በቃል ዘገባ ያደርጋሉ፡፡<br>ቦታ በመቀያየር መገጣጠም መምህር ተማሪዎችን ፊደላትን በመጠቀም በማጥፋት፣ በመቀነስና በመቀያየር ያጫውቷቸው፡፡<br>ሀ.**ማጥፋት** ተማሪዎች የሰሙትን ቃል የመጀመሪያ ድምጽ አጥፍተው ያንብቡ<br>**ለ መጨመር** ተማሪዎች ያዳመጡት ድምጽ ላይ ድምጽ ወይም ፊደል ይጨምሩ<br>ሐ. **መቀያየር ተማሪዎች** ያደምጡና ሆሂያቱን /ድምጹን ያቀያይሩ<br>**ማፍለቅ** መምህር ሰርተው ያሳዩ፣ቃላትን ያሳዩ፣የተመረጡ ድምጾችን ይጥሩና ያጣምሩ (ሆሄን ከድምጽ አቀናጅቶ መጠቀም) (ስእሎች፣ የቃላት ወይም የፊደላት/ድምጾች ካርድ፣ ባለቀለም ወረቀት ፣ቅርጻቅርጽ፣ካርቶን ፣ጥቁር ሰሌዳ ወዘተ.) | ➢ የጽሁፍና የቃል ጥያቄ መጠየቅ<br>➢ አካላዊ ምላሽ<br>➢ ተማሪዎች ለሚያሳዩት አካላዊ ጥያቄ በተናጠል ምላሽ መስጠት<br>➢ ኢ-መደበኛ ቁጥጥር<br>➢ ምልከታ |

| ብቃት | ይዘት | የመማር ስልት እና መርጃ መሳርያ | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ው ጋር ያዛምዳሉ<br>➢ ቃለአጋኖ እና የጥያቄ መምልክት ይጠቀማሉ<br>➢ አቀላጥፈው ያነባሉ ለደረጃቸው የሚመጥን አረፍተነገር ይጽፋሉ | (ትምህርታዊ) የስያሜ ጽንሰ ሃሳብ<br>➢ **ማፍለቅና መረዳት**<br>➢ **መነጠልና ማጣመር**<br>➢ **የማንበብ** ፍጥነት ፣ትክክለኛነት፣አገላለጽ፣መረዳት<br>➢ **በትክክል መጻፍ**<br>➢ **ድምጸትን የመገንዘብ ችሎታ** | **ጽሁፍን ማገናኘት**<br>ተማሪዎች ማፍለቅ ይለማመዳሉ<br>**ደጋግሞ በቃል ማንበብ**<br>**ተማሪዎች** ምንባብን ደጋግመው ያንብቡ፣ ግብረመልስ በመምህር ፣ በጓደኛ እና በቤተሰብ ይሰጣቸው<br>**በሰአት የተገደበ ንባብ**<br>አንድን ምንባብ ሰዐት ይዞ በተደጋጋሚ ማንበብ እና ለውጡን በቻርት ላይ መመዝገብ<br>**አረፍተነገር አነባበብ** ፡- አንድ አረፈተ ነገር በተለያየ መንገድ ያንብቡ፡፡ በዚህ ጊዜ የተለያዩ ድምጾችን ጎላ አድርገው ያንብቡ፡፡<br>**ስርአተ ነጥብ** አገላለጽን ማሳደግ፣መምህር ስለስርአተ ነጥብ ቀለል በለ መልኩ ይግለጹለቸው እንዴት ተቀላጥፎ እንደሚነበብም ያሳዩአቸው<br>**የመጽሄት ምላሽ** መምህር በየእለቱ በክፍል ውሰጥ ከሚያከናውኑት ተግባራት ሁለቱን እንዲመዘግቡ ያድርጉ፡፡ ተማሪዎች ባለፈው ክፍለጊዜ የተማሩትን እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡( በመጽሄት ንባብ ይወያዩ) | ➢ እይታዊውክልና<br>➢ ሚና በመቀያየር ሃላፊነት መውሰድ<br>➢ ማጠቃለያ ውጤት<br>➢ አቀራረብ. አቀራረብ |

# አማርኛ

## እንደመጀመሪያ ቋንቋ
## የመምህር መምሪያ

፪ኛ ክፍል